# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ


## የሂዩማኒትስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
## የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር


**በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ**

**የቀረበ ጥናት**

# በአማራና በትግራይ ክልላዊ መንግስታት 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት
## (በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች)


በ

ገብረመስቀል ገብረእግዚአብሔር



ነሐሴ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በአማራና በትግራይ ክልላዊ መንግስታት 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት (በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች)

በ

ገብረመስቀል ገብረእግዚአብሔር

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒትስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

ነሐሴ 2009 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒትስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

## በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ

## የቀረበ ጥናት

## በአማራ በትግራይ ክልላዊ መንግስታት 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት

## (በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች)


በ

ገብረመስቀል ገብረእግዚአብሔር


### የፈተና ቦርድ አባላት

ስም

------------------------------------ ፊርማ------------------ ቀን-----------------------

አማካሪ

------------------------------------ ፊርማ-------------------- ቀን---------------------

------------------------------------- ፊርማ---------------------- ቀን--------------------

ፈታኝ

ነሐሴ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ምስጋና

ይህ ጥናት ከዳር እንዲደርስ ያለምንም መሰልቸት የተለያዩ አቅጣጫዎችን በመጠቆም፣ ስህተቶችን በማረምና በማማከር መልካም ትህትናቸው ለለገሱኝ ለአማካሪዬ ዶ/ር ፀጋይ አረጋይ ለዚህ ሁሉ ጥረታቸው ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ የጥናቱን ሙሉ የገንዘብ ወጪ የሸፈኑ ተቋማት በመሆናቸው ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ (የማዕርነትና የሳቃ) እና በትግራይ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ (የየጭላና የፌናርዋ) የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን በመስጠት ከፍተኛ እገዛ ስላደረጉልኝ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም በገንዘብም ሆነ በሞራል እየደገፉ እዚህ እንድደርስ ላደረጉኝ ለውድ አባቴ ቄስ ገ/እግዚአብሔር ታፈረ እና ለውዷ እናቴ ወ/ሮ ሐዳሽ ገ/ሕይወት ውለታችሁን አምላክ ይክፈልልኝ፡፡ ለባለቤቴ ወ/ሮ ምጽላል ካልአዩ፣ ለልጆቼ ህጻን ንግስተ ማርያም ገ/መስቀልና ለህጻን ሐመልማል ገ/መስቀል ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እህቶቼንና ወንድሞቼን እንዲሁም የዶርሚ ልጆችና ጓደኞቼን አመሰግናለሁ፡፡

# ማውጫ

ምስጋና ............ i
ማውጫ ............ ii
ሰንጠረዥ ማውጫ ............ v
አጠቃሎ ............ vi
ሙዳየ ቃላት ............ vii
ምዕራፍ አንድ
መግቢያ ............ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ............ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............ 4
1.3 የጥናቱ ዓላማ ............ 5
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ............ 5
1.5 የጥናቱ ወሰን ............ 6
1.6 የጥናቱ ውስንነት ............ 7
ምዕራፍ ሁለት
የተዛማጅ ፅሑፍ ቅኝት ............ 8
2.1 የተከታታይ ምዘና ምንነት ............ 8
2.2 የምዘናና ግምገማ ዓይነቶች ............ 9
2.3 የተከታታይ ምዘና ባህሪያት ............ 10
2.3.1 ተከታታይ ምዘና ስርዓታዊ ነው ............ 11
2.3.2 ተከታታይ ምዘና የተደጋጋሚ ጊዜ የምዘና ውጤት ነው ............ 11
2.3.3 ተከታታይ ምዘና ሁሉን አቀፍ ነው ............ 11
2.3.4 ተከታታይ ምዘና አቅጣጫ ጠቋሚ ነው ............ 12
2.4 የተከታታይ ምዘና ዓላማ ............ 12
2.5 የተከታታይ ምዘና አተገባበር ............ 13
2.6 የተከታታይ ምዘና የሂደት ደረጃዎች ............ 14
2.6.1 ከማስተማር በፊት ............ 15
2.6.2 በመማር ማስተማር ሂደት ............ 15
2.6.3 ከማስተማር በኋላ ............ 15
2.7 የአጠቃላይና የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ............ 16
2.7.1 የአጠቃላይ ተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ............ 16

2.7.2 የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ..... 16
2.7.2.1 የቃል ጥያቄ ..... 18
2.7.2.2 ምልከታ ..... 19
2.7.2.3 ቅድመ ፈተና ..... 19
2.7.2.4 የቤት ሥራ ..... 20
2.7.2.5 ፈተና እና ሙከራ ..... 20
2.7.2.6 ፕሮጀክት ..... 21
2.7.2.7 የመምህር ተማሪ ውይይት ..... 22
2.7.2.8 ሰነደ ትምህርት ..... 23
2.7.2.9 የራስ ምዘና ..... 24
2.7.2.10 የጓደኛ ለጓደኛ (የቢ.ጤ) ምዘና ..... 25
2.7.2.11 እየወጡ ማቅረብ ምዘና ..... 26
2.8 ተከታታይ ምዘናን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ምክንያቶች ..... 26
2.9. ብዙ ተማሪዎች ባሉበት የመማሪያ ክፍል የምዘና ዘዴዎች ..... 27
2.10 የግብረ-መልስ ምንነት ..... 28
2.10.1 የማወዳደር ግብረ-መልስ ..... 29
2.10.2 የውጤቶች ወይም የሂደት ግብረ-መልስ ..... 29
2.10.3 ገላጭ ወይም ግምገማዊ ግብረ-መልስ ..... 30
2.11 ብዙ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል ውስጥ የተከታታይ ምዘና አተገባበር ..... 31
2.12 ብዙ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል የምዘና መርሆች ..... 31
2.13 የምዘናና ግምገማ ጥቅሞች ..... 32
2.14 የቀደምት ተጓዳኝ ጥናቶች ቅኝት ..... 33
ምዕራፍ ሦስት
የአጠናን ንድፍና ዘዴ ..... 36
3.1 የጥናቱ ንድፍ ..... 36
3.2 የናሙና አመራረጥ ..... 36
3.3 የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ..... 37
3.3.1 የፅሑፍ መጠይቅ ..... 37
3.3.2 ሰነድ ፍተሻ ..... 37
3.3.3 ቃለ መጠይቅ ..... 38

3.3.4 ምልከታ ........ 38
3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ........ 38
ምዕራፍ አራት
የመረጃ ትንተና........ 39
4.1 የመምህራን አጠቃላይ መረጃ ........ 39
4.2 ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና........ 41
4.3 ከመምህራን ጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና ........ 56
4.3 ከመምህራን ልቅ ጥያቄዎች የተገኘ መረጃ ትንተና........ 73
4.4 ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ ትንተና........ 75
4.5 በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ስለተከታታይ ምዘና አተገባበር ያላቸው አንድነትና ልዩነት ........ 76
4.5.1 በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ስለተከታታይ ምዘና አተገባበር ያላቸው አንድነት ........ 76
4.5.2 በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ስለተከታታይ ምዘና አተገባበር ያላቸው ልዩነቶች ........ 77
ምዕራፍ አምስት
ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሐሳቦች........ 79
5.1 ማጠቃለያ........ 79
5.2 የጥናቱ መደምደሚያ........ 81
5.3 የመፍትሔ ሐሳቦች ........ 82
ዋቢ መጻሕፍት........ 101
አባሪዎች........ 104

# ሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1 ፡- የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ......... 17

ሰንጠረዥ 2 ፡- የሚከተለው ሠንጠረዥ መቼ እና እንዴተ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘናን መጠቀም እንደሚቻል ያሳያል። ......... 18

ሰንጠረዥ 3 ፡- የተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ ......... 39

ሠንጠረዥ 4 ፡- የተከታታይ ምዘና አጠቃላይ መርህን በተመለከተ ......... 41

ሰንጠረዥ 5 ፡- በአራቱም ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በተከታታይ ምዘና ጠቀሜታ ዙሪያ የሰጡት ምላሽ ......... 45

ሰንጠረዥ 6 ፡- የተከታታይ ምዘና እርማት አሰጣጥ፣ ደካማና እና ጠንካራ ጎኖችንና መሻሻል ጉዳዮች የሚያሳይ መረጃ ......... 49

ሰንጠረዥ 7 ፡- ከምዘና ስልቶች ጋር የተገናኘ የጽሑፍ መጠይቅ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ ......... 53

ሰንጠረዥ 8 ፡- የተከታታይ ምዘና አሰጣጥ የጊዜ ድግግሞሽ በተመለከተ ......... 55

ሰንጠረዥ 9 ፡- መምህራን የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ተማሪዎችን ለመመዘን ምን ያህል እንደሚጠቀሙባቸው የሚያሳይ ......... 57

ሰንጠረዥ 10 ፡- የተከታታይ ምዘና አጠቃላይ መርህን በተመለከተ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰጡት ምላሽ ......... 59

ሰንጠረዥ 11. ፡- የተከታታይ ምዘና አስፈላጊነት የመምህራን ምላሽ ......... 60

ሰንጠረዥ 12 ፡- በተከታታይ ምዘና እቅድ ማውጣትና በእቅዱ መሰረት መስራት የሚኖረውን ሚና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰጡት ምላሽ ......... 62

ሰንጠረዥ 13 ፡- በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎች የሚኖራቸውን ሚና በተመለከተ ......... 64

ሰንጠረዥ 14 ፡- የተከታታይ ምዘና ጥቅምና ዓላማ በተመለከተ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰጡት ምላሽ ......... 66

ሰንጠረዥ 15 ፡- የሰነድ ፍተሻ መከታተያ ቅጽ ......... 75

ሰንጠረዥ 16፡- የተከታታይ ምዘና ተግባራዊነትን በተመለከተ ተተኳሪ መምህራን የሰጡት ምላሽ ......... 70

ሰንጠረዥ 17 ፡- በአራቱም ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ምጋቤ ምላሽ ወይም አስተያየት አሰጣጥ በተመለከተ ......... 68

# አጠቃለሎ

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማራና በትግራይ ክልላዊ መንግስታት 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል የተከታታይ ምዘና አተገባብር ንጽጽራዊ ጥናት በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎች ለመሰብሰብ ዐቢይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጽሑፍ መጠይቅና የሰነድ ፍተሻ የተጠቀመ ሲሆን ምልከታና ቃለ መጠይቅ ደግሞ ደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተጠቅሟል፡፡ በእነዚህ መሳሪያዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች ዓይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴዎችን በመጠቀም የተገኙትን ውጤቶች በገለጻና በቁጥር መልኩ ተተንትነዋል፡፡ በጥናቱም የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ በጽሑፍ መጠይቅ ሁለቱም የጥናቱ ተተኳሪ ቡድኖች ስለተከታታይ ምዘና ጥቅሞች ጥሩ ግንዛቤ እንዳላቸው ቢረጋገጥም፤ ተከታታይ ምዘናን በዕቅድ የተመራና ቀጣይነት ባለው መልኩ በመተግበር ግን በትግራይ ክልላዊ መንግስት ስር የሚገኙ (የየጭላና የፈናርዋ) መምህራን ተሽለው ተገኝተዋል፡፡ በተከታታይ ምዘና ዘዴዎች አጠቃቀም፣ ዝቅተኛ ውጤት ላገኙ ተማሪዎች በሚደረጉ የማሻሻያ እገዛዎች፣ በጽሑፋዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥና በተከታታይ ምዘና ሰነዶች አጠቃቀም የትግራይ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቤቶች የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ነገር ግን በሙከራና በግል ስራ (ፕሮጀክት) በተከናወኑ የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ለተሰበሰቡ ውጤቶች የአማራ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን ተሽለው ተገኝተዋል፡፡ ከዚህ ጋር በማያያዝ የክፍለ ጊዜ ጫና፣ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ በተከታታይ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ አለመገኘት ወይም መቅረትና ስለተከታታይ ምዘና አተገባበር ከአንድ መምህር በቀር፣ ድጋፍ አለማግኘት በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዋና ዋና የችግር ምንጭ መሆናቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በመጨረሻም ከጥናቱ የተገኙ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሚተገበረው ምዘና በዕቅድ የተመራ ቢሆን፣ ተከታታይ ምዘና ሲጠቀሙ ለውጤት ሳይሆን የመማር ማስተማር ዘዴ ለመምረጥ ቢጠቀሙበት፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን ጥቆማዎች ተሰጥተዋል፡፡*

## ሙዳየ ቃላት

ሙከራ (Quiz) = መደበኛ ያልሆነ በአንድ ይዘት ላይ የተመሰረተና አጭር የምዘና ስልት ሲሆን የተማሪዎችን የመማር እድገት ለመለካት የሚያገለግል ጽንሰ ሐሳብ ነው። የክፍለ ጊዜ ትምህርት ከመቅረቡ በፊትና በኋላ የሚከናወን የምዘና አይነት

ቴስት (Test) = መደበኛ የሆነ የተማሪዎችን የመማር እድገት ለመለካት የሚያገለግል ሆኖ ከሁለት ከማይበልጡ የትምህርት ይዘቶች የሚወጡ ጥያቄዎችና የትምህርት ተግባራት የያዘ የምዘና ስልት

ፈተና (Examination) = መደበኛ የሆነ ብዛት ያላቸውን የትምህርት ይዘቶችን የሚያካትተውና የተለያዩ የፈተና አይነቶችን ያየዙ ጥያቄዎች ሲሆኑ ከአንድ ኮርስ የትምህርት አይነት ወይም ስልጠና ከተጠናቀቀ በኋላ የምዘና አይነት

ሥፈራ (Measurement) = ማለት የተማሪዎችን የባህሪ ለውጥን በቁጥር መግለፅ ያመለክታል። ሥፈራ በሌላ አገላለፅ የተማሪዎችን የመማር ውጤቶች ወደ ቁጥር የመለወጥ ሂደትን የሚያመለክት የምዘና አይነት

ምዘና (Assessment) = ማለት በተለያዩ የምዘናና ግምገማ ስልቶች ለምሳሌ በሙከራ፣ ምልከታ፣ በቡድን ስራ፣ በክፍል ስራ፣ በቤት ስራ ወዘተ ስለተማሪዎች የመማር ዕድገት መረጃ መሰብሰብ፣ ማደራጀትና ትርጉም መስጠትን የሚያመለክት ፅንሰ ሐሳብ

ግምገማ (Evaluation) = ማለት በምዘና የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ የሚከናወን ዳኝነትና ውሳኔ የመስጠት ሂደት

ሰነደ ትምህርት (Portifolio of evidence) = በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት እየሰሩ ያጠራቀሟቸው የተለያዩ ክምችት

ቅድመ ፈተና = ወደፊት ለማስተማር ስለምናቅደው ርዕስ ተማሪዎች ያላቸውን የመማር ግንዛቤ ለማወቅ የምንጠቀምበት የምዘና ስልት

ተለምዷዊ ምዘና = በፅሁፍ  ፈተና ላይ ብቻ ያተኮረ የምዘና ስልት ሆኖ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀመው ተማሪው አልፏል ወይስ ወድቋል ብሎ ውሳኔ ለመስጠትነው

ተከታታይ ምዘና = በየጊዜውና በየወቅቱ ተማሪዎች ስርዓተ ትምህርቱ በነደፈው አላማ መሰረት ትምህርቱን መከታተላቸውን መምህሩ በመመዘኛ መሳሪያዎች የሚያረጋግጥበት ዘዴ ነው ፡፡

አማካይ ውጤት  = የተገኘው ጠቅላላ ውጤት ከተደመረ በኋላ በተሳታፊዎች ተካፈሎ የሚገኘው ውጤት

ልይይት = የበቡድን አንድ አማካይ ውጤት ሲቀነስ የቡድን ሁለት አማካይ ውጤት

## አህጽሮተ ቃላትና የምልክቶች ትርጉም

AED = Academy for Educational Development

GEQIP = General Education Quality Improvement Package

ICDR = Institute for Curriculum Development and Research

TESO = Teacher Education System Overhaul

USAID = United States Agency for International Development

X1 = የአማራ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቤቶች የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት

X2 = የትግራይ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቤቶች የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ አማካይ ውጤት

X1-X2 = የሁለቱም ክልሎች አማካይ ውጤት ልይይት

# ምዕራፍ አንድ
# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋን ማስተማር እና ምዘና በጣም ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው ነገሮች በመሆናቸው ተነጣጥለው አይታዩም፡፡ በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ የሚካሄዱ ምዘናዎች የቋንቋ መማር ማስተማሩ ሂደት ዋነኛ አካላት ናቸው፡፡ በመሆኑም ተስፋ (2000) Waal and Andersen (1991፡3) ን ጠቅሰው እንደሚገልፁት ቋንቋን የማስተማር አላማዎች ግባቸውን ሊመቱ የሚችሉት ምዘናን በተግባር ላይ በማዋል ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርት ሂደትን ይበልጥ ውጤታማና ፍሬያማ ከሚያደርጉት መካከል ለትምህርቱ የምንጠቀምበት የማስተማር ዘዴና የመመዘኛ ስልቶቹ በዋነኛነት የሚጠቀሱ መሆናቸውን አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ (2000፣ 175) ይገልፃል፡፡

ምንም እንኳን የተለያዩ ምሁራን ቋንቋን በማስተማርና በምዘና መካከል ከፍተኛ ቁርኝት እንዳለ ቢገልፁም፣ የትኛው የምዘና ዓይነት የቋንቋ መማር ማስተማሩን ሂደት የበለጠ እንደሚያግዘው ግልፅ የሆነ ነገር አላስቀመጡም፡፡ በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የሚሰጡት ሙከራዎችና የማጠቃለያ ፈተናዎች ተማሪው በአንድ ቋንቋ ትምህርት ላይ የሚያሳየውን ጠንካራና ደካማ ጎን እንዲሁም ችሎታ ሙሉ በሙሉ አያሳዩም፡፡ እንዲሁም AED/BESO II (2006:27) እንደሚገልፀው፣ በእያንዳንዱ የትምህርት ምዕራፍ ወይም ሴሚስተር ማጠቃለያ ላይ የሚሰጡት ፈተናዎች ተማሪው በየዕለቱ የሚያሳያቸውን ሁለንተናዊ ባህርያት እንዲሁም የሚያከናውናቸውን ተግባራት አያመለክቱም፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ሐሳብ በተጨማሪ ሂደታዊ ምዘና (Formative assessment) መምህራን በሂደት ባለው ትምህርት በተወሰነ ጊዜ ለተማሪዎቻቸው የሚመዝኗቸው የመማር ማስተማሩን ውጤታማ ለማድረግ የሚያደርጉት ምዘና መሆኑን፣ የተማሪዎች የመማር ብቃት ለመመዘን እንደሚያገለግል በ(WIKPEDIA 2015) ተገልጧል፡፡ የተከታታይ ምዘና ዋና አላማ ተማሪው ወድቋል፣ ወይም አልፏል ለማለት ወይም ነጥብ /Mark/ ለመስጠት ሳይሆን የመማር ማስተማር ሂደት ለመመዘን ነው ተስፋ (2000)፣ የ(TESOL፣ 2003) ጠቅሰው እንደገለጹት፡፡

ከላይ ከቀረበው ሐሳብ መረዳት የሚቻለው ተከታታይ ምዘና የመማር ማስተማሩ አካል በመሆን የትምህርቱን ዑደት ለመከታተልና ተማሪዎችን ለመደገፍ እንጂ የማጠቃለያ ፈተና አካል

አድርጎ መወሰድ እንደሌለበት ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ጠቅላይ (መደበኛ) ምዘና (Summative assessment) የምንለው ደግሞ የተማሪዎች ስኬት፣ የትምህርቱ ውጤትና ውሳኔ ለመስጠት ነው፡፡

በሂደታዊ ተከታታይ ምዘና እና ጠቅላይ (መደበኛ) ምዘና መካከል ያለው ልዩነት በመመዘኛ መሳሪያ ሳይሆን በዓላማው መሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ አንድ መምህር ፈተና ቢፈትን ለተለያዩ ዓላማዎች ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ፈተናው ፈትኖ የመማር ማስተማሩን ሂደት ብቻ ለመገምገም ሊጠቀምበት ይችላል፣ ወይም ደግሞ ተማሪዎችን መዝኖ የመጨረሻ ውጤት ሊሰጠው ይችላል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ሂደታዊ ምዘና ተማሪዎች በሚማሩት ትምህርት ላይ የሚያሳዩትን መሻሻል ለማወቅ ሂደታዊና ተከታታይ በሆነ መልኩ የሚከናወን የምዘና ዓይነት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ አካሄዱም ተከታታይ በሆነ መልኩ ተማሪዎች በትምህርታቸው ላይ የሚሳዩትን አቅምና ብርታት እንዲሁም ደካማና ጠንካራ ጎን ለማውቅ በየጊዜው የሚካሄድ የምዘና ዓይነት መሆኑን ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት ይቻላል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ Coulingford (1995፡75) የተከታታይ ምዘናን አስፈላጊነት አስመልክተው ሲገልፁ የሚከተለውን ይላሉ፡-

> *ማንኛውም የማስተማር ስራ ከምዘና ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነገር ነው፡፡ በክፍል ውስጥ ገብቶ ስለአንድ ርዕሰ ጉዳይ ለተማሪዎች ገለፃ ሰጥቶ መውጣት ቀላል ነገር ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ተማሪዎች የተማሩትን ይዘት ምን ያህል አውቀውታል? በሂደት ምን ዓይነት ችግር አጋጥሟቸዋል? ብሎ ተማሪዎችን በተከታታይ መመዘኑ ነው፡፡*

እስከ አሁን በተለያዩ ምሁራን ስለተከታታይ ምዘና ከተሰጡት ብያኔዎች መገንዘብ እንደተቻለው ተከታታይ ምዘና ከመማር ማስተማሩ ሂደት ጋር በተቀናጀ መልኩ የሚካሄድ የምዘና ዓይነት መሆኑንና የትኩረት አቅጣጫውም አንድ ትምህርት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ተማሪው ምን እንደተገነዘበና ምን ምን ዓይነት መሻሻል እንዳሳየ በሂደት የሚመዘንበት የምዘና ስርዓት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የተከታታይ ምዘና ዋና ትኩረት ተማሪዎች በሂደት የሚያሳዩዋቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለይቶ የማስተካከል ሀሳቦችንና የእርምት ርምጃ መስጠት ነው (Wikpedea 2015)::

በአጠቃላይ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና እንደ (Wikpedea 2015) አገላለፅ ስድስት ጠቀሜታዎች አሉት ይላል፡፡ እነሱም፡-

1. ጥቅል የዕውቀት ስሜት ያሳድጋል
2. የመማር አቅም ያጎለብታል
3. የምዘና ዓላማ ግልፅ ያደርጋል
4. ከደካማነት ወደ ጠንካራነት ያሸጋግራል የተማሪዎቹ የግል ግንዛቤ ያሳድጋል
5. ለመምህሩም የማስተማር ብቃቱን እንዲፈትሽ ያስችላል፡፡

ከምሁራኑ አገላለጽ መረዳት የሚቻለው ተከታታይ ምዘና በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ነው፡፡ ስለተከታታይ ምዘና ጠቀሜታ በክለሳ ድርሳናት ርዕስ በሰፊው የሚብራራ ይሆናል፡፡

እንደ Livingston (2001፡29-30) አገላለፅ ተከታታይ ምዘና ለተማሪዎች ከሚሰጠው ጥቅም ጎን ለጎን ለመምህራንም የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ መምህራን የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ስልቶችን ወይም ዘዴዎችን ተጠቅመው ተማሪዎቻቸውን በሚመዝኑበት ጊዜ ስለ ተማሪዎች ተነሳሽነት፣ ንቁ ተሳትፎ፣ መሻሻል፣ ባህርይ ወዘተ አስፈላጊውን የማስተካከያ መንገድ እንዲቀይሱ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለተከታታይ ምዘና ሲነሳ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸው ዕውቀትና አመለካከት ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ እንደሆነ ተስፋ (2000) እና (Teshome 2001) ይገልጻሉ፡፡

> ተከታታይ ምዘና ለቋንቋ መምህራን የሚሰጠው ጥቅም በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ የቋንቋ አስተማሪዎች የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ዘዴዎችን ወይም ስልቶችን ተጠቅመው ተማሪዎችን የማስተማሪያ ዘዴው ጠንካራና ደካማ ጎኖች፣ ስለ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርቱ ሁኔታ ተገቢ የሆነ ውሳኔ መስጠት ይችላሉ (Shabaan 2001፡17)::

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ተከታታይ ምዘና መምህራን በክፍል ውስጥ መተግበራቸው የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲያስተምሩ እንደሚያግዛቸው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ትምህርት ሚኒስተር ተከታታይ ምዘና በክፍል ውስጥ መተግበር እንዳለበት በፖሊሲ ቀርጾ እንደሚከተለው አስቀምጧል፡-

ትምህርት ሚኒስተር (2000) በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ትምህርት ቤቶች የተከታታይ ምዘናዎችን ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው በግልጽ ያስገነዝባል፡፡ በትምህርት ሚኒስተር የተነደፈውን የተከታታይ ምዘና ስልትም በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በስራ ላይ እያዋሉት ይገኛሉ፡፡

አማርኛ ቋንቋ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋና እንደ የትምህርት ዓይነት ከሚሰጥባቸው ክልሎች ውስጥ አንዱ የአማራ ክልል ነው፡፡ በአማራ ክልል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ በትምህርት ዓይነትና የማስተማሪያ ቋንቋ (Instructional media) በመሆን ያገለግላል፡፡ ይሁን እንጂ በዋግኽምራ ብሔረሰብ ዞን ውስጥ ከሚገኙ ሰባት ወረዳዎች በአራቱም ወረዳዎች ማለትም በአበርገሌ፣ በሰቆጣ ዙሪያ (ግማሽ)፣ በዝቋላና በሰሜን ሰሃላ ወረዳዎች የሚገኙ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ኽምጣኛ (አገውኛ) ነው፡፡ በመሆኑም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እስከ 8ኛ ክፍል ሌሎች የትምህርት ዓይነቶች (ሕብረተሰብ ሳይንስ) በአማርኛ ቋንቋ ሳይሆን በኽምጣኛ (አገውኛ) ቋንቋ ይሰጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ አማርኛ ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ይሰጣል፡፡

በሌላ በኩል አማርኛ ቋንቋ በትግራይ ክልላዊ መንግስት ከ3ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ሆኖ ይሰጣል፡፡ እንዲሁም በኮሌጅ ደረጃ እንደ የጥናት መስክ ሆኖ በትምህርትነት እየተሰጠ ይገኛል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው ተከታታይ ምዘና በተመለከተ የልምድ ልውውጥ በሚካሂድበት ጊዜ ጉዳዩን አስመልክቶ መደበኛ ያልሆነ ውይይት በሚደርግበት ጊዜ፣ መምህራኑ ተከታታይ ምዘናን የሚተገብሩት የተለያዩ የቡድን ስራዎችንና ፈተናዎችን ብቻ እያከታተሉ በመስጠት ተማሪዎችን መመዘንና ለሰሩት ስራ ውጤት መስጠት እንደሆነ ሊገነዘብ ችሏል፡፡ በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ደግሞ አጥኚው ከዚህ በፊት ስለተከታታይ ምዘና አተገባበር ከሚያውቀው ጋር የሚቃረን ሁኗል ብሎ ይገምታል፡፡ ስለዚህ አጥኚው ከላይ የተጠቀሱትን አነሳሽ ምክንያት መሰረት በማድረግ በአማራና በትግራይ ክልላዊ መንግስታት 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ጥናት ተደርጓል፡፡ ማለትም ሁለት ትምህርት ቤቶች ከአማራ ክልላዊ መንግስት (በማዕርነትና በሳቃ  ሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች) እንዲሁም በትግራይ ክልላዊ መንግስት (በፊናርዋና በየጭላ ሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች) የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የተከታታይ ምዘና አተገባበር በሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ንጽጽራዊ ጥናቱን አድርጓል፡፡

1. በማዕርነት፣ በሳቃ በፊናርዋና በየጭላ ሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ተከታታይ ምዘና ምንነትና ዓላማ ያላቸው ግንዛቤ ምንድን ነው?
2. በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና ዕቅድ ምን ይመስላል?
3. በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን የሚጠቀሙዋቸውን የመመዘኛ ስልቶች ምን ምን ናቸው?
4. በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከታታይ ምዘናዎችን ሲተገብሩ የሚያጋጥሙዋቸውን ችግሮች ምን ምን ናቸው? መፍትሔ ያቸውስ?

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማራ ክልላዊ መንግስት (በማዕርነትና በሳቃ) እንዲሁም በትግራይ ክልላዊ መንግስት (በፊናርዋና በየጭላ) አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ምን እንደሚመስል ንጽጽራዊ በሆነ መልኩ መፈተሽ ነው፡፡ ዝርዝር ዓላማዎቹ ደግሞ፡-

1. በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ምንነትና ዓላማ ያላቸውን ግንዛቤ መፈተሽ፣
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን የሚጠቀሙዋቸውን ስልቶች መፈተሽ፣
3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከታታይ ምዘናዎችን ሲተገብሩ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ካሉ መለየት፣
4. በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታ መፈተሽ፣
5. እነዚህ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና የዕቅድና የተግባር ተሰማሚነት መፈተሽ ነው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

ሀ. በጥናቱ ውስጥ ተተኳሪ ለሆኑት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበራቸው እስከምን ደረጃ እንደሆነ የሚመለክት መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ለ. የተከታታይ ምዘና አተገባበር እውን ለማድረግ በሚደረገው ጥረት የቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና ስልትና አቅጣጫ ምን መሆን እንዳለበትና ተማሪዎቻቸውን እንዴት መመዘን እንዳለባቸው አቅጣጫ ሊያሳይ ይችላል፡፡

ሐ. ከዚህ ርእስ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ጥናት ማካሄድ ለሚፈልጉ አጥኝዎች እንደመነሻና እንደማጣቀሻ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

መ. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አሰጣጥን ለማሻሻል አስተዋፅኦ

ሊያደርግ ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአማራ ክልላዊ መንግስት (በማዕርነትና በሳቃ)፣ በትግራይ ክልላዊ መንግስት (በፊናርዋና በየጭላ) አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍል ብቻ በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡

በመሆኑም በተጠቀሱት አራት ትምህርት ቤቶች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸው ግንዛቤ ምን እንደሚመስል፣ በተከታታይ ምዘና ሂደት ምን ምን የመመዘኛ ስልቶችን እንደሚጠቀሙና በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ምን ምን ችግሮች እንደሚያጋጥሙዋቸው ንጽጽራዊ በሆነ መልኩ ዳሰሳ አድርጓል፡፡

ጥናቱ ከላይ በተጠቀሱት በአራቱም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የሚካሄደውን ሁሉንም የአማርኛ ቋንቋ አስተማሪዎች ለማየት ይሞክራል፡፡ ይሁን እንጂ በሁለቱም ክልሎች የሚማሩ ተማሪዎች የቋንቋ ብቃታቸው የተለያየ መሆኑ ቢገመትም የታላሚ ክፍል ተማሪዎች የቋንቋ ብቃታቸው አልተመለከተም::

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

ይህን ጥናት በሚዘጋጅበት ወቅት እጅግ በርካታ የሆኑ ችግሮችን አጋጥመዋል፡፡ የመጀመሪያው ችግር በተከታታይ ምዘና ዙሪያ የክለሳ ድርሳናት መረጃ አለማግኘት፣ በስራ ጫና ምክንያት በቂ የሆነ ጊዜ አለማግኘት፣ ሲሆኑ በዋናነት ደግሞ የመረጃ ሰጪዎች በወቅቱና በቦታው ያለመገኘት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የክለሳ ድርሳናት ችግር ለመፍታት በአቅራቢያ ከሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመሄድ የተለያዩ መጻሕፍት ሊያነብ ችሏል፡፡ በተጨማሪም በክረምት ሊጨመሩ የሚችሉ መረጃዎች ሊጠናከሩ ችሏል፡፡ መረጃ ሰጪዎች ለማግኘት ደግሞ በተደጋጋሚ በመሄድ መረጃ ሊሰበሰብ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ፅሑፍ ቅኝት

## 2.1 የተከታታይ ምዘና ምንነት

ተከታታይ ምዘና ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ከተለያዩ የምዘና ዘዴዎች አንዱና ተከታታይ ድርጊትን የሚጠይቅ መሆኑን ያመለክታል (ሙሀመድ 2002፣7)፡፡ ይህንን የምዘና ዓይነት ምሁራን በተለያዩ ስያሜዎች ሲጠሩት፣ የክትትል መዝገብ፣ ስርዓተ ትምህርት ተኮር ምዘና፣ ሂደታዊ ምዘና፣ ወዘተ. በመሳሰሉት ስያሜዎች ይጠራል (በድሩ 1994፣25)፡፡ ስለ ተከታታይ ምዘና የተለያዩ ምሁራን የሰጡት ማብራሪያ እንደሚከተለው በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

Curzon (1990፡135) ተከታታይ ምዘና ብዙ ድርጊቶችን የያዘ ሐረግ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ግን በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ በማተኮር የተማሪዎችን የዕውቀት፣ የክህሎትና የዝንባሌ ዝርዝር ባህሪያት መግለጫ በማደራጀት የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት የሚያጎለብትና የመማር ማስተማሩን ስራ ለማሻሻል የሚረዳ ነው ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም ታጠቁና ሌሎች (1995፣12) እንዳስረዱት ተከታታይ ምዘና እንደሂደታዊ ግምገማ (Formative Evaluation) የሚታይ ሆኖ ትኩረቱ ስርዓቱን በጠበቀ መንገድ ተማሪው በዕውቀት፣ በአስተሳሰብና በክህሎት ያገኘውን ለውጥ በየጊዜው ተከታትሎ ለማሳየት የሚረዳ የምዘና ስልት ነው፡፡

Dessalegn (2004፡2) እና Dessalegn and Girma (2009፡283) እንደሚገልጹት ደግሞ፣ ተከታታይ ምዘና በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ በልዩ ልዩ ተግባራት (በቤት ሥራ፣ በግል ሥራ፣ በፕሮጀክት ሥራ፣ በራስ ምዘና፣ ወዘተ.) ተማሪውን በማሳተፍ ብቁ የሆነ ክህሎት ይዞ እንዲያድግ ለማድረግ የሚረዳ ነው፡፡ ተከታታይ ምዘና የተማሪውን ብቻ ሳይሆን የመምህሩን የማስተማር ስልት፣ ዝግጅትና ዕውቀት ከሚገኘው ምጋቤ ምላሽ ለማሻሻል የሚያግዝ ነው ሲሉ አጠናክረውታል፡፡ ከዚህ ጋር በማያያዝም Aggrawal (1994፡364) እና ተካ (1998፣20) ተከታታይ ምዘና በፈተና ሊገኙ የማይችሉ ሌሎች ተፈላጊ የባህሪ ክህሎቶች አሉ፤ እነዚህ ደግሞ መታወቅና መገምገም ያለባቸው ለስብዕና መዳበር ጠቃሚ የሆኑ ክህሎቶች ናቸው፡፡ እነዚህን ባህርያት ለማስገኘት የሚረዳ ስልት ነው ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም ተስፋ (2000) ተከታታይ ምዘና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትኩረት እያገኘ የመጣ የምዘና ስርዓት ነው፡፡ ተከታታይ ምዘና የመማር ማስተማር ሂደት ዋና አካልና ተማሪዎችን በሂደት የመመዘኛ ስልት ሲሆን ዓላማውም ተማሪዎች በሚማሩበት ትምህርት ውጤታማ እንዲሆኑ ማገዝና የመማር ማስተማሩን ሂደት መሻሻል ነው፡፡

ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን አጠቃላይ ዕውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከት፣ የትምህርት አቀባበልና አካሄድ በመመዘን ተማሪዎችን ለማገዝ እንዲሁም በተማሪዎች፣ በመምህራንና በትምህርት ቤቱ ላይ ጠቃሚ ውሳኔ ለመስጠት መረጃ የሚሰብሰብበት የምዘና ስርዓት መሆኑን /AED/BESO II 2005፡ 3) እና (የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ 1997፣ 2) ይገልጻሉ፡፡

ከላይ የቀረቡትን የተከታታይ ምዘና ትርጓሜዎች የሚከተሉትን ማጠቃለያዎች መስጠት ይቻላል፡፡ ተከታታይ ምዘና የተለያዩ የምዘና መሳሪያዎችን በመጠቀም የተለያዩ የመማር ክፍሎችን የማሰብ ሂደትን ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ ባህሪያትንና ግለሰባዊ ገፅታዎችን ለመመዘን የሚያስችል የምዘና አቀራረብ ነው፡፡ በተመሳሳይ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት ለማሳደግ፣ የተማሪዎችን ጥንካሬና ድክመት ለመመዘን፣ ለተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍ ለመስጠት፣ መምህራንና ተማሪዎች ሥርዓተ ትምህርቱን ለመከለስ፣ እና ተማሪዎችን ለማነቃቃትና ለማበረታታት ይረዳል ብሎ ማጠቃለያ መስጠት ይቻላል፡፡

## 2.2 የምዘናና ግምገማ ዓይነቶች

እንደ ትግራይ ትምህርት ቢሮ (1999፣6-8) አገላለፅ የምዘናና ግምገማ ሂደቱ ከሚከናወንበት ጊዜና ከሚመዘነው ባህሪ አንፃር ምዘናና ግምገማ በአራት ይከፈላል። እነሱም፡-

ሀ. የቦታ ምደባ ምዘና **(Placement Evaluation)**

ይህ የምዘና ዓይነት የተማሪዎችን ቅድመ ባህሪና የመማር ዝግጅት ለመለካት የሚያገለግል ሲሆን ማስተማር ሂደቱ ከመከናወኑ ከመከናኑ በፊት የሚሰጥ የምዘና ዓይነት ነው። ተማሪዎችን አንድን የትምህርት ይዘት ከመማራቸው በፊትና ለአንድ የክፍል ደረጃና ትምህርታዊ ቦታ ምን ያህል ዝግጁ መሆናቸውንና በዚህ ትምህርታዊ ቦታ ለመመደብ የሚያስችል የምዘና ዓይነት ነው (ትግራይ ትምህርት ቢሮ፣ 1999) ።

ለ. ተከታታይ ምዘና **(Formative Evaluation)**

ተከታታይ ምዘና ማለት የመማር ማስተማሩ ሂደት እየተከናወነ ባለበት ጊዜ የተማሪዎችን የመማር ዕድገት ፣ ጠንካራና ደካማ ተማሪዎችን መለየትና የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል የሚያገለግል የምዘና ዓይነት ነው (ዝኒ ከማሁ)።

ሐ. ችግር መርማሪ ምዘና **(Diagnostic Assessment)**

ይህ የምዘና ዓይነት የመማር ማስተማሩ ሂደት እየተከናወነ ባለበት ጊዜ የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት የተማሪዎችን ደካማ ጎን ለማሻሻልና መፍትሄዎችን ለመስጠት የሚያስችል ነው (ትግራይ ትምህርት ቢሮ፣ 1999፣ 6)።

መ. የማጠቃለያ ምዘና **(Summative Assessment)**

የማጠቃለያ ምዘና አንድ የትምህርት ዓይነትና ኮርስ እንዲሁም የመማር ማስተማር ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የመማር ማስተማር መርሀ ግብሩ ውጤታማ መሆን አለመሆኑን ለመለካት፣ ከክፍል ክፍል ለመዘዋወርና ሰርቲፊኬት ለመስጠት የሚጠቅም የምዘና ዓይነት ነው (ዝኒ ከማሁ)።

እነዚህ አራት የምዘና ዓይነቶች የየራሳቸውን ተግባርና ዓላማ ያሏቸው በመሆናቸው በደንብ በመለየት መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ተማሪዎችን በተከታታይ ለመመዘን የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት የመማር ማስተማሩን ሂደት ማሻሻል እንደሚቻል መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 2.3 የተከታታይ ምዘና ባህሪያት

ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ውጤት ለማወቅ የሚረዳ ሳይሆን ተማሪው በመማር ማስተማሩ ምን እንዳገኘና የትምህርት አቀባበሉን በበለጠ እንዲያዳብር የሚያደርግ መሆኑ ተከታታይ ምዘናን ልዩ የሚያደርጉት አራት መሰረታዊ ባህሪያት እንዳሉት Alausa (1999፡7) እንዲሁም የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ (1997፣5) ይገልፃሉ፡፡ ባህሪያቱም የሚከተሉት ናቸው ይላሉ፡-

ሀ. ተከታታይ ምዘና ስርዓታዊ ነው፡፡

ለ. ተከታታይ ምዘና የተደጋጋሚ ጊዜ የምዘና ውጤት ነው፡፡

ሐ. ተከታታይ ምዘና ሁሉ አቀፍ ነው፡፡

መ. ተከታታይ ምዘና አቅጣጫ ጠቋሚ ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ሐሳቦች የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ (1997፣5) በዝርዝር እንደሚከተለው አቅርቧቸዋል፡፡

### 2.3.1 ተከታታይ ምዘና ስርዓታዊ ነው

ተከታታይ ምዘና ስርዓት ያለው ነው ሲባል ግልፅ በሆነ መንገድ እቅድ ያለው ሆኖ መምህራን የተማሪዎችን ችሎታ የሚገመግሙባቸውን የተከታታይ ምዘና መሳሪያዎች ማለትም ከአጫጭር የፅሁፍ ፈተናዎች፣ የቃል ፈተናዎች፣ የግልና የቡድን ሥራዎች፣ ቃለ መጠይቆችን ወዘተ የሚይዝ እንዲሁም ግምገማዎች የሚደረጎባቸውን ጊዜያት ስርዓትን ተከትለው ተከታታይነት ባለው መልኩ የሚቀርቡበት መሆኑ ነው፡፡ ለተከታታይ ምዘና ዕቅድ ይዘጋጃል፡፡ በዕቅዱ መሰረት ይተገበራል፡፡ ዕቅድ በሚዘጋጅበት ጊዜ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች ምዘናው የሚካሄድበት ስልት፣ ጊዜ፣ የሚተኮርባቸው የትምህርት ክፍሎች፣ የውጤት አያያዝ ወዘተ መሰረት አድርጎ ነው (አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ 2006)፡፡

### 2.3.2 ተከታታይ ምዘና የተደጋጋሚ ጊዜ የምዘና ውጤት ነው

በአንድ ተማሪ ላይ የተሟላና ተገቢውን የትምህርት ምስክርነት እና ውሳኔ ለመስጠት በአንድ ጊዜ የሚሰጥ የፈተና ግምገማ በቂ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ስለተማሪው ሁለንተናዊ የአዕምሮ፣ የሙያ ክህሎትና አመለካከት ዕድገት በቂ መረጃ ስለማይሰጥ ነው፡፡ በተከታታይ ምዘና አማካይነት የተሰበሰቡ መረጃዎች ተጠናቅረው መቅረብ አለባቸው፡፡ ይህ ካልተደረገ ስለተማሪዎቹ የተሟላ መረጃ ተይዟል ለማለት አይቻልም (ዝኒ ከማሁ) ፡፡

ተከታታይ ምዘና የተደጋጋሚ ጊዜ የምዘና ውጤት ነው ሲባል ተከታታይ ምዘና በባህሪው የተለያዩ የምዘና ስልቶችን ስለሚጠቀም ተማሪው በተለያዩ ጊዜያት የሚያሳያቸውን አጠቃላይ ባህርያት አጠቃሎ የሚያሳይ ማለት ነው (ተስፋ 2000፣10)፡፡

### 2.3.3 ተከታታይ ምዘና ሁሉን አቀፍ ነው

ተስፋ (2000) ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው በቂ ዕውቀት ቀስመው፣ ክህሎታቸውን አዳብረውና አመለካከታቸውን አስፍተው እንዲወጡ ይጠበቃል፡፡ ተማሪዎች ሊማሯቸው የሚገቧቸውን እነዚህን ባህርያት በትክክል ለመመዘን በተለያዩ ጊዜያት የሚሰጡ ፈተናዎችና መሳሪያዎች በቂ አይደሉም፣ በእርግጥ በፈተና ዕውቀትንና ክህሎትን መለካት ይቻል ይሆናል፡፡ አመለካከትንና የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ፣ ወዘተ ለመለካት ግን ያስቸግራል፡፡ ተከታታይ

ምዘና እንደ ተለምዶአዊው ፈተና በአዕምሮአዊ ክህሎት (Cognitive Skill) ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም፣ ሁለቱንም ማለትም እውቀትንና ክህሎትን እንዲሁም አመለካከትን (ስሜትን፣ ዝንባሌንና እምነትን) ለመመዘን ያስችላል (ዝኒ ከማሁ)፡፡

### 2.3.4 ተከታታይ ምዘና አቅጣጫ ጠቋሚ ነው

ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው ውጤት የተማሪዎችን የወደፊቱ አቅጣጫ ስለሚጠቁም በመማር ማስተማሩ ሂደት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ በትምህርታቸው ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት ለመርዳት የሚቻለው የተከታታይ ምዘና ውጤትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የተከታታይ ምዘና ዋነኛ አላማ ተማሪዎችን አልፈዋል ወይም ወድቀዋል ብሎ ውሳኔ ለመስጠት (ለመፍረድ) አይደለም፣ ተማሪዎችን ለመርዳት እንጂ፣ ተማሪዎችን ለመርዳት ደግሞ በተከታታይ ምዘና አማካይነት ስለተማሪዎች በቂ መረጃ መሰብሰብ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ አገላለፅ ተከታታይ ምዘና መምህራን የተማሪዎቻቸውን ችግሮች በሚገባ እንዲለዩና አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ የሚያግዝ ነው (ተስፋ 2000)፡፡

ስለዚህ የተከታታይ ምዘና ዋና ዋና ባህሪያት ከላይ የተለገጹት መሆናቸውን መረዳት ይችላል፡፡

## 2.4 የተከታታይ ምዘና ዓላማ

እንደ MoE (2003፡7) እና AED/BESO (2005፡10) መምህራን ተማሪዎቻቸውን እንዲመዝኑ የሚያደርጉዋቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ዓላማዎች መሰረት በማድረግ እንደሆነ ይገልፃሉ፡-

ሀ. የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ ለማሻሻል፡- ይህ ማለት የምዘና ውጤቶች ተማሪው እንዴት እየተማረ እንዳለ እና አስተማሪው እንዴት እያስተማረ እንዳለ ምጋቤ ምላሽ ስለሚሰጡ ከምጋቤ ምላሽ የተገኘውን መረጃ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ያግዛል፡፡

1) ተማሪዎች የትኛውን ይዘት የበለጠ መማር እንዳለባቸው ለመወሰን፡፡
2) ስለተማሪዎች የትምህርት ሁኔታ ለወላጆች፣ ለትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ለሚመለከታቸው ክፍሎች አስተማማኝ የሆነ መረጃ ለመስጠት፡፡

3) ተማሪዎች በየትኞቹ የትምህርት ዓይነቶች ጠንካራ እንደሆኑ፣ በየትኞቹ የትምህርት ዓይነቶች ደግሞ ድክመት እንዳሳዩ ለመለየትና ድክመት ባሳዩበት ትምህርት ላይ የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመቀየስ፡፡

በአጠቃላይ የተከታታይ ምዘና ዋና ዓላማ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሁኔታዎችን ለማሻሻልና ተማሪዎችን በሚማሩት ትምህርት ዙሪያ ውጤታማ ማድረግ ነው፡፡

## 2.5 የተከታታይ ምዘና አተገባበር

ተከታታይ ምዘና በተማሪዎች ላይ ስለሚታዩ ባህርያትና ስለአጠቃላይ የመማሪያ ክፍል ሁኔታን አስመልክቶ ተከተታይነት ባለው ሂደት መረጃ የሚሰበሰብበት ሂደት አድርጎ መውሰድ ይቻላል፡፡ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመማደራጀትና በመተንተን መምህራን ተማሪዎቻቸውን እንዲያውቁ፣ ዕቅዳቸው እንዲያቅዱ፣ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለመቆጣጠር፣ ምቹና ጤናማ የመማሪያ ክፍሎች ሁኔታ እንዲፈጥሩ ይረዳቸዋል (Capper 1996 Nitko 1996 እና Airasian 1997)፡፡ በተመሳሳይ ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ምን ያህል ውጤታማ እንዲሆኑ፣ መምህራን ደግሞ የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል ምን ያህል እንደሰሩና ተማሪዎች የራሳቸውን መማር ምን ያህል እንዳሻሻሉ ተደጋጋሚ ምዘና የሚደረግበት ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ተፈላጊውን የመማር ውጤት ምን ያህል እንዳሳኩ ለማረጋገጥ፣ ተማሪዎች ምን መሻሻል ምን እንዳሳዩ ለማረጋገጥ፣ በመማር ማስተማር ሂደት ያጋጠሟቸውን ለመለየት፣ የመማር ማስተማር ሥነዘዴዎች ውጤታማነት ለማረጋገጥ እና በመማር ማስተማር ሂደት ላጋጠሙ ችግሮችና እጥረቶች የተወሰዱ ርምጃዎችን ለማረጋገጥ የሚረዱ መረጃዎች የመሰብሰቢያ ሂደት ነው፡፡

የተከታታይ ምዘና ዓይነቶች የሆኑት ሂደታዊና አጠቃላይ ተከታታይ ምዘናዎች በተማሪዎች የመማር ሂደት ውስጥ እንደመማር ማስተማር ሂደት እና እንደመረጃ መሰብሰቢያ ሂደት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ሚና ይጫወታሉ፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ጥቅሞች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

※ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና መምህራን ከተማሪዎች ወይም ተማሪዎች ከተማሪዎች በጋራ እና ተማሪዎች በተናጠል ለብቻቸው የሚያከናውኗቸውን እንዲለዩ ይረዳቸዋል፡፡

※ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና አሳታፊ የመማር ማስተማር ሥነዘዴ፣ ተማሪዎችን በተግባራዊ የሥራ እንቅስቃሴ እንዲገቡ እና ተማሪዎች በመማር ማስተማር ግቦች

ላይ እንዲያተኩሩ ያበረታታል፡፡

※ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና የአቻ ለአቻ እና ግለ ግምገማ ማካሄድ ተማሪዎች የማህበራዊ ዕድገት ዕውቀታቸው እንዲገነቡ ይረዳቸዋል፡፡

※ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በተገቢ ነጥቦች ላይ ግብረ-መልስ የመቀበልና የተሰጣቸውን ግብረ-መልስ ተጠቅመው በቀጣይ የተሻለ እንዲሰሩ ይረዳቸዋል፡፡

ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና የሚከተሉትን ቁልፍ ሀሳቦች ያካትታል፡፡

1. ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ቀለበት ወይም እሽክርክሪት (loop) ነው፡፡ ተማሪዎችና መምህራን ትኩረታቸውን ዝርዝር ዓላማው ላይ ያደርጋሉ፤ የተማሪዎችን ሥራ ከዝርዝር ዓላማ አንፃር ይገመግማሉ፤ ተማሪዎች ያከናወኗቸውን ተግባራት ከዝርዝር የትምህርት ዓላማው ጋር እንዲቀራረብ ይሰራሉ፡፡
2. ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ለትምህርት ከሚሰጣቸው ጥቅሞች የሚከተሉት ይካተታሉ፡፡ ተማሪዎች ለማሻሻል የሚጠቅማቸውን መረጃ ከሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ያገኛሉ፡፡ ተማሪዎች መማርን እንዴት እንደሚማሩ (learning how to learn) እንዲለማመዱ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና እገዛ ያደርግላቸዋል፡፡
3. ተማሪዎችን ከማነቃቃት አንፃር ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ለትምህርት ከሚሰጣቸው ጥቅሞች ውስጥ ተማሪዎች የራሳቸውን ትምህርት የመቆጣጠር ስሜትና እራሳቸውን የመምራት ብቃት እንዲያጎለብቱ ማስቻል የሚጠቀስ ነው፡፡
4. የተማሪዎችን መማር ለመደገፍ የትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች በሥርዓት ከተደራጁ የክፍል ና የቤት ሥራ፣ የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ግብረ-መልስና ራስን መመዘን እና መስፈርቶችን ላይ የተመሰረተ እርማት ማካሄድ (ማስተሳሰር) አለበት፡፡
5. መምህራን የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና መረጃን ከተማሪዎች ጋር በመነጋገር፣ ሥራ ሲሰሩ በመመልከትና የሥራቸውን ውጤት ያገኛሉ፡፡
6. ተማሪዎች የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና መረጃን የሚያገኙት በግብረ-መልስ መልክ ነው (አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ 2006)፡፡

## 2.6 የተከታታይ ምዘና የሂደት ደረጃዎች

ዳንኤል (1999፣7) እና አልማዝ (2003) ተከታታይ ምዘና በሦስት ደረጃዎች ተከፋፍሎ ሊካሄድ እንደሚገባ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡-

### 2.6.1 ከማስተማር በፊት

በዚህ ደረጃ ተከታታይ ምዘና የሚደረግበት ዋና ዓላማ፡-

ሀ. ተማሪዎች በሂደት ስለሚማሩት ምዕራፍ፣ ዋና ርዕስና ንዑስ ርዕሶች ያላቸውን ቅድመ ግንዛቤና ልምድ በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ፣

ለ. ተማሪዎች ስለሚማሩት ይዘት የተዛባ (የተሳሳተ) ፅንሰ ሐሳብ ካላቸው መረጃ ለመሰብሰብ፣

ሐ. በመጨረሻም የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ ይመጥናሉ የሚባሉት ተግባራትንና መልመጃዎች በላይ እቅድ ለማቀድ፣ ወዘተ ናቸው (ዳንኤል 1999፣7)፡፡

### 2.6.2 በመማር ማስተማር ሂደት

በዚህ ደረጃ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና የሚተገበርበት ዋና ዓላማ፡-

ሀ. ለተማሪዎች የሚማሩት ትምህርት ምን ያህል እየተከታተሉ ናቸው? ምን ያህል እየተረዱ ናቸው? ከተማሩት ውስጥ ምን ያህሉን ተገንዝበዋል? ምን ዓይነት ችግር አጋጥመዋቸው? ወዘተ በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ መረጃ ለመሰብሰብ፣

ለ. በደንብ እየተከታተሉ ያሉትን ለማበረታታት፣

ሐ. የመማር ችግር ያጋጠማቸውን እንደ ችግራቸው መጠን የተለያዩ ድጋፎችን ለመስጠት፣

መ. በማስተማር ሂደቱ ላይ መሻሻል በሚገባቸው ነጥቦች ዙሪያ ማስተካከያ ለማድረግ፣ ከትምህርት ዕቅድ ጀምሮ እስከ ድጋሚ ማስተማር ሊያጠቃልል ይችላል(ዝኒ ከማሁ)፡፡

### 2.6.3 ከማስተማር በኋላ

በዚህ ደረጃ ተከታታይ ምዘና የሚካሄድበት ዋና ዓላማ፡-

ሀ. በየምዕራፉ የተከተቱትን የትምህርት ዓላማዎች መሠረት ባደረገ መልኩ ተማሪዎች ምን ያህል የባህርይ ለውጥ አምጥተዋል? በሚሉ ጥያቄዎች ዙሪያ መረጃ ለመሰብሰብ፡፡

ለ. በተሰበሰበው መረጃ መሰረት አንድ ተማሪ አልፏል ወይስ ከሚጠበቀው በታች አምጥቷል? ብሎ ለመወሰንና ውጤት ለመስጠት እንዲሁም ከተፈለገው በታች ያመጡትን ተማሪዎች በድጋሚ ለማዘጋጀት ይውላል (አልማዝ 2003)፡፡

## 2.7 የአጠቃላይና የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ዘዴዎች

### 2.7.1 የአጠቃላይ ተከታታይ ምዘና ዘዴዎች

መምህራን ሊጠቀሙባቸው ከሚችሉ የአጠቃላይ ተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ውስጥ የተወሰኑትን ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

1. በሥርዓተ ትምህርት ማቴሪያሉ ላይ የተመሠረቱና የተካተቱ ሙከራዎች፣
2. ከትምህርቱ ዓላማዎች ጋር የተዛመዱ በመምህራን የተዘጋጁ ሙከራዎች፣
3. ከትምህርቱ ዓላማዎች ጋር የተዛመዱ በሥርዓት የታረሙ ፕሮጀክቶች፣
4. በተማሪ የተሰሩ የተግባር ውጤትና ተማሪዎች ተግባሩን ሲያከናውኑ የሚደረግ ምዘና፣
5. ከትምህርቱ ዓላማዎች ጋር የተዛመዱ በሴሚስተሩ ወይም በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚከናወን ምዘና (አማራ ትምህርት ቢሮ 2006)፡፡

### 2.7.2 የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ዘዴዎች

መምህራን ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና በመተግበር ሰፋ ያለ መረጃ ይሰበስባሉ፡፡ ይህም የመማር ማስተማሩን ሂደት ከተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ጋር እንዲጣጣሙ ያግዛቸዋል፡፡ መምህራን የምዘናውን ተግባራት ሲቀርፁ በተማሪዎች ሂደት የሚገኘውን ግንዛቤ ለሚቀጥለው ደረጃ ምልከታ፣ ወርክሺት፣ በክፍል ውስጥ የሚጠየቁ ጥያቄዎች፣ የመምህር-ተማሪ ጉባኤና ሌሎች ማቀድንና መማር ማስተማርን ዘዴዎች ውስጥ የሚጠበቅን መረጃ ሠጪ ዘዴን እንዲያዘጋጁ ይረዳቸዋል (አማራ ትምህርት ቢሮ 2006)፡፡

በተጨማሪም MoE (2004:29) ተከታታይ ምዘና የመማር ማስተማሩን ሂደት በተገቢው መንገድ ለመምራት የሚያግዝ ዘዴ እንጂ፣ ተማሪዎችን በደረጃ አስቀምጦ ከክፍል ወደ ክፍል ለማሸጋገር የሚያገለግል መሳሪያ ብቻ አይደለም፡፡ ዘዴዎቹ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ተጠቃልለው ቀርበዋል፡፡

### ሰንጠረዥ 1 ፡- የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች

| የምዘና ዘዴ | የአሠራር ቅድም ተከተል | ዓላማ |
|---|---|---|
| የተማሪዎችን ማዳመጥና ምልከታ ማካሄድ | ተማሪዎች በማንበብ እያሉ፣ ከሌሎች ጋር በትብብር በሚሠሩበት ወቅት፣ የተሠጡትን ሥራ በሚሠሩበት ወቅት | ተማሪዎች የሠሯቸውን ስህተቶችና ያሉባቸውን የግንዛቤ ችግር ለመለየት |
| ተማሪዎችን ማነጋገር | ተማሪዎች እየሠሩት ያለውን ሥራ ለምን እንደሚሠሩት እና እንዴት እየሠሩት እንደሆነ ሂደቱን እንዲናገሩ በመጠየቅ | ጽንሰ-ሀሳቦችን እንዴት እየተረዷቸውና እንዴት ችግሮችን ለመፍታት እንዴት እያሰቡ እንደሆነ ለመወሰን |
| ተማሪዎች የሚሰጡትን ምላሽ ማዳመጥ | የመማር ማስተማር ሂደት በመካሄድ ላይ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ምላሻቸውን በማዳመጥ | ለጥያቄዎች በተደጋጋሚ ምላሽ እንዴት እየሠጡ እንደሆነ በማወዳደር ምን ያህል ግንዛቤያቸው ለመወሰን |
| ኢ-መደበኛ የቃልና የፅሑፍ አጫጭር ፈተናዎች(quizzes) | ኢ-መደበኛ የቃልና የፅሑፍ አጣጥር ፈተናዎች(quizzes) በመስጠት | ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት በደንብ የተረዱትንና ያልተረዱትን በመለየት ድጋፍ ለማድረግ |
| የመጀመሪያ ረቂቅ የሥራ ውጤቶች፣ ፕሮጀክቶችንና የተግባር ሥራዎችን በመከለስ | የመጀመሪያ ረቂቅ የሥራ ውጤቶች፣ ፕሮጀክቶችንና የተግባር ሥራዎችን በመከለስ | ተማሪዎች ተግባራትን በተገቢ በማከናወን ላይ መሆናቸውንና ሥራቸውን በአግባቡ ማጠናቀቅ እንዲችሉ ግብረ-መልስ ለመስጠት |

ምንጭ፡- አማራ ትምህርት ቢሮ (2006 ዓ.ም) ለርዕሰ መምህራንና ለሱፐርቫይዘሮች ስልጠና የተዘጋጀ ሞጁል (ያልታተመ)፡፡

ሰንጠረዥ 2 ፡- የሚከተለው ሠንጠረዥ መቼ እና እንዴት ሂደታዊ ተከታታይ ምዘናን መጠቀም እንደሚቻል ያሳያል፡፡

| የሚካሄድበት ጊዜ | የምዘና ተግባራት |
|---|---|
| ከመማር ማስተማር ሂደት በፊት | ዓላማ፡-ስለትምህርቱ ተማሪዎች ምን ያህል እንደሚያውቁ ለማወቅ |
| | ዘዴ፡-በመምህራን የሚመራ የክፍል ውስጥ ምልከታ በማካሄድ ማስታወሻ በመያዝ |
| መማር ማስታማር ሂደት በመካሄድ ላይ እያለ | ዓላማ፡-ተማሪዎች የተቀመጡትን የመማር ግቦች ምን ያህል እንዳሳኩ እና ያመጡትን መሻሻል ለመመዘን |
| | ዘዴ፡-የቃል ጥያቄ፣ የክፍል ሥራ፣ አጫጭር ፈተናዎች (Quizzes) |
| ከመማር ማስተማር ሂደት በኋላ | ዓላማ፡-ተማሪዎችምን ያህል እንደተማሩ ለመወሰን<br>-የምዘና ነጥብ ለመስጠት<br>-ለተማሪዎችና ለወላጆች ሪፖርት ለማቅረብ |
| | ዘዴ፡-የክፍል ሥራዎች፣ አሳይሜንቶች፣ ፕሮጀክቶች፣ ፈተናዎች |

**ምንጭ፡-** አማራ ትምህርት ቢሮ (2006 ዓ.ም) ለርዕሰ መምህራንና ለሱፐርቫይዘሮች ስልጠና የተዘጋጀ ሞጁል (ያልታተመ)፡፡

አብዛኛውን ጊዜ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎችን በተከታታይ ሁኔታ ለመመዘን የምንጠቀምባቸው የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ወይም ስልቶች የሚከተሉት መሆናቸውን (ተስፋ 2000፣27) ይገልፃሉ፡፡

## 2.7.2.1 የቃል ጥያቄ

ይህን የተከታታይ ምዘና ስልት አንድ መምህር በየትኛውም የመማር ማስተማር ሂደት ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ይህ ዓይነቱ ስልት ተማሪዎች የተማሩትን ምን ያህል እንደተገነዘቡትና ተማሪዎች የት ላይ ችግር እንዳለባቸው ለማወቅ ይጠቅማል፡፡

አብዛኛውን ጊዜ አንድ መምህር የዚህ ዓይነቱን የምዘና ስልት መደበኛ ባልሆነ በመማር ማስተማሩ ሂደት ከተማሪዎች ጋር ተራክቦ ለመፍጠርና ለመመዘን የሚያስችል ነው፡፡ በክፍል ውስጥ የቃል ጥያቄን እንደአንድ የምዘና ዘዴ የመጠቀም ዋና ዓላማ በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎችን ትኩረት ወደ ትምህርቱ ለመሳብ እንደሆነ (Elington Eari 1997፡ 4-15) ይገልፃሉ፡፡

ስለቃል ጥያቄ ከቀረበው ሀሳብ ማየት እንደተቻለው አንድ መምህር በተከታታይ በሚያስተምርበት ወቅት መጠቀም እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.7.2.2 ምልከታ

ምልከታ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰሩትንና የሚናገሩትን በጥሞና በዓይን በመከታተል የምንመዘግብበት ዘዴ መሆኑን Brooks (2002፡5) ይገልፃሉ፡፡ በምልከታ አማካይነት መረጃ ለማግኘት ከተፈለገ መምህራን የምልከታ ክሂል ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህም የምልከታ ክሂል ምን መመልከት እንደሚፈልጉ ማወቅን፣ በጥሞና ማዳመጥን፣ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው በሚያደርጓቸው ተራክቦዎች ላይ ማተኮርን፣ ጠቃሚ ነገሮችን በማስታወሻ መያዝን እና ደግሞ ደጋግሞ ማሰብን ይጠይቃል፡፡

እንደ Shabaan (2001፡19-25) ገለፃ ምልከታ አብዛኛውን ጊዜ መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው፡፡ ምልከታ የሚካሄደው በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ሲወያዩና የተለያዩ የክፍል ውስጥ ተግባራትን ሲያከናውኑ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ አስማተሪው እየተዘዋወረ በመመልከት እንዲሰሩ፣ የታዘዙትን ተግባራት በትክክል ማከናወናቸውንና በሂደትም ያጋጠሙዋቸውን ችግሮች መጠየቅና መረዳት አለበት፡፡

ስለዚህ ምልከታ የሚካሄደው በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ሲወያዩና የተለያዩ የክፍል ውስጥ ተግባራትን ሲያከናውኑ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 2.7.2.3 ቅድመ ፈተና

ለማስተማር በምናቅድበት ጊዜ ተማሪዎቻችን ስለምናስተምረው ርዕስ ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው ትምህርቱን ማስተማር ከመጀመራችን በፊት ማወቅ መቻል እንዳለብን ተስፋ (2000፣ 27) ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ስለርዕሱ ያላቸውን የቀደመ ግንዛቤ ለማወቅ ከተወሰነ ጊዜ ቀደም ብሎ ለተማሪዎች የቅድመ ግንዛቤ ፈተና መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ከቅድመ ግንዛቤ ፈተና የተገኘው ውጤት አስተማሪው ለወደፊት ለማስተማር የሚጠበቅበትን ትምህርት በአግባቡ እንዲያቅድና የተለያዩ የምዘና ተግባራትን በዕቅዱ ውስጥ እንዲያካትት ዕድል ይፈጥርለታል፡፡

#### 2.7.2.4 የቤት ሥራ

የቤት ሥራ ተማሪዎች የተማሩትን ይዘት በሚገባ እንዲለማመዱ የሚያግዝ የምዘና ስልት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቤት ሥራ አንድ አስተማሪ ተማሪዎቹን ምን ያህል ትምህርቱን እየተከታተሉ እንደሆነ የሚያረጋግጥበት ስልት ነው፡፡ የቤት ሥራ ከሂደታዊ የምዘና ስልቶች መካከል አንዱ ሲሆን ተማሪዎች የትኞቹን ርዕሶች ደግመው መማር እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው የእርምት ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የምዘና ስልት ነው፡፡

#### 2.7.2.5 ፈተና እና ሙከራ

ፈተና እና ሙከራ በቋንቋ ክፍል ውስጥ ተማሪዎችን ለመመዘን ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ በፈተና እና በሙከራ መካከል የተወሰነ ልዩነት እንዳለ Noam (2000) በመጥቀስ ተስፋ (2000፣29) ይገልፃሉ፡፡ አንድ መምህር ፈተና ለመፈተን በሚያስብበት ጊዜ ለተማሪዎቹ አስቀድሞ ይነግራቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፈተና የትኩረት አቅጣጫ በተወሰኑ ይዘቶች ላይ ነው፡፡ በሙከራ ጊዜ ግን መምህሩ ሙከራ ለተማሪዎች እንደሚሰጥ አይነግራቸውም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለተማሪዎች የሚሰጠው ሙከራ በንግግር ወይም በጽሁፍ መልክ ሊቀርብ ይችላል፡፡

ከትምህርቱ ዓላማ ጋር ግንኙነት ያላቸውና በጥንቃቄ የተዘጋጁ የቋንቋ ፈተናዎችና ሙከራዎች በተማሪዎቹ አዕምሮ ውስጥ አዎንታዊ አመለካከት እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡ በተገቢው ሁኔታ የተዘጋጁ ፈተናዎችና ሙከራዎች የተማሪዎችን በርትቶ የማጥናት ስሜት ይቀሰቅሳሉ፡፡ እንዲሁም በጥንቃቄ የተዘጋጁ ፈተናዎች ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ያለባቸውን ችግር እንዲለዩና በየትኞቹ ርዕሶች ላይ በርትተው መስራት እንደሚገባቸው አስፈላጊውን መረጃ እንደሚሰጡ (Race and et al. 2008: 82) ይገልፃሉ፡፡

በእያንዳንዱ ምዕራፍ ማጠቃለያ ላይ የሚሰጡት ፈተናዎች ለመምህራንና ለተማሪዎች የሚሰጡት መረጃ ጠቃሚ መሆኑን ተስፋ (2000፣27) ይገልፃሉ፡፡ ነገር ግን ፈተናዎች ተማሪዎች የመንፈቁን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ የሚሰጡ ከሆነ መምህሩ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ማስተካከል ስለሚገባው ነገር የሚሰጡት መረጃ የዘገየ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም መምህሩ ፈጥኖ ለተማሪዎች ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ ላይሰጥ ይችላል፡፡ ከዚህ ሀሳብ ጋር ተያያዥነት መልኩ Teshome (2001:28) የSalem (1989)

ስራዎችን በመጥቀስ በመንፈቅ ማጠቃለያ ላይ የሚሰጡትን ፈተናዎች ተማሪዎች ማሻሻል የሚገባቸውን በመጠቆም በኩል የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ የጎላ ነው፡፡ ምክንያቱም ፈተናዎች የሚሰጡት በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ስለሆነ ነው ይላሉ፡፡

ፈተናዎችና ሙከራዎች ተማሪዎች አንድ ምዕራፍ ከመጨረሳቸው በፊት የሚሰጡ ከሆነ ግን ለመምህራንና ለተማሪዎች ስለመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያስተላልፉት መረጃ በጣም ጠቃሚ እና ሂደቱን የሚያግዝ ይሆናል፡፡ በመሆኑም መምህራን ከፈተናዎችና ከሙከራዎች የተገኙትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ ተማሪዎች በየትኞቹ ርዕሶች ላይ ጥንካሬ እንዳሳዩ በየትኞቹ ርዕሶች ላይ ደግሞ ድክመት እንዳሳዩ መለየት ይችላሉ፡፡ መረጃዎችን መሰረት በማድረግም ተማሪዎች ድክመት ያሳዩባቸውን ርዕሶች እንደገና ሊከልሱላቸው ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ፈተናዎችና ሙከራዎች በተከታታይ ምዘና ሂደት የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማገዝና ስለተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ የተከታታይ ምዘና ስልቶች መሆናቸውን (Shabaan 2001፡19-25) ይገልፃሉ፡፡

## 2.7.2.6 ፕሮጀክት

ፕሮጀክት ተማሪዎች የተማሩትን ነገር ምን ያህል በተግባር ላይ እንደሚያውሉት ለማወቅ የሚካሄድ የምዘና ስልት መሆኑን Shabaan (2001፡19-25) ይገልፃሉ፡፡ የፕሮጀክት ሥራ በሚሰጥበት ጊዜ የእያንዳንዱን ተማሪ የፕሮጀክት ሥራ ይታረምና ውጤት ይሰጠዋል፤ ውጤቱም ይመዘገባል፡፡ በመሆኑም ፕሮጀክት በተከታታይ ምዘና ውስጥ አንድ ዘዴ ወይም ስልት ነው ማለት ይቻላል፡፡ የፕሮጀክት ሥራ ለተማሪዎች በሚሰጥበት ጊዜ በጥንቃቄ ማቀድና ማሰብን ይጠይቃል፡፡

በግልም ሆነ በቡድን የሚሰሩ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ትክክለኛ ጊዜ ተመድቦላቸው መከናወን እንደሚገባቸው Race et al. (2005፡89-92) ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በግልም ሆነ በቡድን አንድ ፕሮጀክት እንዲያከናውኑ ማድረጉ የተማሩትን ነገር ምን ያህል ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ለማወቅ እና ሀሳባቸውን በግልፅ እንዲያንፀባርቁ ለማድረግ እንደሚረዳቸው ይገልፃሉ፡፡

ምንም እንኳ የቡድን ሥራዎች ለማረም አስቸጋሪ ቢሆኑም፣ ለተማሪዎች የተለያዩ የቡድን ሥራዎችን መስጠት ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ከእነዚህም መካከል ተማሪዎች አንድን ርዕሰ ነገር ወይም ፍሬ ነገር በራሳቸው አስሰው እንዲያገኙ ያበረታታቸዋል፡፡

የተማሪዎችን ተነሳሽነት ያበረታታሉ፡፡ ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን የተለያዩ ችግሮች በራሳቸው እንዲፈቱ ያደርጋል፡፡ የተማሪዎችን የእርስ በርስ ትብብር ከፍ ያደርጋል፡፡

ይሁን እንጂ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ለተማሪዎች መስጠት የራሱ የሆኑ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ሁሉ ደካማ ጎኖችም አሉት፡፡ የተለያዩ የቡድን እና የግል ፕሮጀክቶችን ለተማሪዎች ለመስጠትና ለማቀድ ብዙ ጊዜ ይወስዳል፣ ተማሪዎች በግልም ሆነ በቡድን ያከናወኗቸውን ተግባራት አርሞ አስፈላጊውን ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ይወስዳል፣ ተማሪዎች በመካከላቸው የሀሳብ መሰራረቅ እንዳይኖር ስለሚፈሩ እርስ በርሳቸው እንዳይረዳዱና እንዳይተባበሩ ያደርጋል (ተስፋ 2000)፡፡

በአጠቃላይ ውጤታማ የቡድንና የግል ሥራ ወይም ፕሮጀክት በሚከተሉት ነገሮች ላይ ይመሰረታል፡፡ ግልፅ የሆኑ ተግባራትን በመስጠት፣ ግልፅ የሆኑ የመመዘኛ መስፈርቶችን በማውጣት፣ ፍትሀዊ (Fair) ውጤት በመስጠት፣ ከትምህርቱ ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተግባራትን በመቅረፅ፣

በመሆኑም ውጤታማ የቡድን ሥራ (ፕሮጀክት) ለማካሄድ ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ሁሉ ቢሟሉ ተማሪዎች በሚሰሩት ሥራ እርካታ ያገኛሉ፡፡

## 2.7.2.7 የመምህር ተማሪ ውይይት

የመማር ማስተማሩን ሥራ በተመለከተ በመምህርና በተማሪ መካከል የሚካሄድ ውይይት አንድ የምዘና ዘዴ (ስልት) ነው፡፡ በተማሪዎችና በመምህራን መካከል የሚካሄድ ውይይት ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ምን ያህል መሻሻል እንዳሳዩ ለመምህሩ ጥሩ የሆነ አዕምሮአዊ ምስል ከመስጠቱም በላይ በውይይቱ ጊዜ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው (Shabaan 2001፡20) ይገልፃሉ፡፡

በመሆኑም በመምህርና በተማሪ መካከል የሚካሄድ ውይይትና ቃለ መጠይቅ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች ያሳዩትን መሻሻል ኢ-መደበኛ መልኩ የምንመዝንበት ስልት ነው፡፡ በመምህር በተማሪ መካከል የሚካሄድ ውይይት አንድ ተማሪ በትምህርቱ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነና ፍላጎቱ ምን እንደሆነ ለመመዘን ያስችላል፡፡

### 2.7.2.8 ሰነደ ትምህርት

ሰነደ ትምህርት በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎችን ለመመዘን ከምንጠቀምባቸው ዘዴዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ሰነደ ትምህርት ማለት ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት ያከናወኗቸው ሥራዎች ስብስብ ወይም ክምችት ሲሆን ተማሪው በሚማረው የቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ምን መሻሻሎችን እንዳሳዩ ለመምህሩ አዕምሮአዊ ስዕል የሚሰጥ የምዘና ስልት መሆኑን (Elington and Earl 1997፡7) ይገልፃሉ፡፡

ምንም እንኳን ሰነደ ትምህርት በተከታታይ ምዘና ሂደት እንደ አንድ የምዘና ስልት መጠቀሙ የተማሪዎችን የቋንቋ ትምህርት ችሎታ በማዳበር በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ቢኖረውም፣ የራሱ የሆኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዳሉት ግን ሳይጠቀስ መታለፍ እንደሌለበት (Elington and Earl 1997፡8) ይገልፃሉ፡፡

ሰነደ ትምህርት ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት እየሰሩ ያስቀመጧቸው የተለያዩ ሥራዎች ክምችት በመሆኑ ተማሪዎች ያዳበሯቸውን ክሂሎች በተመለከተ በስፋው መረጃ ይሰጣል፡፡ ሰነደ ትምህርት የተማሪዎች የቀደመ ዕውቀት ምን እንደነበርና አሁን ደግሞ በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለማወቅ ይጠቅማል፡፡ ሰነደ ትምህርት የተማሪዎችን ዕውቀትና ክሂል ምን እንደሆነ አጉልቶ ስለሚያንፀባርቅ ለአስተማሪው ጥሩ መረጃ ይሰጣል፡፡ ሰነደ ትምህርት ተማሪው ረዘም ላለ ጊዜ ያሳየውን ግለሰባዊ ዕድገት ስለሚያንፀባርቅ ከሌሎች የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ይልቅ ስለተማሪው ሁለንተናዊ ባህሪ አስተማማኝ መረጃ ይሰጣል፡፡

ይሁን እንጂ ሰነደ ትምህርት ምዘና ከላይ የቀረቡትን ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትም እንደ Elington and Earl (1997፡8) የሚከተሉትን ደካማ ጎኖች አሉት፡፡

የእያንዳንዱን ተማሪ ሰነደ ትምህርት አንብቦ ለተማሪዎች ገንቢ አስተያየት ለመስጠት ጊዜ ይሰዳል፡፡ የሰነደ ትምህርት ሥራዎች በውስጣቸው የተለያዩ ተግባራትን ስለሚይዙ እያንዳንዱን መስፈርት ተግባር አውጥቶ ለመመዘን ይከብዳል፡፡

ሰነደ ትምህርት የራሱ የሆኑ ጠንካራና ደካማ እንዳላቸው አውቀው መምህራን በተገቢ ሁኔታ እንደአንድ የምዘና ዓይነት ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

### 2.7.2.9 የራስ ምዘና

ከምዘና ሂደት ውስጥ አንዱ ዘዴ የራስ ምዘና ነው፡፡ የራስ ምዘና ማለት ተማሪዎች የራሳቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን በራሳቸው የሚገመግሙበት ስልት ነው፡፡ እንደ Puhi (1997፡10) ገለፃ ተማሪዎች በተወሰነ ትምህርት ላይ ትኩረት ሰጥተው ከሰሩ በኋላ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ራሳቸውን ይመዝናሉ፡፡ ይህ ምዘናም ያሳዩትን መሻሻል እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል፡፡ የራስ ምዘና ማለት ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው የሚመዝኑበት ሂደት ነው፡፡ እንደ Puhi (1997፡10) ገለፃ ተማሪዎች የራሳቸውን የትምህርት ሂደት በራሳቸው ሊመዝኑ የሚችሉት አስፈላጊ ሁኔታዎች ከተሟሉላቸው ነው፡፡ ከነዚህም አስፈላጊ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው እስከአሁን ደህና አድርጌ የሰራሁት ምንድን ነው? በሚቀጥለው ማሻሻል ያለብኝ ምንድን ነው? ጠንካራና ደካማ ጎኔ የት ላይ ነው? ብሎ ለመመዘን መስፈርቶች ያስፈልጋቸዋል፡፡

እንደ Hamis (1997፡10) ገለጻ የራስ ምዘና ተማሪዎች በራስ የመተማመን ችሎታቸው እንዲያጎለብቱና ግልፅነትን እንዲላበሱ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ደካማና ጠንከራ ጎናቸውን ለይተው በማውጣት ለድክመቶቻቸው ማስተካከያ የሚሆን መንገድ እንዲቀይሱና ችግሮቻቸውን ለመቅረፍ የሚያስችሉ እርምጃዎች እንዲወስዱ ያስችላቸዋል፡፡ ራስን መመዘን ተማሪዎች ለትምህርታቸው ከፍተኛ ሀላፊነት እንዲሰማቸው ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ከማጎልበቱም በላይ ተማሪዎች ስለራሳቸው ትክክለኛ እና አስተማማኝ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ እንደ Puhi (1997፡ 7) ገለፃ፣ በተከታታይ ምዘና ወቅት የራስ ምዘናን መጠቀም ተማሪው የቋንቋ ችሎታውን የበለጠ እንዲያዳብር ብስለት የተሞላበት የማሰብ ችሎታ እንዲያጎለብት ያደርገዋል፡፡

የራስ ምዘና ስልት በተማሪዎች በኩል ተቀባይነት እንዲያገኝ ጠቃሚነቱም የጎላ እንዲሆን መምህራን የራስ ምዘናን በአግባቡ ሊያዘጋጁት እና ሊተገብሩት ይገባል፡፡ በመሆኑም መምህራን ስለራስ ምዘና ዓላማ፣ ጠቀሜታና መስፈርቶች ተማሪዎቻቸውን በአግባቡ ማሳወቅ አለባቸው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በራሳቸው የመመዘን ችሎታ እንዲያዳብሩ ለማድረግ የራስ ምዘና በክፍል ውስጥ በሚካሄዱ ዕለታዊ የመማር ማስተማር ክንውኖች መካተት አለበት፡፡

## 2.7.2.10 የጓደኛ ለጓደኛ (የቢ.ጤ) ምዘና

በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎችን ለመመዘን ከምጠቀምባቸው የምዘና ስልቶች አንዱ የቢ.ጤ (የጓደኛ ለጓደኛ) ምዘና ነው፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ከቢ.ጤዎቻቸው (ከጓደኞቻቸው) ጋር በመሆን ሥራዎቻቸውን እርስ በርሳቸው የሚመዘኑበት ጠቃሚ የሆኑ የማሻሻያ ሀሳቦችን ከጓደኞቻቸው የሚቀስሙበት የምዘና ስልት የቢ.ጤ ምዘና እንደሚባል Puhi (1997፡ 4) ይገልፃሉ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ብያኔዎች መገንዘብ እንደሚቻለው፣ የቢ.ጤ ወይም የጓደኛ ለጓደኛ ምዘና ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የሚያካሂዱት የምዘና ስልት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን የእርስ በርስ መስተጋብር ከፍ በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

የቢ.ጤ ምዘና ለተማሪዎች ስለሚሰጠው ጥቅም Puhi (1997፡7-8) የሚከተሉትን ነገሮች አቅርቧል፡፡ በቢ.ጤ ምዘና ዓውድ ውስጥ ተማሪዎች በሚሳተፉበት ጊዜ ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የተለያዩ የምዘና መስፈርቶችን እንዲያወጡ ያስችላቸዋል፡፡ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ምጋቤ ምላሽ እንዲሰጣጡ ያስችላቸዋል፡፡ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲያንፀባርቁ ያስችላቸዋል፡፡ ተማሪዎች እንዲነቃቁ ያደርጋቸዋል፡፡ ተማሪዎች ነገሮችን ከተለያየ አቅጣጫ የማየትና አመዛዝኖ የማሰብ ችሎታን ያጎለብትላቸዋል፡፡ አስተማሪዎች የተማሪዎቻቸውን ሥራ በማረም የሚያጠፉትን ጊዜ ይቀንስላቸዋል፡፡

ምንም እንኳን የቢ.ጤ ምዘና ከላይ የተጠቀሱት ጠቀሜታዎችና ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትም ደካማ ጎኖች ደግሞ አሉት፡፡ ተማሪዎች እርስበርስ የመተራረም ችሎታ ላይኖራቸው ይችላል፡፡ በጓደኛሞች መካከል በጣም የመቀራረብ ሁኔታ ስለሚኖር ተማሪዎች በትክክል የጓደኞቻቸውን ሥራዎች ላይመዝኑ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች ጓደኞቻቸው የሚሰጧቸውን አስተያየት አምነው ላይቀበሉት ይችላሉ፡፡

ስለሆነም ምንም እንኳን የቢ.ጤ ወይም የጓደኛ ለጓደኛ ምዘናን መጠቀሙ ከላይ የተገለፁት ደካማ ጎኖች ቢኖሩትም፤ መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት ምዘናን አዘውትረው መጠቀም አለባቸው፡፡ ይህንን ለማድረግ የቢ.ጤ ምዘናን ዓላማና ጥቅም ለተማሪዎቻቸው ግልፅ ማድረግ እንዳለባቸው ነው፡፡

### 2.7.2.11 እየወጡ ማቅረብ ምዘና

Shabaan (2001፡19) እንደሚገልፁት፣ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማወቅ ከምንጠቀምባቸው የምዘና ስልቶች መካከል አንዱ እየወጡ ማቅረብ ነው፡፡ እንደ ምሁሩ ገለፃ ከቋንቋ ትምህርቱ ጋር በተያያዘ መልኩ ተማሪዎች በተለያዩ ተግባራትን እየወጡ እንዲያቀርቡ በማድረግ መመዘን የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እየወጡ በሚያቀርቡበት ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታና አጠቃቀም መመዘን ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እየወጡ በሚያቀርቡበት ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን የሀሳብ አደረጃጀት መመዘን ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እየወጡ በሚያቀርቡበት ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን ፍላጎት መመዘን ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ መምህራን በቋንቋ ክፍል ውስጥ የተማሪዎችን የተለያዩ የክፍል ውስጥ ተግባራትን እየወጡ  እንዲያቀርቡ በማድረግ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ፣ ፍላጎት፣ የሀሳብ አደረጃጀት ችሎታ ወዘተ መመዘን ይችላሉ፡፡

## 2.8 ተከታታይ ምዘናን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ምክንያቶች

Puckett and Black (2008) Salivia Yacildayek (1998) በመጥቀስ ለምዘና ውሳኔ ለመስጠት ዓላማ የሚውል የግለሰቦችንና የቡድኖችን አጠቃላይ መረጃ የመሰብሰብ ሂደት ነው የሚል ትርጉም ከሰጡ በኋላ ምዘና ያስፈለገባቸውን ምክንያቶች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

※ የግለሰብን ፍላጎት፣ ጥንካሬና ውጤታማ ሥራ ለመስራት መነሳሳትን ለመወሰን፣

※ የግለሰብን የመማር ዕድገትንና መሻሻልን እና የአካዳሚክ ውጤታማነትንና ተግዳሮቶችን ለመወሰን፣

※ የተማሪዎችን መሻሻል፣ የመማርና የውጤታማነት ግቦችን ለማስቀመጥ ከተማሪዎች ጋር መረጃ ለመለዋወጥና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል መልካም ግንኙነት ለመፍጠር፣

※ የተማሪዎችን ግላዊ መሻሻልና ፍላጎት ለወላጆችና ለአሳዳጊዎች መረጃ ለመስጠት የሚያስችል የግንኙነት ሥርዓት ለመዘርጋት፣

※ የተማሪዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሥርዓተ ትምህርቱ ይዘቶችንና የመማር ማስተማር ሂደት ስልቶችን የተመለከቱ መረጃዎችን በመሰብሰብና በመተንተን አስፈላጊ ማስተካከያዎችን ለማድረግ ወዘተ ነው፡፡

ተከታታይ ምዘና ያስፈለገበት ዋና ምክንያት የትምህርት ዓላማዎችን (educational objctives) የአመለካከት ዓላማዎችን ጨምሮ የምዘና ቴክኒኮችንና የቡድን ሥራን በመጠቀም ለመመዘን እንዲቻል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተከታታይ ምዘና በትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማሻሻል ይረዳል፡፡

Nejabli (1987) ተከታታይ ምዘና ማካሄድ ያስፈለገበትን ዋና ምክንያት ፡-

አንድ ፈተና በመስጠት ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ወይም ችግር ለማጥፋት ወይም ለመቀነስ እንዲቻልና የተማሪዎችን ስኬታማነት በተመለከተ ትክክለኛ አመላካች ለማስቀመጥ ነው፡፡ ምክንያቱም ተከታታይ ምዘና በንቃት በመማር ማስተማር ሥራ የተሳተፈ ማንም ተማሪ ሊወድቅ አይገባም የሚል አስተሳሰብ ስለሚይዝ ነው በማለት ገልጿል፡፡

እንደ ምሁራኑ ገለጻ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ስኬታማነት ዕውቀትንና ክህሎትን መመዘንን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡ በተጨማሪም መምህራንና ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት ምን ባህርይ እንደነበራቸው በመከታተል አስተያየት መስጠት አለባቸው፡፡ የተከታታይ ምዘና የመደገፍ አስተሳሰብ የመነጨው ተከታታይ ምዘና መምህራን በተማሪዎች ሁለንተናዊ የምዘና ሂደት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በከፍተኛ ደረጃ እንዲሳተፉ የሚያደርግ በመሆኑና ስለተማሪዎች ሁለንተናዊ ችሎታና ውጤታማ የሥራ አፈፃፀም ትክክለኛ ምዘና ሊሰጥ በመቻሉ ነው፡፡ በመጨረሻም ተከታታይ ምዘና መምህራን በመማር ማስተማር ሂደት የራሳቸውን የማስተማር ሥነ-ዘዴ እንዲያሻሽሉ መሠረት የሚጥል መሆኑና መምህራን ፈተና የመስጠት ልምዳቸውን እንዲጨምሩ የሚረዳ በመሆኑ ነው፡፡

## 2.9. ብዙ ተማሪዎች ባሉበት የመማሪያ ክፍል የምዘና ዘዴዎች

ብዙ ተማሪዎች ባሉበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ የሂደታዊ የምዘና ዘዴዎች (formative methods) አሉ፡፡ የተወሰኑት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የቃል ጥያቄና መልስ ዘዴ፣ የጽሁፍ የክፍል መልመጃዎች፣ የቤት ሥራ መልመጃዎችና የፕሮጀክት ሥራ፣ የተሠሩ ሥራዎችን ማቅረብ (presentations)፣ አጫጭር ፈተናዎች (quizzes and tests)፣ የግልና የአቻ ለአቻ ግምገማ፣ ወዘተ፣ ናቸው (አማራ ትምህርት ቢሮ 2006)፡፡

ከምሁራን ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ብዙ ተማሪዎች ባሉበት መማሪያ ክፍል ውስጥም ተከታታይ ምዘና እንደአስፈላጊነቱ መተግበር እንደሚቻል መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 2.10 የግብረ-መልስ ምንነት

እንደ አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ (2006) አገላለፅ ግብረ-መልስ ለመሻሻል የሚጠቀምበት መረጃ ነው፡፡ ግብረ-መልስ መምህራን ተማሪዎች በመማር ሂደት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት፣ የሠሯቸውን ሥራዎች እና የሰጡትን መልስ በመመርመርና በመተንተን ያገኙትን ለተማሪዎች መልሰው የሚያሳውቁበት መንገድ ሲሆን መረጃውም ተማሪዎች አፈፃፀማቸውን ወይም ክንዋኔያቸውን እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡ ይልቁንም ጥሩ ግብረ - መልስ የተማሪዎችን ሥራ ገላጭ ነው፤ በክንዋኔና በዝርዝር ዓላማ ላይ የተወሰነ ነው፤ ተማሪው እንዴት እንደሚሻሻል የሚደረግለት ድጋፍ የያዘ ነው፡፡ ግብረ-መልስ ጥንካሬን፣ መሻሻልን የሚፈለገውንና የማሻሻያውን መንገድ (ዘዴ) የሚያሳይ ነው፡፡ ጥሩ ግብረ-መልስ ተማሪው የሚጠቀምበትን መረጃ የያዘ ነው፡፡ ይህ ማለት መጀመሪያ ተማሪዎች ግብረ-መልሱን ሊሰሙትና ሊረዱት የሚችሉት መሆን አለበት፡፡ ከግንዛቤቸውና ከአቅማቸው በላይ የሆነን ነገር አይሰሙም፡፡

በተመሳሳይ ማዳመጥ የማይፈልጉትን ነገር አይሰሙም ወይም ጠቃሚ አይደለም ብለው ካሰቡትም አያዳመጡትም፡፡ በጣም ጠቃሚ ግብረ-መልስ የተማሪዎችን የሥራ ጥራት ወይም ሥራው የሚሰራበት ሂደትና ስትራተጂዎች ላይ ያተኩራል፡፡ የተማሪው ትኩረት ወደ እራስን መምራት ስትራተጂ ወይም ችሎታዎች የሚስብ ግብረ-መልስ ጠቃሚ ነው፡፡ መምህራን ለተማሪዎች የሚሰጡት የግብረ-መልስ ዓይነት በመምህራን የማስተማር ሁኔታ ይወሰናል፡፡ ግብረ-መልስ ለመስጠት ዓላማ ሊኖር ይገባል፡፡ ግብረ-መልሱም ከተማሪዎችና ከመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴዎች/ዘይቤዎች ጋር መዛመድ ይኖርበታል (ዝኒ ከማሁ)፡፡

Nitko (2008) ሦስት ዓይነት የግብረ-መልስ አሰጣጥ እንዳሉ ይገልፃሉ፡፡ እነርሱም የማወዳደር (የማነፃፀር) ግብረ-መልስ፣ የውጤቶች ወይም የሂደቶች ግብረ-መልስ እና የገላጭ ወይም የግምገማ ግብረ-መልስ ናቸው፡፡

እነዚህ እንደሚከተለው በዝርዝር እንመተከታቸዋለን፡፡

### 2.10.1 የማወዳደር ግብረ-መልስ

ግብረ-መልስ በሚሰጥበት ወቅት ከሚተገበረው የንፅፅር ዓይነቶች አኳያ ይለያያል፡፡ ለተማሪዎች ንፅፅራዊ ግብረ-መልስ ለመስጠት ሦስት መሰረታዊ መንገዶች አሉት፡፡

1. በተማሪዎች የእርስ በርስ የችሎታ ንፅፅር ላይ የተመሰረተ ግብረ-መልስ (Norm-referenced feedback)፡- የተማሪው/ዋን ሥራ ተማሪዎች ሥራ ጋር ያነፃፅራል፡፡ ለምሳሌ የውሀ ውህድ ሥዕልህ/ሽ ከክፍሉ ተማሪዎች እጅግ በጣም ጥሩ ነው፡፡
2. በመስፈርት ላይ የተመሰረተ ግብረ-መልስ (Criterion-refrenced feedback)፡- የተማሪዎችን ሥራ ከዝርዝር ዓላማው ጋር በማነፃፀር ተማሪዎች ማድረግ ያለባቸውንና የሌለባቸውን ይነግራቸዋል፡፡ ለምሳሌ አንተ/አንቺ በባለአራት አሃዝ የማባዛት ችሎታህ/ሽ በጣም ጥሩ ነው፡፡
3. በራስ ላይ የተመሰረተ ግብረ-መልስ (Self-referenced feedback)፡- የተማሪው/ዋ ሥራ ከዚህ በፊት የተሰራ ሥራ ጋር ወይም በተወሰነ ጊዜ ከሚጠበቅ የአፈፃፀም ደረጃ ያነፃፅራል፡፡ ለምሳሌ ይህ ህይወት ያላቸው እና የሌላቸው ዝርዝር ከዚህ በፊት ከሠራኸው የተሻለ ነው፡፡

ጥሩ የሚባለው የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ግብረ-መልስ ተማሪዎች እየተማሩ የሚሰጥ በመስፈርት የተመሰረተው ግብረ-መልስ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ስለራሳቸው ችሎታ እርግጠኛ ላልሆኑና ለመማር በቂ ችሎታ የለንም ብለው ለሚያስቡ ተማሪዎች በራስ ላይ የተመሰረተ ግብረ-መልስ መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ምን ያህል እንደተሻሻሉ እንደሆኑ ለማሳየት ይችላሉ (አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ 2006)፡፡

### 2.10.2 የውጤቶች ወይም የሂደት ግብረ-መልስ

ግብረ-መልስ ከሚገልጸው የተማሪ ውጤቶች አንፃር ወይም ተማሪው/ዋ አንድ ሥራ ለመፈፀም ከተከተለው/ችው ዘዴ /መንገድ/ አንፃር ይለያያል፡፡ ማለትም የሚሰጠው ግብረ-መልስ የተማሪዎችን የሥራ ውጤት አሠራር ላይ ወይም ተማሪው ሥራውን ለመስራት የሄደበትን መንገድ /ዘዴ/ ላይ ሊመረኮዝ ይችላል፡፡ የውጤት ግብረ-መልሰ (outcome feedback) የመምህራን ግምገማ ተማሪው/ዋ ያገኘው/ችው ውጤት ላይ ብቻ በማተኮር ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡ ለአብነት በፕሮጀክት ሥራው 80% አግኝተሀል/ሻል፡፡ የዚህ ዓይነት ግብረ-መልስ አሠጣጥ የመምህሩ/ሯን ግምገማ በተማሪው/ዋ ሥራ ብቻ

የተመሰረተና የውጤቱን ማጠቃለያ ብቻ ለተማሪው/ዋ የሚነገረው፡፡ ግምገማው ከሚጠበቀው ውጤት አንፃር ምን ያህል እንደተማሩ፣ ምን ያህል እንዳሻሻሉ እና ምን እንደሚያሻሽሉ ለተማሪዎች አይገልፅም (Nitko 2008)፡፡

በሌላ በኩል በግንዛቤ ላይ ያተኮረ ግብረ-መልስ (Cognitive feedback) ተማሪው/ዋ ሥራውን ለመስራት በተከተለው መንገድ (ዘዴ) እና ያገኘው/ችው ውጤት መካከል ያለውን ግንኙነት ለተማሪው/ዋ ይገልጻል፡፡ በዚህም ሥራው የሚሻሻልበትን መንገድ ይመራል፡፡ የተሻለ ግብረ-መልስ የሚባለው የግንዛቤ ግብረ-መልስ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ለማሻሻል ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡ የውጤት ግብረ-መልስ በጣም ውሱን ነው፡፡ የውጤት ግብረ-መልስ ተማሪው/ዋ እንዲያሻሽል ወይም እንድታሻሽል የሚረዳው/ዳት ተማሪው/ዋ ለራሱ/ሷ የግንዛቤ ግብረ-መልስ መስጠት ከቻለ ብቻ ነው (ዝኒ ከማሁ)፡፡

### 2.10.3 ገላጭ ወይም ግምገማዊ ግብረ-መልስ

የዚህ ዓይነቱ ግብረ-መልስ አሠጣጥ ገላጭ (Explainatve) እና ግምገማዊ (Evaluative) ግብረ-መልሶችን ያካተተ ነው፡፡ በገለጭ ግብረ-መልስ ተማሪው/ዋ በሠራው/ችው ሥራ ላይ ሥራውን በተመለከተ ለተማሪው/ዋ መረጃ ይሠጣል፡፡ ለምሳሌ በድርሰትህ ውስጥ የድርጊት ገላጭ ቃሎች አጠቃቀምህን/ሽን ወድጄዋለሁ፡፡ ይህ ዓይነት ግብረ-መልስ አሰጣጥ ተማሪው/ዋ በሠራው/ችው ሥራ ያለውን መልካም ነገር በመግለፅ ተማሪው/ዋ ከተቀመጠው መስፈርት አኳያ ምን ያህል እንደሠራ/ች ያመለክታል፡፡

በግምገማዊ ግብረ-መልስ (Evaluative Feedback) ሥራውን በተመለከተ የመምህሩ/ሯ ውሳኔ ምንም ዓይነት ተጨማሪ የሥራውን ጥራት የሚያሳይ ሳይኖር ለተማሪው/ዋ ይገለፃል፡፡ ለአብነት በሥራው 60% አግኝተሀል/ሻል ወይም በጣም ጥሩ ሥራ ነው፡፡ ይህ ግብረ-መልስ ጥሩ ሥራ ስለተባለው ምን ነገር ጥሩ እንዳደረገው አይገልፅም፡፡ ተማሪው/ዋ ሥራውን ለምን እንደሆነ ከግምት ያለፈ ማስተካከያ ሊወስድ ወይም ልትወስድ አይ/ትችልም፡፡ ተማሪዎች የበለጠ ጥሩ ሆኖ የሚያገኙት መምህራን ገላጭ የሆነ ግብረ-መልስ ሲሰጧቸው እንጂ ግምገማዊ ግብረ-መልስ ሲሰጧቸው አይደለም፡፡ ምክንያቱም በገላጭ ግብረ-መልስ ለተማሪዎች የሚሰጠው ግብረ-መልስ ተማሪዎች የሰሩት ሥራ

ከተቀመጠው መስፈርት ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ሊነገራቸው ይገባል (አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ 2006)፡፡

እነዚህ የግብረ መልስ አይነቶች በተከታታይ ምዘና ሂደት ሦስቱም መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ቢቻልም፣ ከውጤታዊ ግብረ መልስ ይልቅ ውድድራዊና ገላጭ የሆኑ ግብረ መልሶችን መጠቀም በጣም አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.11 ብዙ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል ውስጥ የተከታታይ ምዘና አተገባበር

ምዘና በሂደት እየተካሄደ እንደሆነና የመማር ማስተማር ዓላማ መሳካት ወይም አለመሳካት ለማረጋገጥ የሚረዱ ሁሉንም ዘዴዎች ያካተተ ነው፡፡ ምዘና ያለምንም ጥርጥር በትክክል (Objectively) ሊለኩ የሚችሉ የሂደት ክፍሎችና ውጤቶችን እንዲሁም ግላዊ ሀሳብን የያዙ (subjective evaluative) የምዘና ውሳኔን ይጨምራል፡፡ ተከታታይ ምዘና ወይም ያለማቋረጥ በሂደት ላይ የሚካሄድ እና የአጠቃላይ ወይም በመጨረሻ ላይ (ማጠናቀቂያ ምዕራፍ) የሚካሄዱ የምዘና ክፍሎች ናቸው፡፡ የተማሪዎች ቁጥር በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተፅእኖ እንደሚያሳድረው ሁሉ በምዘና ዘዴዎችም ላይ የራሱ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያሉ የትምህርት ጽሁፎች ብዙ ተማሪዎች ካሉበት የመማሪያ ክፍሎች ጋር በተያያዘ በርካታ የምዘና ጉዳዮችን ለይተዋል፡፡ እነርሱም የሚከተሉትን ያካትታል፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ የውጤት አሰጣጥ ጫና፣ በቂና አፋጣኝ ግብረ-መልስ መስጠት፣ ያለምንም ዕውቅና መስጠት የሚደረግ ማጭበርበርና ኩረጃን መቆጣጠር፣ የውጤት አሰጣጥን ጥራትና ተአማኒነት መጠበቅ፣ አርቆ ማሰብን የሚጠይቁ ፈተናዎች በአንዳንድ የምዘና መሣሪያዎች እጥረት ያለ መሆን (አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ 2006)፡፡

ምንም እንኳ እነዚህ ጉዳዮች ለማንኛውም የተማሪ ቁጥር ላለባቸው ክፍሎች ችግሮች ቢሆኑም ብዙ ተማሪዎች ላሉባቸው ክፍሎች ችግሩቹ የከፉ (የተባባሱ) ናቸው፡፡ ምክንያቱም ተጨማሪ እጥረቶች በመኖራቸውና የሀብት ውሱንነት (ሰብአዊ እና ቁሳዊ) በመኖሩ ነው፡፡

## 2.12 ብዙ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል የምዘና መርሆች

ብዙ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል የሚኖሩ የምዘና መርሆች በሌሎች ክፍሎች ላይ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ ናቸው፡፡ መምህራን በመማሪያ ክፍላቸው ያሉ የተማሪዎች ብዛት ግምት

ውስጥ ሳያስገቡ ጥራት ያለውና በትክክል የተካሄደ ምዘና እንዲኖር ይፈልጋል፡፡ የተሻለ ምዘና የሚባለው ለተቀመጠለት ዓላማ ትክክለኛ (valid)፣ አስተማማኝ (realiable) እና ተገቢ (appropriate) ሲሆን ነው፡፡ ምዘናው ከተማሪዎች ውጤታማነት በመነሳት ሠርቲፊኬት ለመስጠት ወይም ምደባ ለማካሄድ የሚያስችል ሊሆን ይችላል ወይም የተማሪዎች መማርና ግንዛቤ ለመማቻቸት የሚረዳ ይሆናል፡፡ የምዘና መሣሪያዎች ትክክለኛ ናቸው የሚባለው እንዲመዝኑ ከተቀረፁበትን የተጣጣመ ማካሄድ ሲችሉ ነው (አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ 2006)፡፡

እንዲሁም መሣሪያዎቹ አስተማማኝ ናቸው የሚባሉት ተለዋዋጭ ያልሆነ ምዘና ማካሄድ ሲችሉ ነው፡፡ ሊነሱ የሚችሉ ቅሬታዎች ለመቀነሰ የምዘና ሂደቶች የትክክለኛነት ገፅታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የትክክለኛነት ገፅታ ያላቸው ምዘናዎች ለመዛኞችም ሆነ ለተመዛኞች ስህተት የሌለበት ምዘና እንዲኖር ያስችላቸዋል፡፡ አስተማማኝነት ያለው ምዘና ባለው የትክክለኛነት ገፅታ ምክንያት የተማሪዎችን ችሎታ ለመለካት የሚያስችል ተቀባይነት ያለው መመዘኛ ሁኗል፡፡ አስተማማኝነት ያለው ምዘና በምዘናው ከሚሳተፉት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ግንኙነት ያላቸው ግባራት መጠቀምን ያካትታል፡፡ ብዙ ተማሪዎች ባሉበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ አስተማማኝነት ያለው ምዘና ተግባራዊ ማድረግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም ለሁሉም ተማሪዎች የሚሆን በመስፈርት ላይ የተመሰረተ ልምድ ማቅረብ ስለማይቻል ነው (አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ 2006)፡፡

## 2.13 የምዘናና ግምገማ ጥቅሞች

የሚከተሉት የምዘናና ግምገማ ጥቅሞች ናቸው ፡-

1. የተማዎችን የመማር ዝግጁነትና ቀደምት ባህሪያት ለመለካት ያስችላል።
2. ጠንካራና ደካማ ተማሪዎችን ለመለየት ያስችላል።
3. የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት መፍትሄ ለመስጠት ያስችላል።
4. የተማሪዎችን የትምህርት ውጤትና የባህሪ ለውጥ ለማሻሻል ያስችላል።
5. የመምህሩን የመማር ማስተማር ዘዴ ለመቀየር ወይም ለማሻሻል ይጠቅማል።
6. መምህሩ የሚጠቀምባቸውን የመማር ማስተማር ሚዲያዎችን ለመለወጥና ለማሻሻል።
7. ተማሪዎችን በትምህርታዊ ተግባራትና የክፍል ደረጃ ለመመደብ።
8. የመምህሩን የትምህርት ዕቅድ ለመከለስና ለማሻሻል።

9. ለደካማ ተማሪዎች የምክርና የአመራር አገልግሎ ለመስጠት።

10. ተማሪዎችና ከክፍል ክፍል ለማዘዋወርና ሠርቲፊኬት ለመስጠት።

11. ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር ስለመምህሩና ስለመማር ማስተማሩ ሂደት መረጃ ለመስጠት።

12. የተማሪዎችን የመማር ዕድገትና ለውጥ ለወላጆች መረጃ ለመስጠት ወዘተ (ደሴ መም/ትምህርት ኮሌጅ ገፅ 2004፤3)።

## 2.14 የቀደምት ተጓዳኝ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸውን የተከታታይ ምዘና አተገባበር በሚመለከት የተደረጉ ጥናቶች ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ እነዚህም ጥናቶች ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ አራት ጥናቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም በዚህ ርዕስ ስር ለማየት የተሞከረው ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ግንኙነት ነው፡፡ እነዚህ ጥናቶችም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

1. ተስፋ አከለ (2000 ዓ/ም) የጥናቱ ርዕስ "የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ በትግራይ ክልል በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች" የሚል ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኮሌጅ የሚስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት የጽሁፍ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሲሆኑ ሰነድ ፍተሻና ምልከታ ደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፈጣንና በቂ ግብረ-መልስ እንደማይሰጡ፣ የተማሪዎቻቸው የግልና የቡድን ስራዎች ሲያርሙ መስፈርት እንደማይጠቀሙና የተከታታይ ምዘና ዕቅድ እንዳላካተቱ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

የተስፋ ጥናት ከዚህ ጥናት የሚመሳሰልበት በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሲሆን በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተለይ የጽሑፍ መጠያቆቹ አንድ ዓይነት ናቸው፡፡ ይህ ጥናት ከተስፋ ጥናት የሚለይበት በመጀመሪያ የተስፋ ጥናት ትኩረት በኮሌጅ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ምን እንደሚመስል መፈተሽ ሲሆን፣ የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ በአንደኛ ደረጃ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ

መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ምን እንደሚመስል ንጽጽራዊ በሆነ መልኩ መፈተሽ በመሆኑ፣ ስለዚህ በጥናቱ ትኩረት ይለያል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የተስፋ ዐቢይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጽሑፍ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ሲሆኑ፣ ሰነድ ፍተሻና ምልከታ ደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት ዐቢይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ደግሞ የጽሑፍ መጠይቅና ሰነድ ፍተሻ ሲሆኑ፣ ቃለ መጠይቅና ምልከታ ደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመሆናቸው በዚህ ይለያል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ በጥናቱ ዘመን ይለያል፡፡

2. ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያለው አልማዝ ሀይሉ (1999 ዓ/ም) ሲሆን ይህ ጥናት አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ርዕስም "አራተኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ" የሚል ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማም የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር መመርመር ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት የሰነድ ፍተሻና ምልከታ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሲሆኑ የጽሑፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በጥናቱ ግኝት መሰረትም ተጠኚ መምህራን ተከታታይ ምዘናን የሚተገብሩት ተከታታይ ፈተናዎችን በመስጠት እንደሆነ የጥናቱ አቅራቢ ለማረጋገጥ ችላለች፡፡
በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር በርዕስ ቢመሳሰልም በጥናቱ ትኩረት፣ በጥናቱ ዘመን ይለያያል፡፡

3. ከዚህ ርዕስ ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ የተመለከትኩት ሌላው የአልማዝ ፍሬው (2003) ሲሆን የጥናቱ ርዕስ "በአማራ ክልል በሚገኙ ሁለት የመግስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ" የሚል ሲሆን የጥናቱ ዋና ዓላማ በኮሌጅ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከታታይ ምዘና እንዴት እንደሚተገብሩ መመርመር ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት የክፍል ውስጥ ምልከታና የጽሑፍ መጠይቅ ዐቢይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሲሆኑ የሰነድ ፍተሻና ቃለ መጠይቅ ደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ የጥናቱ መረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ደግሞ አሃዛዊና ዓይነታዊ የመተንተኛ ዘዴዎች ሲሆኑ የጥናቱ ወጤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው የተከታታይ ምዘና መሳሪያዎች

የቡድን ስራ፣ የቃል ጥያቄ፣ እየወጡ ማቅረብና የክፍል ስራ ሲጠቀሙ የቢጤ ግምገማና የሚና ጨዋታ ወዘተ የማይጠቀሙባቸው መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

የአልማዝ ጥናት ትኩረት በኮሌጅ ደረጃ አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ በአንደኛ ደረጃ 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበራቸው ምን እንደሚመስል ንጽጽራዊ በሆነ መልኩ መፈተሽ ስለሆነ በርዕስና በአላማ ቢመሳሰልም በቦታና በጥናት ጊዜ ይለያያል፡፡

4. ከዚህ ጥናት ተያያዥነት ያለው ሌላው የሙሀመድ አሊ (2002 ዓ.ም) ጥናት ነው፡፡ የዚህ ጥናት ርዕስ "የተከታታይ ምዘና አተገባበር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ንጽጽራዊ ጥናት በደሴ ከተማ በሚገኙ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች" የሚል ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ቢመሳሰልም፣ የሙሀመድ አሊ ትኩረት በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ሲያተኩር የዚህ ጥናት ትኩረት ግን በአማራና በትግራይ ክልሎች 8ኛ ክፍልን የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከታታይ ምዘና አተገባበር ንጽጽራዊ በሆነ መልኩ ስለሚፈትሽ በዓላማ ይለያል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ንድፍና ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ይህ ጥናት የተካሄደው በአማራና በትግራይ ክልላዊ መንግስታት 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ንፅፅራዊ ጥናት (በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች) ላይ ያተኮረ በመሆኑ፣ የመረጃ ምንጮች በአራቱም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ሰነዶች፣ ርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ናቸው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጽሑፍ መጠይቅ፣ ሰነድ ፍተሻ፣ ቃለ መጠይቅና ምልከታ ሲሆኑ፣ ዓይነታዊና መጠናዊ የአተናተን ዘዴ በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡

## 3.2 የናሙና አመራረጥ

አራቱም ትምህርት ቤቶች የተመረጡት ከወሳኝ ንሞና ዘዴዎች መካከል አመቺ ወይም ግኝት የንሞና ዘዴ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ የንሞና ዘዴ አንድ ተመራማሪ ጥናቱን በቅርበት ባገኛቸውና ጥናቱን ለማካሄድ አመቺ በሆኑለት ሰዎች ወይም ነገሮች ላይ ተመርኩዞ ምርምሩን ሲያካሄድ አመቺ ተጠቀመ ማለት ይቻላል (ያለው 2004፣ 132)፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት አቅራቢም ከሥራ ቦታው ቅርበት ያላቸው ወረዳዎችና ትምህርት ቤቶች በመምረጥ ጥናቱ አድርጓል፡፡ እነዚህም ትምህርት ቤቶች በትግራይ ክልል የሚገኙት ሁለት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማለትም በፌናርዋ እና በየጭላ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ በአማራ ክልል ደግሞ በአበርገሌ ወረዳ የሚገኙትን የማዕርነትና የሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል የመምህራንን አመራረጥ በተመለከተ ጠቅላይ የንሞና ዘዴ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን በአራቱም ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ አራት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጥናቱ ተካተዋል፡፡ የተማሪዎችን አመራረጥ በተመለከተ እንደየትምህርት ቤቱ ተጨባጭ ሁኔታ ይለያያል፡፡ ምክንያቱም በ2009 ዓ/ም  በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዚህ የክፍል ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች 32 ብቻ በመሆናቸው ጠቅላይ የንሞና ዘዴ የተጠቀመ ሲሆን በሌሎቹ ትምህርት ቤቶች ግን ምድብ ለመምረጥ ከዕድል ሰጭ የንሞና ዘዴ አንዱ የሆነውን ዕጣ

የማውጣት ዘዴ ተጠቅሟል፡፡ በየጭላ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙ አምስት ምድቦች መካከል በዕጣ የማውጣት ዘዴ በመጠቀም የ8ኛ ‹ለ› ክፍል፣ በፊናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙ ሁለት ምድቦች መካከል የ8ኛ ‹ለ› ክፍል እንዲሁም በማዕርነት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙ ሁለት ምድቦች መካከል የ8ኛ ‹ሀ› ክፍል የተመረጡ ሲሆኑ ከሁሉም ትምህርት ቤቶች በአጠቃላይ አንድ መቶ ሀያ ስምንት (32×4=128) ተማሪዎች በረድፋዊ የአመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

## 3.3 የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

በዚህ ጥናት ስራ ላይ የዋሉት ዐቢይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎች የፅሑፍ መጠይቅና የሰነድ ፍተሻ  ሲሆኑ ደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎች ደግሞ ቃለ መጠይቅና ምልከታ ናቸው፡፡

### 3.3.1 የፅሑፍ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ስራ ላይ ከዋሉት ዋና ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አንዱ የፅሑፍ-መጠይቅ ነው፡፡ የጽሑፍ መጠይቆቹ የተዘጋጁት በመጀመሪያ ከጥናቱ ጋር ተቀራራቢ የሆኑት የቀደምት ጥናቶች የተጠቀሙዋቸውን መሳሪያዎች ፍተሻ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥናት ሊጠቅሙ የሚችሉ የጽሑፍ መጠይቆች የተወሰነ ማሻሻያ በማድረግ ተወስደዋል፡፡ የፅሑፍ መጠይቁ የቀረበው በጥናቱ ተሳታፊ ለሆኑት መምህራንና ተማሪዎች ነው፡፡ የጽሑፍ መጠይቆቹም ለተማሪዎች የቀረቡት አጠቃላይ መረጃና 28 ዝግ ጥያቄዎች ሲሆኑ በአራቱም ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ደግሞ አጠቃላይ መረጃ፣ 50 ዝግና 3 ልቅ ጥያቄዎችን የያዙ ናቸው፡፡

### 3.3.2 ሰነድ ፍተሻ

በዚህ ጥናት ውስጥ ከፅሑፍ መጠይቅ በተጨማሪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሰነድ ፍተሻ ተደርጓል፡፡ የሰነድ መፈተሻ ቅጾች በተዛማጅ ጽሑፍ ከተነሱት በመመስረት ተዘጋጅተዋል፡፡ መምህራን በየጊዜው የሚጠቀሙባቸውን ሰነዶች በመፈተሽ ከፅሑፍ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች ትክክለኛነታቸውንና ተአማኒነታቸውን ለማረጋገጥ ከፍተኛ እገዛ አድርጓል፡፡ በመሆኑም መምህራን የተከታታይ ምዘና ተግባራትን በአግባቡ መዝግቦ

ለመያዝ የሚጠቀሙባቸውን የውጤት መመዝገቢያ ቅፆችና ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት የሚያከናውኑዋቸው የግል ስራዎች ተፈትሸዋል፡፡

### 3.3.3 ቃለ መጠይቅ

ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ ለማጠናከር ቃለ መጠይቅ እንደደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አገልግሏል፡፡ ቃለ መጠይቆቹ በተዛማጅ ጽሑፍ ከተነሱት በመመስረት ተዘጋጅተዋል፡፡ በቃለ መጠይቁ ለሚሳተፉ አራት ርዕሳነ መምህራንና አራት የጉድኝት ማዕከል ሱፐርቫይዘሮች ስድስት የተዋቀሩ የቃል ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል፡፡

### 3.3.4 ምልከታ

ለጥናቱ የሚሆኑ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የምልከታ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ስራ ላይ ውሏል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ምልከታውን ለመከታተል የምልከታ ቅፅ ተዘጋጅቷል፡፡

## 3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተን አይነታዊና አሃዛዊ የመረጃ አተናተን ዘዴዎች ስራ ላይ ውለዋል፡፡ ጥናቱ አይነታዊና መጠናዊ መረጃ የመተንተኛ ዘዴዎች ስልትን የተከተለበት ምክንያትም የጥናቱን ርዕሰ ጉዳዮች ለመግለጽ የሚያስችሉ ዘዴዎች በመሆናቸውና ለጥናቱ አጋዥ የሚሆኑ መረጃዎችን ማለትም በፅሑፍ መጠይቅ፣ በሰነድ ፍተሻ፣ በቃል መጠይቅና በምልከታ የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተን ምቹ ናቸው ተብለው በመታሰባቸው ነው፡፡ ከቃለ መጠይቅ፣ ከሰነድ ፍተሻ እንዲሁም ልቅ የፅሑፍ ጥያቄዎች የተገኘ መረጃ በሰፊው በገለጻ መልኩ ተተንትኗል፡፡ ከአይነታዊ የመተንተኛ ዘዴ በተጨማሪም በመጠን ለሚገለጹ ከዝግ ጥያቄዎች የተገኙትን መረጃዎች ደግሞ መጠናዊ (አሀዛዊ) የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት
# የመረጃ ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ስር በምዕራፍ ሦስት በዐቢይና በንዑስ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመጀመሪያ በሰንጠረዥ ከቀረቡ በኋላ በመጨረሻ በገለጻ መልኩ ተተናትነዋል፡፡ የሁለቱም የጥናቱ ተተኳሪ ቡድኖች አማካይ ውጤት ተሰልቶ መጠነ ልይይቱ ተቀምጦ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ የልይይት መጠን የሚያመለክተው አዎንታዊ ከሆነ የአማራ ክልል ትምህርት ቤቶች የተሻሉ መሆናቸው ሲያመለክት፣ አሉታዊ ከሆነ ደግሞ የትግራይ ትምህርት ቤቶች የተሻሉ መሆናቸውን ያሳያል ማለት ነው፡፡

## 4.1 የመምህራን አጠቃላይ መረጃ

የመምህራን አጠቃላይ መረጃ ስንመለከት ወንድ= 6፣ ሴት= 2 በድምር= 8 ሲሆኑ ከትምህርት ደረጃ አንጻር ዲፕሎማ = 4 ሲሆኑ ዲግሪ = 4 ናቸው፡፡ የአገልግሎት ዘመን ስንመለከት ከ3 እስከ 30 ዓመት ናቸው፡፡ ሥልጠና በተመለከተ አንድ ስልጠና የወሰደ ሦስት ደግሞ ስልጠና ያልወሰዱ ናቸው፡፡ ስለሆነም ከዚህ መረዳት የሚቻለው መምህራኑ በቂ የትምህርት ዝግጅትና የአገልግሎት ዘመን ስላላቸው በቂ የሆነ መረጃ ተገኝቷል፡፡

**ሰንጠረዥ 3 ፡- የተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ**

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | አጠቃላይ የተማሪዎች | | | ናሙና ተማሪዎች | | | | የምድብ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | % | |
| 1 | ማዕርነት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 56 | 59 | 115 | 16 | 16 | 32 | 27.8 | 2 |
| 2 | ሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 12 | 20 | 32 | 20 | 12 | 32 | 100 | 1 |
| 3 | የጭላ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 153 | 172 | 325 | 16 | 16 | 32 | 9.8 | 5 |
| 4 | ፊናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 63 | 65 | 128 | 16 | 16 | 32 | 25 | 2 |

ከዚህ ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው በማዕርነት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 8ኛ ክፍል ከሚማሩት ወንድ 56፣ ሴት 59፣ በድምሩ 115 ተማሪዎች መካከል ወንድ 16፣ ሴት 16፣ በድምሩ 32 ተማሪዎች የተመረጡ ሲሆኑ በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚማሩት ወንድ 12፣ ሴት 20፣ በድምሩ 32 ተማሪዎች ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል፡፡ እንደዚሁም በየጭላ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚማሩት ወንድ 153፣ ሴት 172፣ ድምር መካከል ወንድ 16፣ ሴት 16፣ በድምሩ 32 ተማሪዎችን በናሙናነት የተመረጡ ሲሆኑ፣ በፊናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወንድ 63፣ ሴት 65፣ ድምር 128 ተማሪዎች መካከል በተመሳሳይ ወንድ 16፣ ሴት 16፣ ድምር 32 ተማሪዎችን በናሙናነት የተመረጡ መሆናቸውን መመልከት ይቻላል፡፡

## 4.2 ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

### ሠንጠረዥ 4 ፡- የተከታታይ ምዘና አጠቃላይ መርህን በተመለከተ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X1) | በየጭላና በፊናርዋ አንደኛ ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X2) | ልይይት (X1-X2) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | | |
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | | |
| 1 | መምህራን የተለያዩ የቡድንና የግል ተግባራትን ከመስጠታቸው በፊት ግልጽ የሆነ መመሪያና ማብራሪያ ይሰጡኛል | 6 | 9.4 | 8 | 12.5 | 10 | 15.6 | 40 | 62.5 | 1.7 | 39 | 60.9 | 7 | 10.9 | 15 | 23.4 | 3 | 4.7 | 3.3 | -1.6 |
| 2 | ከተለያዩ የምዘና ስልቶች የሚገኘው መረጃ ለወደፊቱ ማሻሻል ያለብኝን ነገር እንድገነዘብ አስችሎኛል | 4 | 6.3 | 14 | 21.9 | 12 | 18.8 | 34 | 53.1 | 1.8 | 5 | 7.8 | 3 | 4.7 | 22 | 34.4 | 34 | 53.1 | 1.7 | 0.1 |
| 3 | በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ በማሳያቸው ድክመቶች የማስተካከያ እገዛ ያደርጉልኛል | 6 | 9.3 | 14 | 21.8 | 20 | 31.2 | 24 | 37.5 | 2.03 | 34 | 53.1 | 14 | 21.8 | 16 | 25 | - | - | 3.3 | -1.25 |
| 4 | በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ መምህራን የተለያዩ የማጠናከሪያ ተግባራትን እየሰጡ ችሎታዬን የበለጠ እንዳዳብር ያደርጉኛል | 2 | 3.12 | 16 | 25 | 14 | 21.8 | 32 | 50 | 1.8 | 33 | 51.6 | 14 | 21.9 | 11 | 17.2 | 6 | 9.3 | 3.1 | -1.3 |
| 5 | ከተለያዩ የምዘና ስልቶች የማገኘው መረጃ ለወደፊቱ ማሻሻል ያለብኝን ነገር እንድገነዘብ አስችሎኛል | 8 | 12.5 | 4 | 6.25 | 8 | 12.5 | 44 | 68.8 | 1.6 | 38 | 59.3 | 12 | 18.7 | 10 | 15.6 | 4 | 6.25 | 3.3 | -1.64 |

ከላይ ከሰንጠረዥ 4 ማየት እንደሚቻለው በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች በተራ ቁጥር አንድ፣ “መምህራን የተለያዩ የቡድንና የግል ተግባራትን ከመስጠታቸው በፊት ግልጽ የሆነ መመሪያና ማብራሪያ ይሰጡኛል፡፡” ለሚለው ጥያቄ 14 (21.8%) ያህሉ አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ፣ አብዛኛዎቹ ማለትም 50 (77.6%) ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ በትግራይ ክልላዊ መንግስት ሥር የሚገኙ የየጭላና የፊናርዋ ተማሪዎች ደግሞ 41 (64.06%) አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ ቀሪዎቹ 23 (35.93%) ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በተመሳሳይ የየጭላና የፊናርዋ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤት ተሰልቶ X1 (1.69) ሲሆን፣ የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች አማካይ ውጤት ደግሞ X2 (3.28) ነው፡፡ መጠነ ልይይት ስናየው X1-X2 (1.69-3.28=-1.59) በመሆኑ አሉታዊ ውጤቱ የሚያመለክተው የማዕርነትና የሳቃ መምህራን የተለያዩ የቡድንና የግል ተግባራትን ከመስጠታቸው በፊት ግልጽ የሆነ ማብራሪያ እንደማይሰጡዋቸው ያመለክታል፡፡

ስለሆነም ከፍ ሲል ከቀረበው ትንትና መረዳት የሚቻለው የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች የግልና የቡድን ሥራ ከመሰጠታቸው በፊት ማብራሪያ እንደማይሰጡዋቸው ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ የየጭላና የፊናርዋ መምህራን ግን ማብራሪያ እንደሚሰጡዋቸው ማየት ተችሏል፡፡

በተራ ቁጥር 2 ለቀረበላቸው ጥያቄ የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች 46 (71.9%) የሚሆኑት ከተለያዩ የምዘና ስልቶች የሚያገኙትን መረጃ ለወደፊቱ ማሻሻል ያለባቸውን ነገር እንዲገነዘቡ አለመቻላቸውን ሲገልጹ፣ ቀሪዎቹ 18 (28.1%) አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። በተመሳሳይ የየጭላና የፊናርዋ ተማሪዎች 56 (87.5%) አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ ቀሪዎቹ 8 (12.5%) ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የሁለቱም አማካይ ውጤት ማለትም ልይይት =X1-X2 (1.8-1.7 = 0.1) ወደ ዜሮ የተጠጋ በመሆኑ የጎላ ልዩነት የላቸውም፡፡

ስለዚህ ከፍ ሲል ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው በአራቱም ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ከተለያዩ የምዘና ስልቶች የሚያገኙዋቸውን መረጃዎች ለወደፊቱ ማሻሻል ያለባቸውን እንዲገነዘቡ አለመቻላቸውን ጥናቱ ማረጋገጥ ችሏል፡፡

እንዲሁም በጥያቄ ቁጥር 3 ለቀረበላቸው ጥያቄ የማዕርነትና የሳቃ መምህራን 44 (68.8%) ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ በሚያሳዩዋቸው ድክመቶች እገዛ እንደማያደርጉላቸው

ሲያመለክቱ፣ ቀሪዎቹ 20 (31.3%) አዎንታዊ ምላሽ ሰጥዋል፡፡ ይሁን እንጂ የየጭላና የፊናርዋ ተማሪዎች ደግሞ 48 (75%) በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ በሚያሳዩዋቸው ድክመቶች እገዛ እንደሚያደርጉላቸው ሲጠቁሙ፣ 16 (25%) እገዛ እንደሚያደርጉላቸው ገልጸዋል። እንዲሁም መጠነ ልይይት ማለት X1-X2 (2.03-3.28 = -1.25) ስለሚያሳይ በሁለቱም ቡድኖች መካከል ልዩነት መኖሩን ማየት ይቻላል፡፡

ስለሆነም ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ በሚያሳዩዋቸው ድክመቶች የማስተካከያ እገዛ እንደማያደርጉላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በየጭላና በፊናርዋ ግን የማስተካከያ እገዛ እንደሚያደርጉላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

እንዲሁም ሁለቱም በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች በተራ ቁጥር 4 ለቀረበው ጥያቄ 46 (71.9%) ተማሪዎች የማጠናከሪያ ተግባራትን አይሰጠንም ሲሉ፣ 18 (28.1%) ደግሞ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፤ በተቀራኒው በየጭላና በፊናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ደግሞ 47 (73.4%) መምህሮቻቸው በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ የተለያዩ የማጠናከሪያ ተግባራትን እየሰጡ ችሎታቸውን የበለጠ እንዲያዳብሩ ሙሉ በሙሉ እንደሚያግዙዋቸው ሲገልጹ፣ ቀሪዎቹ 17 (26.6%) አሉታዊ ምላሽ መልሰዋል፡፡ ከአማካይ ውጤት የልይይት መጠንም ማየት ይቻላል፡፡

በመሆኑም ከትንተናው መረዳት የሚቻለው የማዕርነትና የሳቃ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የተለያዩ የማጠናከሪያ ትምህርት ስለማይሰጡ ችሎታቸውን ማዳበር ያልቻሉ መሆናቸውን ሲገልጹ፣ በየጭላና በፊናርዋ ግን የተለያዩ የማጠናከሪያ ትምህርት እንደሚሰጡ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

ከላይ ከሰንጠረዡ ማየት እንደሚቻለው በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች በተራ ቁጥር አምስት ለቀረበው ጥያቄ 12 (18.8%) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ አብዛኛዎቹ ማለትም 52 (81.3%) አለታዊ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ይሁን እንጂ የየጭላና የፊናርዋ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ደግሞ 50 (78.1%) አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ 14 (21.9%) ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡

በመሆኑም ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው የየጭላና የፌናርዋ ተማሪዎች ከተለያዩ የምዘና ስልቶች የሚገኘውን መረጃ ተማሪዎቹ ለወደፊት ማሻሻል ያለባቸውን ነገሮች እንዲገነዘቡ ማስቻሉን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል ግን የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች ለወደፊት ማሻሻል ያለባቸው መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ መጠነ ልይይቱም (1.64) በመሆኑም በማዕርነትና በሳቃ ከምዘና ስልቶቹ የሚገኘውን መረጃ ተማሪዎቹ ወደፊት ማሻሻል ያለባቸውን ነገሮች እንዳያሻሽሉ ማድረጉን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተጨማም በአማራ ክልል የሚገኙ በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሰነድ ፍተሻና ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በየጊዜው ጠንካራና ደካማ ጎኖች ተለይተው፣ ውጤታማ የሆነ የድጋፍ እና ክትትል ስርዓት ተዘርግቶ የሚያሳይ መረጃ (ሰነድ) አልተገኘም፡፡

## ሰንጠረዥ 5 ፦ በአራቱም ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በተከታታይ ምዘና ጠቀሜታ ዙሪያ የሰጡት ምላሽ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X1) | በየጭላና በፌናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X2) | ልይይት (X1-X2) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | | |
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ | % | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | | |
| 6 | በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ሁል ጊዜ የራሴን በራሴ እገመግማለሁ | 8 | 12.5 | 14 | 21.8 | 16 | 25 | 26 | 40.6 | 2.06 | 2 | 3.12 | 8 | 12.5 | 16 | 25 | 38 | 59.37 | 1.66 | 0.4 |
| 7 | በግልም ሆነ በቡድን ለማከናውናቸው ተግባራት ጓደኞቼ አስተያየት /ምጋቤ ምላሽ/ ይሰጡኛል | 10 | 15 | 6 | 9.3 | 20 | 31.2 | 28 | 43.7 | 1.97 | 51 | 79.68 | 8 | 12.5 | - | - | 5 | 7.81 | 3.71 | -1.74 |
| 8 | በማከናውናቸው የቡድንና የግል ተግባራት የመምህራን ትኩረት አንድን ነገር እንዴት አድርጌ እንደሰራሁት ማየት ሳይሆን ምን እንደሰራሁ ማየት ነው | 40 | 62.2 | 14 | 21.8 | 6 | 9.3 | 4 | 6.2 | 3.4 | 8 | 12.5 | 9 | 14.6 | 14 | 21.87 | 33 | 51.56 | 1.88 | 1.52 |
| *9* | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ እንደሙከራ የቡድንና የግል ስራ የመሳሰሉ የምዘና ስልቶችን የሚጠቀሙት በትምህርቱ ሂደት ያሳየሁትን መሻሻል ለመመዘን ሳይሆን ውጤት መስጠት ነው | *56* | *87.5* | *4* | *6.2* | *4* | *6.2* | *-* | *-* | *3.81* | *5* | *7.8* | *10* | *15.62* | *11* | *17.2* | *38* | *58.6* | *1.97* | *1.84* |
| 10 | ከተለያዩ የምዘና ስልቶች የማገኘው መረጃ ለወደፊቱ ማሻሻል ያለብኝን ነገር እንድገነዘብ አስችሎኛል | 6 | 9.3 | 10 | 15.6 | 16 | 25 | 32 | 50 | 1.84 | 35 | 54.6 | 11 | 17.18 | 16 | 25 | 2 | 3 | 3.23 | -1.39 |

ከላይ ከሰንጠረዥ 5 ማየት እንደሚቻለው በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች በተራ ቁጥር 6 ላይ ለቀረበው "በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ሁል ጊዜ የራሴን በራሴ እገመግማለሁ" ለሚለው ጥያቄ 22 (34.37%) የሚሆኑት ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ ቀሪዎቹ 42 (65.6%) ተማሪዎች በተከታታይ ምዘና ሂደት የራሳቸውን ስራ በራሳቸው እንደማይገመግሙ አመልክተዋል፡፡ በተመሳሳይ በትግራይ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የየጭላና የፊናርዋ ተማሪዎች 11 (17.19%) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ 53 (82.81%) የሚሆኑት ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ የልይይት መጠን ጠቋሚ ስሌት (0.4) የሚያሳየውም ተቀራራቢ መሆኑን ነው፡፡

ስለዚህም ከመረጃ ትንተናው መረዳት የሚቻለው በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን፣ ተማሪዎቻቸው የራሳቸውን ስራዎች በራሳቸው እንደማይገመግሙ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች በተራ ቁጥር 7 ለቀረበው ጥያቄ 16 (25%) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ ቀሪዎቹ 48 (75%) ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን የየጭላና የፊናርዋ 59 (92.19%) ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ 5 (7.81%) የሚሆኑት ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

በተራ ቁጥር 8 ለቀረበው ጥያቄ 54 (84.38%) የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች እንደገለጹት በሚያከናውኑዋቸው የቡድንና የግል ተግባራት የመምህራኑ ትኩረት በውጤቱ ነው ሲሉ፣ 10 (15.62) የሚሆኑት ደግሞ የመምህራኑ ትኩረት በሂደቱ እንጂ በውጤቱ አይደለም ብሏል፡፡ በአንጻሩ 47 (73.44%) የሚሆኑት የየጭላና የፊናርዋ ተማሪዎች የመምህሮቻቸው ትኩረት በውጤት ብቻ ሳይሆን በሂደት ነው ሲሉ፣ ቀሪዎቹ 17 (26.56%) በውጤት እንጂ በሂደት አይደለም ብሏል፡፡

ስለሆነም ከፍ ሲል ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ አራቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች የራሳቸውን ሥራ በራሳቸው እንደማይመዝኑ ማየት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የግልና የቡድን ሥራዎች ሰጥተው የየጭላና የፊናርዋ መምህራን ትኩረት ተማሪዎቹ ያሳዩትን መሻሻል ለማየት ሲሆን፣ የማዕርነትና የሳቃ መምህራን ትኩረት ግን ለውጤት መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ የልይይት መጠን ስሌትም X1-X2 (1.97-3.71)= -1.74 የሚያሳየው በምዘናው ትኩረት እንደሚለያዩ ያሳያል፡፡

በተመሳሳይ የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ የመምህሮቻቸው ትኩረት በሂደት ሳይሆን በውጤት መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ በአንጻሩ የየጭላና የፊናርዋ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ከውጤት ይልቅ በሂደት መሆኑን ጥናቱን አረጋግጧል፡፡

በተራ ቁጥር 9 ለቀረበው "የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ እንደሙከራ የግልና የቡድን የመሳሰሉት የምዘና ስልቶችን የሚጠቀሙት በትምህርቱ ሂደት ያሳየሁትን መሻሻል ለመመዘን ሳይሆን ውጤት መስጠት ነው" ለሚለው ጥያቄ 60 (93.75%) የሚሆኑ የማዕርነትና የፍናርዋ ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ 4 (6.25%) አሉታዊ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ በአንጻሩ የየጭላና የፊናርዋ ተማሪዎች 15 (23.44%) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ ከሦስት እጅ በላይ 49 (76.55%) የሚሆኑ አሉታዊ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

እንዲሁም በተራ ቁጥር 10 ለቀረበው ጥያቄ የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች 16 (25%) አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ፣ አብዛኛዎቹ 48 (75%) ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተለያዩ የምዘና ስልቶችን የሚጠቀሙት ለተለያየ አላማ መሆኑን የልይይት መጠን ስሌት ማለትም X1-X2 (3.81-1.97=1.84) የሚያሰየው በአማራ ክልላዊ መንግስት (በማዕርነትና በሳቃ) እና በትግራይ ክልላዊ መንግስት (በየጭላና በፊናርዋ) መካከል ሰፊ ልዩነት እንዳለ ያሳያል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የየጭላና የፊናርዋ ተማሪዎች ከተለያዩ የምዘና ስልቶች የሚያገኙዋቸውን መረጃዎች ለወደፊቱ ማሻሻል ያለባቸውን ነገሮች እንዲገነዘቡ አስችላቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ግማሽ የሚሆኑ የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች መገንዘብ እንዳልቻሉ አስቀምጠዋል፡፡

ከላይ ከቀረበው የትንተና ውጤት መገንዘብ የሚቻለው በአራቱም ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የራሳቸውንና የጓደኞቻቸውን ስራዎች በራሳቸው እንዲመዝኑ ዕድል አላገኙም፡፡

ይሁን እንጂ ተስፋ (2000፣75)፣ Shabaan (2001፣20)፣ Hamis (1997፣10) Puhi (1997፣7) እንደሚያሳስቡት በተከታታይ ምዘና ወቅት ተማሪዎች የጓደኛ ለጓደኛ እና የራሳቸውን ስራ

በራሳቸውን እንዲመዝኑ (እንዲገመግሙ) ማድረግ የቋንቋ ችሎታቸውን የበለጠ እንዲያዳብሩና ብስለት የተሞላበት የማሰብ ችሎታ እንዲያጎለብቱ ያደርጋቸዋል ይላሉ፡፡

ምንም እንኳን በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተከታታይ ምዘናን መጠቀም የትምህርት አሰጣጡን ለማሻሻል ቢሆንም የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ እንደሙከራ፣ የቡድንና የግል ስራን የመሳሰሉትን የምዘና ስልቶች የሚጠቀሙት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ያሳዩዋቸውን መሻሻሎች ለመመዘን ሳይሆን ውጤት ለመስጠት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንዲሁም ከተለያዩ የምዘና ስልቶች የሚያገኙት መረጃዎች ለቀጣይ ማሻሻል ያለባቸውን ነገሮች እንዲገነዘቡ አለማስቻሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የምዘናቸው ትኩረት በሂደቱ ሳይሆን በውጤቱ ላይ ያተኮረ መሆኑን የተማሪዎቹ ምላሽ ያሳያል ፡፡

ይሁን እንጂ ከርዕሳነ መምህራኑና ከሱፐርቫይዘሮቹ የቃለ መጠይቅ ምላሽ መረዳት የሚቻለው በማዕርነትና በሳቃ ትምህርት ቤቶች ሂደታዊና የማጠቃለያ የምዘና ዓይነቶች እንደሚጠቀሙ የምዘና ስርዓቱ የሚሳይ ቢሆኑም፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከመሰልቸት የተነሳ በብዛት የሚጠቀሙት ማጠቃለያ ምዘናን መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአንዳንድ መምህራንም ተከታታይ ምዘናው በተከታታይ መዝነው ለመማር ማስተማር ዘዴ ማስተካከያ ሳይሆን ከሁሉም የተሻለ ውጤት በነጥብ መለኩ ለመያዝ እንደሆነ በምልከታ የተሰበሰበ መረጃ ያሳያል፡፡ ነገር ግን ተከታታይ ምዘና መሰጠት ያለበት የመማር ማስተማሩን ዘዴ ለመምረጥ መሆን እንዳለበት በክለሳ ድርሳናት ከተለያዩ ምሁራን ከቀረበው ሐሳብ መመልከት ተችሏል፡፡

## ሰንጠረዥ 6 ፡- የተከታታይ ምዘና እርማት አሰጣጥ፣ ደካማና እና ጠንካራ ጎኖችንና መሻሻል ጉዳዮች የሚያሳይ መረጃ ትንተና

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት | በየጭላና በፌናርዋ አንደኛ ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት | ልይይት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | | በጣም አልስማማም | | እስማማማም | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | | |
| | | በቁ. | % | በቁ. | % | በቁ. | % | በቁ. | % | | በቁ. | % | በቁ. | % | በቁ. | % | በቁ. | % | | |
| 11 | በተከታታይ ምዘና ሂደት በውጤት ዙሪያ ከመምህራን ጋር ተወያይተን እንወስናለን | - | - | 4 | 6.3 | 6 | 9.3 | 54 | 84.3 | 1.22 | 5 | 7.8 | 9 | 14 | 16 | 25 | 34 | 53.1 | 1.77 | -0.55 |
| 12 | በተከታታይ ምዘና የማገኘው ውጤት ከስራዬ ጋር የሚመጣጠን ነው | 34 | 53.1 | 10 | 15.6 | 10 | 15.6 | 10 | 15.6 | 3.06 | 38 | 59.4 | 12 | 18.8 | 14 | 21.9 | - | - | 3 | 0.06 |
| 13 | የሰራሁት ስራ አጥጋቢ ካልሆነ ድክመቴን የማሻሽልበት ሌላ ዕድል ይኖረኛል | 2 | 3.1 | 6 | 9.3 | 16 | 25 | 44 | 68.8 | 1.41 | 46 | 71.8 | 10 | 15.6 | 8 | 12.5 | - | - | 3.59 | -2.18 |
| 14 | ከተከታታይ ምዘና የማገኘው መረጃ የራሴን የጥናት ፕሮግራም እንዳስተካክል ረድቶኛል | 6 | 9.3 | 4 | 6.2 | 8 | 12.5 | 46 | 71.8 | 1.53 | 39 | 60.9 | 11 | 17.2 | 14 | 21.9 | - | - | 3.39 | -1.86 |
| 15 | በቡድንና በግል የማከናውናቸው ተግባራት ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንድለይ አስችለውኛል | 10 | 15.6 | 10 | 15.6 | 8 | 12.5 | 36 | 56.2 | 1.91 | 36 | 56.2 | 10 | 15.6 | 8 | 12.5 | 10 | 15.56 | 3.13 | -1,22 |
| 16 | ከማጠቃለያ ፈተና ይልቅ በተለያዩ ጊዜያት የማከናውናቸው ስራዎች በአማርኛ ቋንቋ የማገኘውን ትምህርት የተሻለ ነው | 4 | 6.3 | 4 | 6.3 | 6 | 9.3 | 50 | 78.1 | 1.41 | 42 | 65.8 | 16 | 25 | 6 | 9.4 | - | - | 3.56 | -2.15 |

ከላይ ከሰንጠረዥ 6 በተራ ቁጥር 11 ለቀረበው ጥያቄ 4 (6.25%) የሚሆኑት የማዕርነትና የሳቃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ አብዛኛዎቹ ማለትም 60 (93.75%) የሚሆኑት ደግሞ በተከታታይ ምዘና ሂደት የሰሩዋቸውን የተለያዩ የቡድንና የግል ስራዎች እንዴት እንደሚታረሙና ምን ያህል ውጤት መያዝ እንዳለባቸው ከመምህራኑ ጋር ተወያይተው እንደማይስኑ መመልከት ይቻላል፡፡ ለዚህ ጥያቄ 14 (21.87%) የሚሆኑት የየጭላና የፈናርዋ ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ አብዛኛዎቹ 50 (78.12%) ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የልይይት መጠኑ (-0.55) ብቻ ስለሆነ ሰፊ ልዩነት የላቸውም፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎች ለሚሰሯቸው የቡድንና የግል ስራዎች እንዴት እንደሚታረሙና ምን ያህል ውጤት መያዝ እንዳለባቸው ከመምህራን ጋር ተወያይተው እንደማይወስኑ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

በተራ ቁጥር 12 ለቀረበው ጥያቄ የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች 44 (68.75%) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ ቀሪዎቹ 20 (31.25%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በአንጻሩ ከግማሽ በላይ የሚሆኑትን የየጭላና የፈናርዋ ተማሪዎች ማለትም 50 (78.12%) ለምንሰራቸው የቡድንና የግል ስራዎች የምናገኘው ውጤት ከስራችን ጋር የሚመጣጠን እንደሆነ ይሰማናል ሲሉ 14 (21.87%) የማዕርነትና የፈናርዋ ተማሪዎች ግን "ለምንሰራቸው የቡድንና የግል ስራዎች የምናገኘው ውጤት ከስራችን ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ ይሰማናል" ብለዋል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች የሚያገኙትን ውጤት ከሚሰሩት ስራ ጋር የሚመጣጠን ሲሆን፣ በአንጻሩ የየጭላና የፈናርዋ ተማሪዎች ግን የሚያገኙትን ውጤት ከስራቸው ጋር የማይመጣጠን መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ የልይይት መጠን (0.06) የሚያሳየውም የማዕርነትና የሳቃ በውጤት በኩል የተሻሉ መሆናቸውን ማወቅ ተችሏል፡፡

በተራ ቁጥር 13 ለቀረበው ጥያቄ የየጭላና የፈናርዋ ተማሪዎች አብዛኛዎቹ ማለትም 56 (87.5%) የሚሆኑት "በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የሰራሁት ስራ አጥጋቢ ካልሆነ ድክመቴን የማሻሽልበት ሌላ ዕድል ይሰጠኛል" የሚል ምላሽ ሲሰጡ፣ ቀሪዎቹ 8 (12.5%) የሚሆኑት ደግሞ ሌላ ዕድል አይሰጠንም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በተቃራኒው 56 (87.5%)

የሚሆኑት የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች "በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የሰራነው ስራ አጥጋቢ ካልሆነ ድክመታችን የምናሻሽልበት ሌላ ዕድል አይሰጠንም" ሲሉ፣ ጥቂቶች 8 (12.5%) የሚሆኑት ደግሞ አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የልይይት መጠን (-2.18) የሚያሰየውም ሰፊ የሆነ ልዩነት መኖሩን ይጠቁማል፡፡

በተመሳሳይ መልክ በተራ ቁጥር 14 "ከሙከራ፣ ከቤት ስራ፣ ከቡድንና ከግል ስራዎች የሚገኘው መረጃ የራሴን የጥናት ፕሮግራም እንዳስተካክል ረድቶኛል" የሚለውን ጥያቄ 10 (15.63%) የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ፣ አብዛኛዎቹ 54 (84.37%) ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በአንጻሩ 50 (78.13%) የየጭላና የፌናርዋ ተማሪዎች መስማማታቸውን ሲጠቁሙ፣ ቀሪዎቹ 14 (21.87%) አለመስማማታቸውን አስቀምጧል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሁለት ጥያቄዎች የመረጃ ትንተና መረዳት የሚቻለው በትግራይ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የየጭላና የፌናርዋ መምህራን በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቻቸው የሚያሳዩትን ድክመት እንዲያሻሽሉ ሌላ ዕድል በመስጠት በኩል በአማራ ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ የማዕርነትና የሳቃ መምህራን ይልቅ የተሻሉ መሆናቸውን ጥናቱን አረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም የየጭላና የፌናርዋ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ ከሙከራ፣ ከቤት ስራ፣ ከቡድንና ከግል ስራዎች የሚያገኙትን መረጃ የራሳቸው የጥናት ፕሮግራም እንዲያስተካክሉ እንደሚረዳቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሁለቱም ቡድኖች አማካይ ውጤት የልይይት መጠን (-1.86) የሚሳየውም በሁለቱም ቡድኖች መካከል ሰፊ የሆነ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡

በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች በተራ ቁጥር 15 "በቡድንና በግል የማከናውናቸው የተለያዩ የምዘና ተግባራት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ የማሳያቸው ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንድንለይ አስችሎኛል" የሚል ጥያቄ 20 (31.25%) የሚሆኑ ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ አብዛኛዎቹ 44 (68.75%) አሉታዊ መልስ ሰጥቷል፡፡ በትግራይ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የየጭላና የፌናርዋ ተማሪዎች 46 (71.88%) የሚሆኑት አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ፣ ቀሪዎቹ 18 (28.12%) የሚሆኑት አሉታዊ መልስ ሰጥቷል፡፡

በመጨረሻ ለቀረበላቸው ጥያቄ ቁጥር 16 በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች 8 (12.5%) የሚሆኑት አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ፣ አብዛኛዎቹ 56 (87.5%) ተማሪዎች ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰጥቷል፡፡ በትግራይ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የየጭላና የፌናርዋ ተማሪዎች አብዛኛዎቹ ማለትም 58 (90.63%) በጽሑፍ ፈተና ላይ ከተመሰረተ ምዘና ይልቅ በተለያዩ ጊዜያት የሚያከናውኑዋቸው የቤት ስራዎች፣ የቡድንና የግል ስራዎች በአማርኛ ቋንቋ የሚገኘውን ትምህርት የተሻለ እንዳደረጓቸው ሲያመለክቱ፣ ቀሪዎቹ 6 (9.37%) አሉታዊ መልስ መስጠታቸው ከሰንጠረዡ መመልከት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው የመረጃ ትንተና መረዳት የሚቻለው በአማራ ክልላዊ መንግስት ስር የሚገኙ የማዕርነትና የሳቃ ተማሪዎች በተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ የሰሯቸውን የተለያዩ የግል ስራዎች እንዴት እንደሚታረሙና ምን ያህል ውጤት መያዝ እንዳለባቸው ከመምህራን እንደማይወያዩ ሲገልጹ፣ ይሁን እንጂ በትግራይ ክልላዊ መንግስት ስር የሚገኙ የየጭላና የፌናርዋ ተማሪዎች ለሚሰሩዋቸው የቡድንና የግል ስራዎች የሚያገኙዋቸው ውጤቶች ከስራቸው ጋር የሚመጣጠኑ እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪ አጥኚው በአማራ ክልል የሚገኙ ሁለቱም ትምህርት ቤቶች ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ፣ ከቃለ መጠይቅና ከሰነድ ፍተሻ ማየት እንደተቻለው መምህሮቻቸው የተከታታይ ምዘና በአግባቡ ተጠቅመው ተማሪዎቻቸውን እንደማይመዝኑ ማረጋገጥ ችሏል፡፡

Murphy (1996፡ 75) እና ICDR (2004፣ 5) ተከታታይ ምዘና ዋና ዋና ዓላማዎች ተማሪው በሚማረው ትምህርት ዙሪያ የሚያሳየውን ጠንካራና ደካማ ጎን ለመለየትና እገዛ ለማድረግ፣ አስፈላጊውን ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት፣ ስለተማሪው ሁኔታ አስፈላጊውን መረጃ ለሚመለከተው ክፍል ለማቅረብ ፣ተማሪው በክፍል ውስጥ ሲማር ከትምህርቱ ጋር በተያያዘ የሚያጋጥመውን ችግር ለመለየት፣ እንደሆነ ያስቀምጣሉ፡፡

### ሰንጠረዥ 7፡- ከምዘና ስልቶች ጋር የተገናኘ የጽሑፍ መጠይቅ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ

| ተ.ቁ | የተከታታይ ምዘና ስልቶች | በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ | | | | | | አማካይ ውጤት (X1) | በየጭላና በሳቃ አንደኛ ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ | | | | | | አማካይ ውጤት (X2) | ልይይት (x1-x2) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | አይጠቀሙም | | | ሁል ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | አይጠቀሙም | | | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | % | በቁጥር | % | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | | |
| 1 | የቃል ጥያቄዎች | 50 | 78.1 | 10 | 15.6 | 4 | 6.2 | 2.72 | 53 | 82.8 | 7 | 10.9 | 4 | 6.2 | 2.77 | -0.05 |
| 2 | የቤት ሥራ | 24 | 37.5 | 40 | 62.5 | - | - | 2.38 | 55 | 85.9 | 9 | 14.06 | - | - | 2.86 | -0.48 |
| 3 | ምልከታ | 14 | 21.8 | 28 | 43.7 | 22 | 34.3 | 1.88 | 9 | 14.06 | 39 | 60.9 | 16 | 25 | 1.89 | -0.01 |
| 4 | ሙከራ/ፈተና/ | 8 | 12.5 | 56 | 87.5 | - | - | 2.13 | 8 | 12.5 | 56 | 87.5 | - | - | 2.13 | 0 |
| 5 | የግል ሥራ/ፕሮጀክት/ | - | - | 60 | 93.7 | 4 | 6.3 | 1.94 | - | - | 4 | 6.3 | 60 | 93.7 | 1.06 | 0.88 |
| 6 | የቡድን ሥራ/ፕሮጀክት/ | - | - | 10 | 15.6 | 54 | 84.4 | 1.16 | - | - | 20 | 31.3 | 44 | 68.8 | 1.31 | -0.15 |

ከላይ ከሰንጠረዥ 7 መረዳት እንደሚቻለው አማራ ክልላዊ መንግስት ስር የሚገኙት የማዕርነትና የሳቃ በየጥናቱ ተተኳሪ መምህራኑ የክፍል ሥራ 60 (93.8%)ና ከተማሪ ፊት እየወጡ ማቅረብ 34 (53.1%) ሁል ጊዜ ይተገበራሉ፤ ግለ ግምገማ 54 (84.37)ና የጓደኛ ለጓደኛ (የቢጤ ለቢጤ) ምዘና 48 (75%) አልፎ አልፎ ሲተገበሩ፤ የተማሪና የመምህር ውይይት 42 (65.6%)፣ ሰነደ ትምህርት (ፖርትፎልዮ) 40 (62.5%) እንደማይተገበሩ ተማሪዎቹ ከሰጡት ምላሽ መመልከት ተችሏል፡፡ ከተማሪዎቹ ምላሽ በተጨማሪም በሰነድ ፍተሻና በምልከታ ተረጋግጧል፡፡

እንዲሁም በትግራይ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የየጭላና የፊናርዋ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ፣ መምህሮቻቸው የቃል ጥያቄዎች 53 (82.8%) ና የቤት ሥራ 55 (85.9%) የሚሆኑት ሁል ጊዜ ይተገብራሉ ሲሉ፤ ምልከታ 39(60.9%)ና ሙከራ/ፈተና/ 56(87.5%) ተማሪዎች አልፎ አልፎ፤ እንዲሁም የግል ሥራ/ፕሮጀክት/ 60 (93.7%)፣ የቡድን ሥራ /ፕሮጀክት/ 44 (68.8%) የሚሆኑት ተማሪዎች አይጠቀሙም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

ስለሆነም ከፍ ሲል ከቀረበው ትንተና መረዳት የሚቻለው ሁሉም ትምህርት ቤቶች የቃል ጥያቄዎች፣ ሙከራ/ፈተና/፣ ምልከታና የቤት ሥራ በመተግበር በኩል ተመሳሳይ ቢሆኑም፤ የግል ሥራ /ፕሮጀክት/ በመተግበር የማዕርነትና የሳቃ መምህራን የተሻሉ መሆናቸውን ማየት ይቻላል፡፡ የአማካይ ውጤት የልይይት መጠን (0.88) የሚያሳየው እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተሻሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በገጽ 65 ከቀረበው የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ መረጃ ትንተና ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ሰንጠረዥ 8 ፡- የተከታታይ ምዘና አሰጣጥ የጊዜ ድግግሞሽ በተመለከተ

| ተ.ቁ | የተከታታይ ምዘና ስልቶች | በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ | | | | | | አማካይ ውጤት (X1) | በየጭላና በፌናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ | | | | | | አማካይ ውጤት (X2) | ልይይት (x1-x2) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | አይጠቀሙም | | | ሁል ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | አይጠቀሙም | | | |
| | | በቁ. | % | በቁ | % | በቁ. | % | | በቁ | % | በቁ | % | በቁ. | % | | |
| 7 | የመምህር ተማሪ ውይይት | 10 | 15.6 | 12 | 18.8 | 42 | 65.6 | 1.5 | - | - | - | - | 64 | 100 | 1 | 0.5 |
| 8 | ሰነደ ትምህርት /ፖርትፎልዮ/ | - | - | 24 | 37.5 | 40 | 62.5 | 1.38 | - | - | - | - | 64 | 100 | 1 | 0.38 |
| 9 | ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ | 34 | 53.1 | 16 | 25 | 14 | 21.9 | 2.31 | 38 | 59.4 | 26 | 40.6 | - | - | 2.59 | -0.28 |
| 10 | ግለ ግምገማ | 10 | 15.6 | 54 | 84.4 | - | - | 2.16 | 54 | 84.4 | 10 | 15.6 | - | - | 2.84 | -0.68 |
| 11 | የጓደኛ ለጓደኛ /የቢጤ/ ምዘና | - | - | 48 | 75 | 16 | 25 | 1.75 | 4 | 6.3 | 60 | 93.8 | - | - | 2.06 | -0.31 |
| 12 | የክፍል ሥራ | 60 | 93.8 | 4 | 6.2 | - | - | 2.94 | 60 | 93.8 | 4 | 6.2 | - | - | 2.94 | 0 |

ከላይ ከሰንጠረዥ 8 ማየት የሚቻለው በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት በአማራና በትግራይ ክልላዊ መንግስት የሚገኙት የማዕርነት፣ የሳቃ፣ የየጭላና የፌናርዋ ተማሪዎች መምህሮቻቸው የክፍል ሥራ 60 (93.8%) ሁል ጊዜ የሚተገብሩ መሆናቸውን ትንተናው ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል በትግራይ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የየጭላና የፌናርዋ ተማሪዎች ግለ ግምገማ 54 (84.37%) የሚሆኑት ሁልጊዜ ይተገብራሉ ሲሉ፤ 60 (93.75%) የሚሆኑት ተማሪዎች ደግሞ የጓደኛ ለጓደኛ/ የቢጤ ምዘና አለፎ አልፎ ይተገብራሉ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

በአንጻሩ በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የሰጡት መልስ በተመሳሳይ የመምህር ተማሪ ውይይትና ሰነደ ትምህርት (ፖርቲፎልዮ) ግን እንደምዘና ስልት የማይተገብሩት መሆናቸውን የመረጃ ትንተናው ያሳያል፡፡ አማካይ ውጤት የልይይት መጠን የሚያሳየውም ተቀራራቢ ነው፡፡

## 4.3 ከመምህራን ጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

በዚህ ንኡስ ምዕራፍ ስር በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ (የማዕርነትና የሳቃ) እና በትግራይ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ (የየጭላና የፌናርዋ) አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አራቱም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸውን ግንዛቤ፣ የአተገባበራቸው ሁኔታ በተመለከተ ከጽሑፍ መጠይቁ የተገኘ መረጃ ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### ሰንጠረዥ 9 ፡- መምህራን የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ተማሪዎችን ለመመዘን ምን ያህል እንደሚጠቀሙባቸው የሚያሳይ

| ተ.ቁ | የተከታታይ ምዘና ስልቶች | በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | | | አማካይ ውጤት (X1) | በየጭላናና በፊናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | | | አማካይ ውጤት (X2) | ልይይት (x1-x2) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | አልጠቀምም | | | ሁል ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | አልጠቀምም | | | |
| | | በቁ | % | በቁ. | % | በቁ | % | | በቁ | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | | |
| 1 | የቃል ጥያቄዎች | 2 | 100 | | | | - | 3 | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | 0 |
| 2 | የቤት ሥራ | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | 0 |
| 3 | ምልከታ | - | - | 2 | 100 | - | - | 2 | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | -1 |
| 4 | ሙከራ/ፈተና/ | - | - | 2 | 100 | - | - | 2 | - | - | 2 | 100 | - | - | 2 | 0 |
| 5 | የግል ሥራ/ፕሮጀክት/ | - | - | - | - | 2 | 100 | 1 | - | - | 2 | 100 | - | - | 2 | -1 |
| 6 | የቡድን ሥራ/ፕሮጀክት/ | - | - | - | - | 2 | 100 | 1 | - | - | 2 | 100 | - | - | 2 | -1 |
| 7 | የመምህር ተማሪ ውይይት | - | - | - | - | 2 | 100 | 1 | - | - | 2 | 100 | - | - | 1.5 | -0.5 |
| 8 | ሰነደ ትምህርት/ፖርትፎልዮ/ | - | - | - | - | 2 | 100 | 1 | - | - | - | - | 2 | 100 | 1 | 0 |
| 9 | ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ | 2 | 100 | | | | - | 3 | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | 0 |
| 10 | ግለ ግምገማ | - | - | 1 | 50 | 1 | 50 | 1.5 | 2 | 100 | - | - | - | - | 2 | -0.5 |
| 11 | የጓደኛ ለጓደኛ /የቢጤ/ ምዘና | - | - | - | - | 2 | 10 | 1 | - | - | 2 | 100 | - | - | 2 | -1 |
| 12 | የክፍል ሥራ | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | 0 |

ከላይ ከሰንጠረዥ 9 መመለከት የሚቻለው በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የማዕርነትና የሳቃ መምህራን የቃል ጥያቄዎች 2 (100%)፣ ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ 2 (100%)ና የክፍል ሥራ 2 (100%) ሁል ጊዜ ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን እንደሚጠቀሙባቸው ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል ምልከታ 2 (100%)ና ሙከራ(ፈተና) 2 (100%) አልፎ አልፎ የሚጠቀሙዋቸው የምዘና ስልቶች መሆናቸውን መመልከት ይቻላል፡፡

በአንፃሩ የግል ስራ 2 (100%)፣ የቡድን ስራ 2 (100%)፣ የመምህር ተማሪ ውይይት 2 (100%)፣ ሰነድ ትምህርት (ፖርቲፎሊዮ) 2 (100%) እና የጓደኛ ለጓደኛ (የቢጤ) 2 (100%) ምዘና በተከታታይ የምዘና ሂደት እንደማይጠቀሙባቸው ጠቁመዋል፡፡

በሌላ በኩል በትግራይ ክልላዊ መንግስት ስር የሚገኙ የየጭላና የፊናርዋ መምህራን የቃል ጥያቄዎች ፣ 2 (100%) የቤት ስራ 2 (100%)፣ ምልከታ ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ 2 (100%)፣ ግለ ግምገማ 2 (100%) እና የክፍል ስራ 2 (100%) ሁሉ ጊዜ የሚጠቀሙባቸው የተከታታይ ስልቶች መሆናቸው ሲገልፁ፣ እንዲሁም ሙከራ(ፈተና) 2 (100%) የግል ስራ 2 (100%) የቡድን ስራ 2 (100%)፣ የመምህር ተማሪ ውይይት 2 (100%)፣ እና የጓደኛ ለጓደኛ (ቢጤ) ምዘና 2 (100%) አልፎ አልፎ የሚጠቀሙባቸው መሆናቸው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ከላይ ከቀረበው የመረጃ ትንተና መረዳት የሚቻለው በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የቃል ጥያቄዎች፣ የቤት ስራ፣ ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብና የክፍል ስራ ሁሉ ጊዜ የሚጠቀሙባቸው መሆናቸው ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ምልከታና ግለ ግምገማ በመጠቀም በኩል ግን የየጭላና የፊናርዋ መምህራን የተሻሉ መሆናቸው ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም የግልና የቡድን ስራ ፕሮጀክት የመምህር ተማሪ ውይይ እና የቢጤ ምዘና ዘልፎ አልፎ በመጠቀም የየጭላና የፊናርዋ መምህራን የተሻሉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በምልከታና በሰነድ ፍተሻም ተረጋግጧል፡፡

**ሰንጠረዥ 10 ፡- የተከታታይ ምዘና አጠቃላይ መርህን በተመለከተ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰጡት ምላሽ**

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X1) | በየጭላናና በፌናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X2) | ልይይት (x1-x2) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | | |
| | | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | | |
| 1 | ተከታታይ ምዘና የመማር ማስተማሩ ሂደት አካል ነው፡፡ | 2 | 100 | - | - | - | - | - | - | 4 | 2 | 100 | - | - | - | - | - | - | 4 | 0 |

ከላይ ከሰንጠረዥ 10 ማየት የሚቻለው በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን በተራ ቁጥር 1 “ተከታታይ ምዘና የመማር ማስተማሩ ሂደት አካል አካል ነው” ለሚለው ጥያቄ ሁሉም መምህራን (100%) አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከላይ ከቀረበው የመረጃ ትንተና መረዳት የሚቻለው ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የተከታታይ ምዘና መርህን በተመለከተ ጥሩ ግንዛቤ ያላቸው መሆናቸውን በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ አማካይ ውጤት ቡድን (X1) እና ቡድን (X2) እኩል (4) በመሆኑ የልይይት መጠኑ ዜሮ (0) ሆኗል፡፡ ይህ ማለት በሁለቱም ቡድኖች መካከል ምንም ዓይነት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡

## ሰንጠረዥ 11. ፦ የተከታታይ ምዘና አስፈላጊነት የመምህራን ምላሽ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X1) | በየጭላናና በፊናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X2) | ልይይት (x1-x2) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | | |
| | | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | | |
| 2 | ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ ተማሪዎች መማር የሚገባቸውን የትምህርት ይዘቶች ለመወሰን ይረዳል፡፡ | 1 | 50 | 1 | 50 | - | - | - | - | 3.5 | | | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | 0.5 |
| 3 | ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ የሚጠቅመው ለአስተማሪው ብቻ ነው፡፡ | - | - | - | - | - | - | 2 | 100 | 1 | - | - | - | - | 2 | 100 | - | - | 2 | -1 |
| 4 | ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለመለየትና ለመርዳት ከተከታታይ ምዘና የሚገኝ መረጃ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ | 2 | 100 | - | - | - | - | - | - | 4 | 2 | 100 | - | - | - | - | - | - | 4 | 0 |

ከሰንጠረዥ 11 ማየት የሚቻለው በአማራ ክልላዊ መንግስት ስር የሚገኙ የማዕርነትና የሳቃ መምህራን በተራ ቁጥር 2 ለቀረበው ጥያቄ የመስማማት ደረጃቸው ቢለያይም 2 (100%) አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ፣ በትግራይ ክልላዊ መንግስት ስር የሚገኙ የየጭላና የፌናርዋ መምህራን ሁለቱም (100%) አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ነገር ግን የልይይት መጠን= (X1-X2) ማለትም (3.5-3=0.5) የሚያመለክተው ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ ተማሪዎች መማር የሚገባቸውን የትምህርት ይዘቶች ከመወሰን አንጻር የማዕርነትና የሳቃ መምህራን የተሻሉ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

በተጨማሪ "ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ የሚጠቅመው ለአስተማሪው ብቻ ነው" የሚለውን ጥያቄ የማዕርነትና የሳቃ መምህራን ሁለቱም (100%) አሉታዊ መልስ ሲሰጡ፣ በተመሳሳይ የየጭላና የፌናርዋ መምህራንም 2 (100%) አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የልይይት መጠን (-1) የሚያሳየው ግን የማዕርነትና የሳቃ መምህራን የተሻሉ መሆናቸውን ይጠቁማል፡፡

በተራ ቁጥር 3 ለቀረበው ጥያቄ የሁለቱም ክልሎች የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የማዕርነትና የሳቃ 2 (100%) እና የየጭላና የፌናርዋ 2 (100%) አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ተመሳሳይ በመሆኑም የልይይት መጠኑ ዜሮ (0) ሆኗል፡፡

ስለሆነም ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የተከታታይ ምዘና አስፈላጊነት በተመለከተ ምንም ዓይነት ልዩነት አለመኖሩን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ከመምህራኑ ምላሽ ለመረዳት የሚቻለው ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ የትምህርት ይዘት ለመወሰን፣ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ለመስጠትና ለብዙ ጉዳዮች እንደሚጠቅም መረዳት ይቻላል፡፡

## ሰንጠረዥ 12 ፡- በተከታታይ ምዘና እቅድ ማውጣትና በእቅዱ መሰረት መስራት የሚኖረውን ሚና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰጡት ምላሽ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X1) | በየጭላናና በፊናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X2) | ልይይት (x1-x2) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | | |
| | | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | በቁ | % | | |
| 5 | በተከታታይ ምዘና ሂደት ዕቅድ ማውጣት የመጀመሪያ ተግባር ነው፡፡ | 2 | 100 | - | - | - | - | - | - | 4 | 2 | 100 | - | - | - | - | - | - | 4 | 0 |
| 6 | የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን በተከታታይ ምዘና ዕቅድ ውስጥ ማካተት በራሱ በቂ ነው፡፡ | - | - | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | 1 | 50 | 1 | 50 | - | - | - | - | 3.5 | -0.5 |
| 7 | ተከታታይ ምዘና ተማሪዎችን እንደየቋንቋ ችሎታቸው ለመለየት ያስችላል፡፡ | 2 | 100 | - | - | - | - | - | - | 4 | - | - | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | 1 |
| 8 | የተከታታይ ምዘና በክፍል ውስጥ በመተግበር መምህራን የተማሪዎችን ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ ይጠቅማቸዋል ፡፡ | 2 | 100 | - | - | - | - | - | - | 4 | - | - | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | 1 |
| 9 | ብዙ ተማሪዎች ባሉበት መማሪያ ክፍል ውስጥ ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል፡፡ | - | - | - | - | 2 | 100 | - | - | 2 | - | - | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | -1 |

ከሰንጠዥ 12 ማየት የሚቻለው የማዕርነትና የሳቃ መምህራን በተራ ቁጥር 5 ለቀረበው ጥያቄ 2 (100%) አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ፣ በተመሳሳይ የየጭላና የፊናርዋ መምህራንም ሁለቱም አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የልይይት መጠን (X1-X2=0) የሚያመለክተውም ምንም ዓይነት ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ እንዲሁም በተራ ቁጥር 6 ለተሰጠው ጥያቄ የሁለቱም ክልሎች መምህራን ተመሳሳይ መልስ 100% አሉታዊ መልስ በመስጠታቸው የልይይት መጠን ዜሮ ሆኗል፡፡

በተራ ቁጥር 7 ለቀረበው ጥያቄ የማዕርነትና የሳቃ መምህራን ሁለቱም አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ፣ እንዲሁም የየጭላና የፊናርዋ መምህራንም ሁለቱም አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በተመሳሳይ የልይይት መጠን (1) በመሆኑ በመካከላቸው ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም በተራ ቁጥር 8 ለቀረበው ጥያቄ የሁለቱም ክልሎች መልስ አዎንታዊ መልስ ቢሰጡም፣ የልይይት መጠን (X1-X2=1) በመሆኑ በመካከላቸው ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ ስለዚህም የማዕርነትና የሳቃ መምህራን ተከታታይ ምዘና በመጠቀም ለተማሪዎች ቁጥጥር በማድረግ በኩል የተሻሉ ቢሆኑም፣ በክፍል ውስጥ በመተግበር ግን የየጭላና የፊናርዋ መምህራን የተሻሉ መሆናቸው በተደረገው ምልከታ መመልከት ተችሏል፡፡

በተራ ቁጥር 9 "ብዙ ተማሪዎች ባሉበት መማሪያ ክፍል ውስጥ ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል" የሚል ጥያቄ በአማራ ክልላዊ መንግስት ስር የሚገኙት የማዕርነትና የሳቃ መምህራን ሁለቱም (100%) አሉታዊ መልስ ሲሰጡ፣ በአንጻሩ በትግራይ ክልላዊ መንግስት ስር የሚገኙት ደግሞ 2 (100%) አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከላይ ከቀረበው ትንተና የሚያሳየው ብዙ ተማሪዎች ባሉበት መማሪያ ክፍል ውስጥ ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረግ በኩል የየጭላና የፊናርዋ መምህራን የተሻሉ መሆናቸውን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ የልይይት መጠን ጠቋሚ (X1-X2=-1) የሚያመለክተውም ልዩነት መኖሩን ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ምላሽ መረዳት የሚቻለው ምንም እንኳን በዕቅድ የተመራ ተከታታይ ምዘና እንተገብራለን ቢሉም ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅና ከምልከታ ለማመሳከር እንደተቻለው ዕቅድ እንደማያወጡ መመልከት ተችሏል፡፡ በተለይ በሳቃ ትምህርት ቤት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በጣም ጥቂት ማለትም 32 ብቻ በመሆናቸው ይህንን የመምህራን ምክንያት አግባብነት ያለው አይመስልም፡፡

## ሰንጠረዥ 13 ፡- በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎች የሚኖራቸውን ሚና በተመለከተ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X1) | በየጭላናና በፌናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X2) | ልይይት (x1-x2) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አላስማማም | | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አላስማማም | | | |
| | | በቁ | በ % | በቁ | በ % | በቁ | በ % | በቁ | በ % | | በቁ | በ % | በቁ | በ % | በቁ | በ % | በቁ | በ % | | |
| 10 | ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በጓደኞቻቸው ሥራዎች ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ | - | - | - | - | 1 | 50 | 1 | 50 | 1.5 | - | - | - | - | - | - | 2 | 100 | 1 | 0.5 |
| 11 | በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው መገምገም ይችላሉ፡፡ | - | - | - | - | - | - | 2 | 100 | 2 | 2 | 100 | - | - | - | - | - | - | 4 | -2 |
| 12 | ተከታታይ ምዘና መምህራን ብቸኛ የውሳኔ ሰጭ አካል እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ | 1 | 50 | 1 | 50 | - | - | - | - | 3.5 | 2 | 100 | - | - | - | - | - | - | 4 | -0.5 |
| 13 | በተከታታይ ምዘና ሂደት የመመዘኛ መስፈርቶችን ማውጣት ያለባቸው መምህራን ብቻ ናቸው፡፡ | - | - | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | - | - | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | 0 |

ከሰንጠረዥ 13 ማየት የሚቻለው በአማራ ክልላዊ መንግስት ስር ያሉት የማዕርነትና የሳቃ መምህራን በተራ ቁጥር 10 የቀረበውን ጥያቄ 2 (100%) አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ በተመሳሳይ የትግራይ ክልል ትምህርት ቤቶች የየጭላና የፌናርዋ ሁለቱም (100%) መምህራንም አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይሁን እንጂ የልይይት መጠን ጠቋሚ (X1-X2=0.5) የሚያሳው ውስን የሆነ ልዩነት መኖሩን ነው፡፡

በተመሳሳይ የጥያቄ ቁጥር 11 ሁሉም የማዕርነትና የሳቃ መምህራን (100%) አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ በአንጻሩ ሁለቱም የትግራይ ክልል መምህራን (100%) አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አማካይ ውጤት (X1-X2= ልይይት)፣ (2-4=-2) የሚያሳየው በሁለቱም ቡድኖች መካከል ሰፊ ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡

ስለሆነም ተማሪዎች በራሳቸው እንዲመዝኑ በማድረግ በኩል የየጭላና የፌናርዋ መምህራን የተሻሉ መሆናቸውን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

በተራ ቁጥር 12 ለቀረበው ጥያቄ ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን አዎንታዊ መልስ በመስጠት በተከታታይ ምዘና ሂደት መምህራን ብቸኛ ውሳኔ ሰጪ መሆን የለባቸውም ብሏል፡፡

በተራ ቁጥር 13 "በተከታታይ ምዘና ሂደት የመመዘና መስፈርቶችን ማውጣት ያለባቸው መምህራን ብቻ ናቸው" የሚለው ጥያቄ በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን አዎንታዊ ምላሽ መስጠታቸው ከሰንጠረዡ መመልከት ይቻላል፡፡

ይሁን እንጂ በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ መምህራን የመመዘኛ መስፈርቶችን ማውጣት ያለባቸው መምህራን ብቻ አይደሉም ቢሉም፤ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ፣ ከምልከታና ከቃለ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ ግን የተከታታይ ምዘና ዕቅድ የሚያወጡት መምህራን እንጂ ተማሪዎች መሳተፋቸውን የሚያሳይ መረጃ ሊገኝ አልቻለም፡፡

## ሰንጠረዥ 14 ፡- የተከታታይ ምዘና ጥቅምና ዓላማ በተመለከተ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰጡት ምላሽ

| ተ. ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X1) | በየጭላናና በፊናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X2) | ልይይት (x1-x2) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም እስማማለሁ | | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም እስማማለሁ | | | |
| | | በቁ | በ% | በቁ | በ% | በቁ | በ% | በቁ | በ% | | በቁ | በ% | በቁ | በ% | በቁ | በ% | በቁ | በ% | | |
| 14 | ከተለምዷዊው(በፅሑፍ ፈተና መልክ ብቻ ከሚቀርበው) የምዘና ስርዓት ይልቅ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ያነሳሳል፡፡ | - | - | 1 | 50 | 1 | 50 | - | - | 2.5 | 2 | 100 | - | - | - | - | - | - | 4 | -1.5 |
| 15 | ተከታታይ ምዘና ተማሪዎችን ትምህርታቸውን ተነቃቅተው እንዲማሩ ያደርጋቸዋል ብዬ አስባለሁ፡፡ | - | - | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | - | - | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | 0 |
| 16 | የተከታታይ ምዘና ትኩረት ተማሪዎችን ጎበዝ ወይም ደካማ ናቸው ብሎ ለመፈረጅ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ | - | - | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | - | - | - | - | 2 | 100 | - | - | 2 | 1 |
| 17 | ከተለምዷዊው (በፅሑፍ ፈተና መልክ ብቻ ከሚቀርበው) የምዘና ስርዓት ይልቅ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን በተሻለ ሁኔታ ለመለየት ያስችላል፡፡ | 2 | 100 | - | - | - | - | - | - | 4 | 2 | 100 | - | - | - | - | - | - | 4 | 0 |
| 18 | የተከታታይ ምዘና ትኩረት በአብዛኛውን ጊዜ በውጤት ላይ እንጂ በሂደት ላይ አይደለም፡፡ | - | - | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | - | - | - | - | 2 | 100 | - | - | 2 | 1 |

በተራ ቁጥር 14 ለቀረበላቸው ጥያቄ በአማራ ክልላዊ መንግስት የማዕርነትና የሳቃ መምህራን ከተለምዱዊው የምዘና ስልት ይልቅ የተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ያነሳሳል አንዱ (50%) አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ፣ አንዱ (50%) አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በአንጻሩ የየጭላና የፈናርዋ 2 (100%) መምህራን ደግሞ ከተለምዱዊው የምዘና ስልት ይልቅ የተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ያነሳሳል ይላሉ፡፡ የልይየት መጠን (X1-X2=-1.5) የሚያሳየው በምዘና በኩል ሰፊ የሆነ ልዩነት እንዳላቸው፡፡

በአጠቃላይ የተከታታይ ምዘና ዓላማ ተረድተው በመተግበር በኩል የየጭላና የፈናርዋ መምህራን የተሻሉ መሆናቸውን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

በሌላ መልኩም በተራ ቁጥር 15 ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁሉም መምህራን ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች ትምህርታቸውን ተነቃቅተው እንዲማሩ ያደርጋቸዋል ብለዋል፡፡ በሁለቱም የጥናቱ ተተኳሪ ክልሎች ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የልይይት መጠን (0) የሚያሳየው ይኸው ነው፡፡

በተራ ቁጥር 16 “የተከታታይ ምዘና ትኩረት ተማሪዎችን ጎበዝ ወይም ደካማ ናቸው ብሎ ለመፈረጅ እንደሆነ ይሰማኛል” ለሚለው ጥያቄ የማዕርነትና የሳቃ 2 (100%) መምህራን አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ ቀሪዎቹ የየጭላና የፈናርዋ 2 (100%) መምህራን አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ “ከተለምዱዊው (በፅሑፍ ፈተና መልክ ብቻ ከሚቀርበው) የምዘና ስርዓት ይልቅ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን በተሻለ ሁኔታ ለመለየት ያስችላል” ለሚለው ጥያቄ ሁሉም መምህራን ያለምንም ልዩነት አዎንታዊ ምላሽ ሰጥዋል፡፡ በተራ ቁጥር 18 ለቀረበው ጥያቄም ሁለቱም የማዕርነትና የሳቃ 2 (100%) መምህራን የተከታታይ ምዘና ትኩረት በአብዛኛውን ጊዜ በውጤት ላይ እንጂ በሂደት ላይ አይደለም ሲሉ፤ በአንጻሩ የየጭላና የፈናርዋ 2 (100%) መምህራን ደግሞ የተከታታይ ምዘና ትኩረት በውጤት ሳይሆን በሂደት መሆን አለበት ይላሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው መምህራኑ የተከታታይ ምዘና ጥቅም ጠንቅቀው ቢረዱትም በዓላማው ላይ ግን ልዩነት አላቸው፡፡ የማዕርነትና የሳቃ መምህራን የተከታታይ ምዘና ትኩረት በውጤት እንጂ በሂደት ማተኮር የለበትም ሲሉ፤የየጭላና የፈናርዋ መምህራን ግን በሂደት ያተኩራሉ፡፡ ስለዚህ የትግራይ ክልላዊ መንግስት መምህራን የተከታታይ ምዘና በመረዳት በኩል የተሻሉ መሆናቸው መረዳት ይቻላል፡፡

## ሰንጠረዥ 15 ፡- በአራቱም ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ምጋቤ ምላሽ ወይም አስተያየት አሰጣጥ በተመለከተ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X1) | በየጭላናና በፊናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | | | | | አማካይ ውጤት (X2) | ልይይት (x1-x2) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | | | |
| | | በቁ | በ% | በቁ | በ% | በቁ | በ% | በቁ | በ% | | በቁ | በ% | በቁ | በ% | በቁ | በ% | በቁ | በ% | | |
| 19 | በተከታታይ ምዘና ሂደት ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ /አስተያየት/ ሲሰጥ ትክክለኛ እና ስህተት መልሶችን በመንገር ላይ ብቻ ማተኮር አለበት፡፡ | - | - | - | - | 2 | 100 | - | - | 2 | - | - | - | - | 2 | 100 | - | - | 2 | 0 |
| 20 | በተከታታይ ምዘና ሂደት ለተማሪዎች ምጋቤምላሽ /አስተያየት/ መሰጠት ያለበት በመምህራን እንጂ በተማሪዎች መሆን የለበትም፡፡ | - | - | 2 | 100 | - | - | - | - | 3 | - | - | - | - | 2 | 100 | - | - | 2 | 1 |
| 21 | በተከታታይ ምዘና ሂደት ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ /አስተያየት/ ማተኮር ያለበት ተማሪዎች የሚያሳዩትን ደካማ ጎን ለማስተካከል ነው፡፡ | 1 | 50 | 1 | 50 | - | - | - | - | 3.5 | 2 | 100 | - | - | - | - | - | - | 4 | -0.5 |

በተራ ቁጥር 19 ለቀረበው ጥያቄ የሁሉም መምህራን ምላሽ በተከታታይ ምዘና ሂደት ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ /አስተያየት/ ሲሰጥ ትክክለኛ እና ስህተት መልሶችን በመንገር ላይ ብቻ ማተኮር የለበትም፡፡

በተራ ቁጥር 20 ለቀረበው ጥያቄ በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ 2 (100%) መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ /አስተያየት/ መሰጠት ያለበት በመምህራንና በተማሪዎች መሆን አለበት ብለዋል፤በትግራይ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የማዕርነትና የሳቃ መምህራን ደግሞ 2 (100%) አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በመጨረሻ በተራ ቁጥር 21 ለቀረበው ጥያቄ የየጭላና የፈናርዋ 2 (100%) መምህራን "በተከታታይ ምዘና ሂደት ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ /አስተያየት/ ማተኮር ያለበት ተማሪዎች የሚያሳዩትን ደካማ ጎን ለማስተካከል ነው" ለሚለው ተተኳሪ መምህራን ግን መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ በአንጻሩ ግን ተተኳሪ ሁለቱም የማዕርነትና የሳቃ መምህራን "በተከታታይ ምዘና ሂደት ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ /አስተያየት/ ማተኮር ያለበት ተማሪዎች የሚያሳዩትን ደካማ ጎን ለማስተካከል መሆን የለበትም ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት የጥያቄዎች ምላሽ ለመረዳት የሚቻለው በትግራይ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ /አስተያየት/ ሲሰጥ ትክክለኛ እና ስህተት መልሶችን በመንገር ላይ ማተኮር ብቻ ሳይሆን ገንቢ የሆኑ አስተያየቶችም በመስጠት መሆን እንዳለበት ነው፡፡ ምጋቤ ምላሽ መሰጠት ያለበትም በመምህራንና በተማሪዎች መሆን እንዳለበትና ይህ ደግሞ ተማሪዎች በራሳቸው ራሳቸውን መገምገም እንዳለባቸው ነው፡፡

## ሰንጠረዥ 16፡- የተከታታይ ምዘና ተግባራዊነትን በተመለከተ ተተኳሪ መምህራን የሰጡት ምላሽ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | አማካይ ውጤት (X1) | በየጭላናና በፊናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የሰጡት ምላሽ | | | | አማካይ ውጤት (X2) | ልይይት (x1-x2) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይደለም | | | አዎ | | አይደለም | | | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | | |
| 1 | በመማር ማስተማሩ ሂደት፣ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘናን ይጠቀማሉ? | 2 | 100 | - | - | 2 | 2 | 100 | - | - | 2 | 0 |
| 2 | በተራ ቁጥር 1 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ ተከታታይ ምዘናን በትምህርት ዕቅድዎ ውስጥ ታሳቢ በማድረግ ያካትታሉ? | 1 | 50 | 1 | 50 | 1.5 | 2 | 100 | - | - | 2 | -0.5 |
| 3 | በተራ ቁጥር 2 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ የሚከተሉትን ተግባራት በዕቅድዎ ውስጥ በግልጽ ያስቀምጣሉ? | | | | | | | | | | | |
| | ሀ. የተከታታይ ምዘናውን ዓላማ | 1 | 50 | 1 | 50 | 0.5 | - | - | 2 | 100 | 1 | -0.5 |
| | ለ.የተከታታይ ምዘናውን ጊዜ | 1 | 50 | 1 | 50 | 0.5 | - | - | 2 | 100 | 1 | -0.5 |
| | ሐ.የተከታታይ ምዘናውን ዘዴ | 1 | 50 | 1 | 50 | 0.5 | 2 | 100 | - | - | 2 | 0 |

ከሰንጠረዥ 16 በተራ ቁጥር 1ና 2 ለቀረቡት ጥያቄዎች በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የሰጡት ምላሽ 1 (50%) አዎ ሲሉ፣ 1 (50%) ደግሞ አይደለም የሚል መልስ ስጥተዋል፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተከታታይ ምዘና ዕቅድ እንደማያወጡ መመልከት ተችሏል፡፡ በአንጻሩ በየጭላና በፊናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የሰጡት ምላሽ 2 (100%) አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በዕቅዳቸውም የተከታታይ ምዘናውን ዓላማ፣ ጊዜና የምዘናውን ዘዴ ደግሞ እንደሚያካትቱ ጠቁመዋል፡፡

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ተግባራት በአግባቡ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የመከታታያ /የመመዝገቢያ/ ቅጾች ይጠቀማሉ? | 2 | 100 | - | - | 2 | 2 | 100 | - | - | 2 | 0 |
| 5 | በተራ ቁጥር 4 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ተግባራት ለመከታተል /ለመመዝገብ/ የሚጠቀሙበት ቅጽ ከየት ያገኛሉ?<br><br>ሀ. ትምህርት ቤቱ አዘጋጅቶ ይሰጠናል | | | | | | | | | | | |
| | ለ. በትምህርት ክፍል ደረጃ እናዘጋጃለን | 1 | 50 | - | - | 0.5 | 2 | 100 | - | - | 2 | 0 |
| | ሐ.በራሴ አዘጋጃለሁ | 1 | 50 | - | - | 0.5 | - | - | - | - | | |
| 6 | ለተማሪዎችዎ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ? | 2 | 100 | - | - | 2 | - | - | - | - | | |
| 7 | በተራ ቁጥር 6 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ ምጋቤ ምላሽ /አስተያየት/ በሚሰጡበት ጊዜ የሚያተኩሩት በምን ላይ ነው? | | | | | | 2 | 100 | - | - | 2 | |
| | ሀ. ትክክለኛውን መልስ በመንገር | 1 | 50 | | | 0.5 | 1 | 50 | | | 0.5 | 0 |
| | ለ.ትክክለኛውን መልስ በመንገርና ተማሪው ማዳበር ስለሚገባው ገንቢ አስተያየት በመስጠት | 1 | 50 | | | 0.5 | 1 | 50 | | | 0.5 | 0 |
| 8 | ለተማሪዎችዎ ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡት መቼ መቼ ነው? | | | | | | | | | | | |
| | ሀ. በእያንዳንዱ የምዘና ተግባር ላይ | | | | | | | | | | | |
| | ለ.ፈተናዎችን፣ የግል ስራዎችንና የቡድን ስራዎችን በምመልስበት ጊዜ | 2 | 100 | | | 2 | 2 | 100 | | | 2 | 0 |

የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ተግባራት በአግባቡ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የመከታታያ /የመመዝገቢያ/ ቅጾች አንድ መምህር በራሳቸው አዘጋጅተው እንደሚመዝኑ አስቀምጠዋል፡፡ በተራ ቁጥር 6፣ 7ና 8 ከምጋቤ ምላሽ ጋር የተገናኙ ጥያቄዎች የማዕርነትና የፊናርዋ 2 (100%) መምህራን ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡ ቢሆንም ሁለቱ ትክክለኛውን መልስ በመንገር ብቻ ሲሆን፣ ሁለቱ (100%) የየጭላና የሳቃ መምህራን ደግሞ ገንቢ የሆነ አስተያየት በመስጠትም ጭምር መሆኑን ነው፡፡ ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡትም ፈተናዎችን፣ የግልና የቡድን ሥራዎችን በሚመልሱበት ጊዜ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ሁሉም መምህራን ተከታታይ ምዘና እንደሚያዘጋጁ እና በምዘናቸው ሂደትም የምዘናውን ዓላማ፣ የምዘናውን ጊዜና የምዘናውን ዘዴ እንደሚጠቀሙ የገለጹ ሲሆኑ፣ የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ተግባራት በአግባቡ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የመከታታያ /የመመዝገቢያ/ ቅጾች አንድ መምህር በራሳቸው አዘጋጅተው እንደሚመዝኑ አስቀምጠዋል፡፡ በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የማዕርነት ይህንኑ ይበሉ እንጂ ከምልከታና ከሰነድ ፍተሻ አጥኚው መመልከት የቻለው ግን ይህንን የሚያሳይ የተከታታይ ምዘና ዕቅድና የመከታተያ ቅጽ መረጃ አልተገኘም፤ ይሁን እንጂ የማጠቃለያ ምዘና ዕቅድና ቅጽ ግን አዘጋጅተው ይተግብራሉ፡፡

ምጋቤ ምላሽ ወይም አስተያየት መሰጠት ያለበት ግን በእያንዳንዱ የምዘና ተግባር መሆን እንዳለበት ብዙዎቹ ይስማማሉ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ Race et.al (2008 ፣ 105-106)

> ተማሪዎች ለሚያከናውኗቸው የምዘና ተግባራት መምህራን ፈጣን የሆነ ምጋቤ ምላሽ ካልሰጧቸውና ተማሪዎች የሚያከናውኑት ተግባርና ምጋቤ ምላሹ የሚሰጥበት ጊዜ ክፍተታቸው በጣም የሰፋ ከሆነ የምጋቤ ምላሹ ውጤታማነት በጣም ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ በማለት ሀሳባቸው ያጠናክራሉ ፡፡

## 4.3 ከመምህራን ልቅ ጥያቄዎች የተገኘ መረጃ ትንተና

የተከታታይ ምዘና ሥልጠና ከመውሰድ አንጻር በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰጡት ምላሽ

በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን "ተከታታይ ምዘና ስልጠና ወስደው ያውቃሉ?" ለሚለው ጥያቄ አንዱ መምህርት አይደለም ሲሉ ሌላኛዋ ግን መውሰዳቸውና የስልጠናው ይዘትም "የተከታታይ ምዘና ፎርም፣ እንዲሁም የጥያቄ አወጣጥና የፈተና ስርዓትን በተመለከተ ነበር" ብሏል፡፡ የተከታታይ ምዘናው ስልጠና በምዘና አተገባበርዎ ላይ ያመጣውን ለውጥ ሲገልጹ ተማሪዎች በምን ደረጃ እንዳሉና ጠንካራና ደካማ ተማሪዎችን ለይቶ ድጋፍ ለመስጠት አስችሎኛል ብሏል፡፡ ሁለቱም መምህራን በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ያጋጠሙዋቸውን ችግሮች ሲገልጹ ብዙ ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ መገኘት፣ የስራ ጫና፣ መቅረትና ሌሎች አጋጥመውናል ብለዋል፡፡ በመጨረሻም በትምህርት ቤታችሁ የሚያሰተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘናን በአግባቡና በተሳካ ሁኔታ እንዲተገብሩ ተገቢ የሆነ ስልጠና መሰጠትና ከሌሎች ልምድ ልውውጥ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

"ተከታታይ ምዘና ስልጠና ወስደው ያውቃሉ?" ለሚለው ጥያቄ ሁለቱም በትግራይ ክልላዊ መንግስት ስር የየጭላና የፊናርዋ መምህራን መውሰዳቸውን ገልጸዋል፡፡ የስልጠናው ይዘት " የተከታታይ ምዘና ሂደት፣ አገባብና ጥቅም እንዲሁም ተከታታይ ምዘና መቼ፣ እንዴትና መቼ መሰጠት እንዳለበት የሚል ነበር" ብለዋል፡፡ የተከታታይ ምዘናው ስልጠና ግን ይህን ያህል ለውጥ አምጥቷል ብዬ ለመግለጽ አልደፍርም፡፡ ምክንያቱም በክፍል ለመተግበር ስለሚያስቸግር ነው ብለዋል፡፡ ሁለቱም መምህራን በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ያጋጠሙዋቸውን ችግሮች ሲገልጹ ብዙ ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ መገኘት፣ የስራ ጫና (በክፍለ ጊዜ ብዛት)፣ የተከታታይ ምዘናውን የአዘገጃጀት ችግርና ሌሎች አጋጥመውናል ብሏል፡፡ በመጨረሻም በትምህርት ቤታችሁ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘናን በአግባቡና በተሳካ ሁኔታ እንዲተገብሩ ተገቢ የሆነ ስልጠና መሰጠት፣ ተነሳሽነት፣ በአጫጭር ስልጠናዎች የመምህራን አቅም መገንባት፣ የመከታተያ ቅጽ ማዘጋጀትና ተከታታይ ምዘናው በትምህርት ሂደቱ እንደአንድ ስርዓት ማዋቀር ከሌሎች ልምድ ልውውጥ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ሙሀመድ አሊ (2002)፤ Alemayehu (2004) ንና Nitko (2005) ን በመጥቀስ እንዳብራሩት፣ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና አተገባበር የሚያግዝ ስልጠናም ሆነ አጋዥ ጽሑፍ ካላገኙ የምዘና ሂደታቸው የተሳሳተ አቅጣጫ ይይዛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መምህራን የተከታታይ ምዘና ትግበራ ዕውቀት ቢኖራቸውም የክፍል ጊዜ ጫና ካለባቸው ተግባራዊ ለማድረግ ይቸገራሉ ብለዋል፡፡

## 4.4 ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ ትንተና

## ሰንጠረዥ 17 ፡- የሰነድ ፍተሻ መከታተያ ቅጽ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ሀሳቦች | በማዕርነትና በሳቃ የተደረገ የሰነድ ፍተሻ | | | | አማካይ ውጤት (X1) | በየጭላና በፌናርዋ የተደረገ የሰነድ ፍተሻ | | | | አማካይ ውጤት (X2) | ልይይት (x1-x2) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይደለም | | | አዎ | | አይደለም | | | |
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | | በቁ | በ% | በቁ | በ% | | |
| 1 | በትምህርት ቤቱ ተከታታይ ምዘና በወቅቱ ይዘጋጃል፤ይካሄዳልም። | - | - | 2 | 100 | 1 | 2 | 100 | - | - | 2 | -1 |
| 2 | የሚዘጋጀው ምዘና ሦስቱ የትምህርት ዓላማዎች ያካተተ ነው፡፡ | - | - | 2 | 100 | 1 | - | - | 2 | 100 | 1 | 0 |
| 3 | ተከታታይ ምዘና የተማሪዎች ፍላጎት ያገናዘበ ነው፡፡ | - | - | 2 | 100 | 1 | 1 | 50 | 1 | 50 | 1.5 | -0.5 |
| 4 | ተከታታይ ምዘና መምህራንና ተማሪዎች ግለ ግምገማ እንዲያደርጉ እየጠቀመ ነው፡፡ | - | - | 2 | 100 | 1 | 1 | 50 | 1 | 50 | 1.5 | -0.5 |
| 5 | ትምህርት ቤቱ መስፈርት ተኮር ተከታታይ ምዘና ተግባራዊ አድርጓል፡፡ | - | - | 2 | 100 | 1 | 1 | 50 | 1 | 50 | 1.5 | -0.5 |
| 6 | ተማሪዎች ከሚፈለገው ደረጃ ደርሰዋል፡፡ | - | - | 2 | 100 | 1 | - | - | 2 | 100 | 1 | 0 |
| 7 | የትምህርቱ ይዘቶች በተቻለ ሁኔታ በፈተና ተካተዋል፡፡ | 2 | 100 | - | - | 2 | 2 | 100 | - | - | 2 | 0 |
| 8 | ተከታታይ ምዘና በመተግበር ወቅታዊ ግብረ መልስ ለተማሪዎች ተሰጥተዋል፡፡ | - | - | 2 | 100 | 1 | - | - | 2 | 100 | 1 | 0 |
| 9 | በትምህርት ቤቱ ተከታታይ ምዘና በመተግበሩ መልካም አስተዳደር ሰፍኗል፡፡ | - | - | 2 | 100 | 1 | - | - | 2 | 100 | 1 | 0 |
| 10 | በየጊዜው ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየታቸው የተሻለ ስነ ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ | - | - | 2 | 100 | 1 | 2 | 100 | - | - | 2 | -1 |
| 11 | በትምህርት ቤቱ ውጤታማ የሆነ የድጋፍ እና ክትትል ስርዓት ተዘርግቷል፡፡ | - | - | 2 | 100 | 1 | | - | 2 | 100 | 1 | 0 |

አጥኚው በማዕርነት፣ በሳቃ፣ በየጭላና በፌናርዋ አጠቃላይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመጋቢትና በሚያዝያ ወሮች ሁለት ሁለት ጊዜ በመገኘት ሰነዶችን በመፈተሽ ከሰንጠረዡ እንደሚታየው መረጃዎችን ማሰባሰብ ችሏል፡፡ በመሆኑም በየጭላና በፌናርዋ ትምህርት ቤቶች ተከታታይ ምዘና በወቅቱ ይዘጋጃል ፤ይካሄዳልም፣ በማዕርነትና በሳቃ ግን በወቅቱ እንደማይዘጋጅ መመልከት ተችሏል፡፡ ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ የማዕርነትና የሳቃ መምህራን የሚያዘጋጁት ምዘና ሦስቱ የትምህርት ዓላማዎች አልካተተም፡፡ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎች ፍላጎት ያገናዘበ ባለመሆኑ መምህራንና ተማሪዎች ግለ ግምገማ እንዲያደርጉ እየጠቀመ አይደለም፡፡ ትምህርት ቤቶቹ የትምህርቱ ይዘቶች በተቻለ ሁኔታ በፈተና ቢካተቱም ተከታታይ ምዘና በመተግበር ወቅታዊ ግብረ መልስ ለተማሪዎች ያለመስጠት ይታያል፡፡ በዚህ ምክንያትም በነዚህ ትምህርት ቤቶች ተከታታይ ምዘና ባለመተግበሩ መልካም አስተዳደር ሊሰፍን አልቻለም፡፡ በትምህርት ቤቱ ውጤታማ የሆነ የድጋፍና ክትትል ስርዓት ባለመዘርጋቱ የተሻለ ዘዴ ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም፡፡

በአጠቃላይ ከሰነድ ፍተሻው ተከታታይ ምዘና በመተግበር በኩል የየጭላና የፌናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተሻሉ ሲሆኑ፣ በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ግን በወቅቱ እንደማይዘጋጅ መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 4.5 በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ስለተከታታይ ምዘና አተገባበር ያላቸው አንድነትና ልዩነት

### 4.5.1 በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ስለተከታታይ ምዘና አተገባበር ያላቸው አንድነት

- በአራቱም ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና የተወሰነ ጅምር ቢኖርም፤ የሚተገበረው ምዘና ግን በዕቅድ የተመራ አይደለም፡፡
- አጥኚው ከመረጃ ትንተናው መረዳት እንደቻለው በአራቱም ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር መርህን በተመለከተ ሁሉም መምህራን መልካም የሚባል ግንዛቤ እንዳላቸው፣ ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ ተማሪዎች መማር የሚገባቸውን የትምህርት ይዘቶች ለመወሰን ከመረዳት አንጻር፣ ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ ለተማሪዎች

ለራሳቸው፣ ለመምህራንና ለባለድርሻ አካላት የሚጠቅም መሆኑን መረዳት መቻል፣ ልዩ ዕገዛ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለመለየትና ለመርዳት ከተከታታይ ምዘና የሚገኝ መረጃ አስፈላጊ መሆኑን መረዳታቸው ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተከታታይ ምዘና ሂደት ዕቅድ ማውጣት የመጀመሪያ ተግባር መሆኑን መረዳታቸው፣ ተከታታይ ምዘና ተማሪዎችን እንደንቋንቋ ችሎታቸው ለመለየት እንደሚያስችል መገንዘባቸውና ከተከታታይ ምዘና ስልቶች መካከል የተወሰኑትን በተከታታይ መጠቀማቸው ናቸው፡፡ በሁለቱም ክልሎች ማለትም በአራቱም ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘናን ሲተገብሩ ከተማሪዎች ጋር በሂደቱ ዙሪያ ግልጽ የሆነ ውይይት በማድረግ አለመወሰን፡፡ ተማሪዎች ሁልጊዜ በራሳቸውም ይሁን በጓደኞቻቸው ተግባራት ላይ ምጋቤ ምላሽ ወይም አስተያየት አለመስጠታቸው፣

አጥኚው በሁሉም ትምህርት ቤቶች ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች በአማርኛ ቋንቋ መምህራን በግንዛቤ ደረጃ እንኳን ቢሆን መረዳታቸው ማረጋገጥ ችሏል፡፡

### 4.5.2 በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ስለተከታታይ ምዘና አተገባበር ያላቸው ልዩነቶች

አጥኚው ምንም እንኳን ከላይ የተጠቆሙትን የጋራ ሀሳቦች ማረጋገጥ ቢችልም፤ በመካከላቸው ግን ሰፊ የተከታታይ ምዘና የአተገባበር ልዩነቶች መኖራቸውን ማየት ችሏል፡፡ ከልዩነቶች መካከልም፡-

- በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የማዕርነትና የሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተለያዩ የግልና የቡድን ተግባራት ከመስጠታቸው በፊት ግልጽ የሆነ መመሪያና ማብራሪያ አለመሰጠታቸው፣
- በተጨማሪም በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማጠናከሪያ ተግባራት እየሰጡ የተማሪዎችን ችሎታ የበለጠ እንዲዳብር አለማድረጋቸው፣
- እንዲሁም እነዚህ መምህራን ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረግ ተማሪዎች ለወደፊቱ ማሻሻል ያለባቸውን እንዲገነዘቡ አለማስቻላቸው፣

- የመምህራኑ ትኩረት ተማሪዎች በሚያከናውኑት ተግባር ላይ ሳይሆን በውጤት ብቻ ማድረግ፣
- ከላይ እንደተጠቆመው በተወሰነ መልኩ ተከታታይ ምዘና ተጠቀሙ እንኳን ቢባል የተማሪዎችን መሻሻል የሚያሳይ ሳይሆን በውጤት ላይ ማተኮራቸው፣
- በቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ ተማሪዎች ለሚያከናውኑዋቸው የግልና የቡድን ተግባራት አጥጋቢ ካልሆነ ድክመታቸውን የሚያሻሽሉበትን ሌላ ዕድል ያለመስጠት በተለይ ደግሞ በማርነትና በፌናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጎልቶ ይታያል፡፡
- በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አብዛኛውን ጊዜ መምህራን ከሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ይልቅ የማጠቃለያ ምዘናን መጠቀም፣
- አጥኚው ቀደም ብሎ እንደጠቆመው የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ከምዘና ስልቶች መካከል የቃል ጥያቄዎች ና የክፍል ስራን በተደጋጋሚ ይጠቃማሉ እንጂ ሌሎች የምዘና ስልቶች ማለትም የግል ስራ(ፕሮጀክት)፣ የመምህርና ተማሪ ወይይት፣ የቡድን ስራ (ፕሮጀክት)፣ ሰነደ ትምህርት (ፖርቲፎሊዮ) ና ግለ ግምገማ በመጠቀሙ በኩል እጥረት መኖሩ፣
- ብዙ ተማሪዎች ባሉበት መማሪያ ክፍል ውስጥ ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ለማድረግ ያስቸግራል ብሎ በማሰብ ተከታታይነት ያለው ምዘና በተለይ ደግሞ በማዕርነትና በየጭላ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጎልቶ ይታያል፡፡
- በፌናርዋ፣ በማዕርነትና በሳቃ ትምህርት ቤቶች የተከታታይ ምዘና መስፈርቶች በመምህራን ብቻ እንዲወጡ ማድረግ፣
- በማዕርነትና በፌናርዋ ትምህርት ቤቶች የተከታታይ ምዘና ተግባራት መከታተያ ቅጽ ያለመጠቀም(በሰነድ ፍተሻ የተረጋገጠ) የሚሉት ናቸው፡፡ አጥኚው በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩትን እጥረቶች በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ የተገኘውን መረጃ ትንተና ማረጋገጥ ችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሐሳቦች

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማራና በትግራይ ክልላዊ መንግስታት 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡

በምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰንና የጥናቱ ውስንነት እንዲሁም በምዕራፍ ሁለት ደግሞ የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝትና ተዛማጅ ጥናቶች ቀርበዋል፡፡ በምዕራፍ ሦስት ደግሞ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፤ ዐቢይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጽሑፍ መጠይቅና የሰነድ ፍተሻ፣ እንዲሁም ደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ቃለ መጠይቅና ምልከታ የተካተቱ ሲሆኑ፣ በምዕራፍ አራት ደግሞ በነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች እንደየዝምድናቸው በማቀናጀት ተተንትነዋል፡፡ በትንተናው የተገኙ ንጽጽራዊ ውጤቶችም ከዚህ በታች ጠቅለል ብለው እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

1. ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ጥቅሞች ለቀረቡላቸው የግንዛቤ ጥያቄዎች ሁሉም አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የተደረገው ምልከታና ሰነድ ፍተሻ እንደሚያስረዳው የየጭላና የፊናርዋ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ችሎታ ማሳያ የሐሰት የነጥብ ማጠራቀሚያ (False marklist) አዘጋጅተው ተከታታይ ምዘና እንደሚተገብሩ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የማዕርነትና የሳቃ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሰነድ ፍተሻ እንደተረጋገጠው የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ጥቅም ቢገነዘቡም፣ ተከታታይነት ባለው መልኩ ተግባራዊ ሊያደርጉ አልቻሉም፡፡
2. በአራቱም ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከታታይ ምዘና የተወሰነ ጅምር ቢኖርም፤ የሚተገበረው ምዘና ግን በዕቅድ የተመራ አይደለም፡፡

3. አራቱም የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በተለያዩ የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ተማሪዎቻቸውን መመዘናቸው ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን ደጋግሞ በማሰራት ሂደት በጥናቱ ተተኳሪ ቡድኖች መካከል ልዩነት ታይቷል፡፡ ሁሉም ትምህርት ቤቶች የቃል ጥያቄዎች በመጠየቅ፣ የክፍል ስራ በማሰራት፣ የቤት ስራ በመስጠትና ከተማሪዎች ፊት እየወጡ በማቅረብ የተሻሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ፣ ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የግል ሥራ (ፕሮጀክት)፣ የቡድን ሥራ (ፕሮጀክት)፣ ግለ ግምገማ፣ ምልከታና የመምህር ተማሪ ውይይት በማድረግ በኩል ዝቅ ያሉ መሆናቸውን ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም ሙከራ በመስጠት በኩል ሁሉም ተመሳሳይ ሆነው ተገኝተዋል፡፡
4. ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ ተማሪዎች መማር የሚገባቸውን የትምህርት ይዘቶች ለመወሰን ከመርዳት አንጻር፣ ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረግ ተማሪዎች ለወደፊቱ ማሻሻል ያለባቸውን እንዲገነዘቡ ከማድረግ አንጻር የየጭላ ና የፊናርዋ የጥናቱ ተተኳሪ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተሻሉ ቢሆኑም፣ የማዕርነትና የሳቃ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ደግሞ ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረግ ተማሪዎች ለወደፊቱ ማሻሻል ያለባቸውን እንዲገነዘቡ አለማስቻላቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡
5. ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ ወይም አስተያየት ማተኮር ያለበት ተማሪዎች ያሳዩትን ደካማ ጎን ለማስተካከል እንደሆነ በግንዛቤ ደረጃ በመያዝ በኩል መልካም ቢሆኑም፣ በሰነድ ፍተሻና በምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የተወሰነ ጅምር እንጂ የሚሰጡት አስተያየት አለመኖር፤ የሚሰጠው ምጋቤ ምላሽ ደግሞ ተማሪውን የሚገነባ አለመሆኑ ተመልክቷል፡፡
6. ተማሪዎች ለሚያከናውኑዋቸው የቡድንና የግል ተግባራት የማዕርነትና የሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህር ቤቶች የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ተከታታይ ምዘና ሲሰጧቸው ግልጽ የሆነ ማብራሪያና መመሪያ እንደማይሰጧቸው እና ግልጽ የሆነ መስፈርትም እንደማይጠቀሙ የተማሪዎች ምላሽ ያሳያል፡፡ ይህ ሁኔታ በሰነድ ፍተሻም ተስተውሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው እንዲመዝኑ ዕድሉን አለማመቻቸታቸው፣ የመመዘኛ መስፈርቶችን በማውጣት ሂደት ተማሪዎችን አለማሳተፋቸው፣ ከተከታታይ ምዘና

የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ ለተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት አለመስጠታቸውና ተማሪዎች በሚያከናውኑዋቸው የቡድንና የግል የምዘና ተግባራት ምጋቤ ምላሽ አለመስጠታቸው ማየት ተችሏል፡፡

7. የጥናቱ ተተኳሪ የማዕርነትና የፌናርዋ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በሚመዝኑበት ጊዜ የመምህራኑ ትኩረት በሂደቱ ላይ ሳይሆን በውጤት ብቻ ትኩረት ስለሚያደርጉ አብዛኛውን ጊዜ ከሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ይልቅ የማጠቃለያ ተከታታይ ምዘና እንደሚጠቀሙ ተስተውለዋል፡፡
8. በየጭላና በማዕርነት የሚገኙ የጥናቱ ተተኳሪ 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍለ ጊዜ ብዛት፣ ብዙ ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ መኖር ፣ የተማሪዎች ተከታትሎ በክፍል አለመገኘት ወይም መቅረት፣ በማዕርነት፣በየጭላና በፌናርዋ ትምህርት ቤቶች ስለተከታታይ ምዘና ድጋፍ ስልጠና አለማግኘትና የእርስ በእርስ ሱፐርቪዥንን ለማድረግ ስርዓት አለመዘርጋት ተከታታይ ምዘና ተግባራዊ ለማድረግ መምህራን ካጋጠሙዋቸው ችግሮች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡
9. ሌላው ርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ለቃለ መጠይቁ የሰጡት ምላሽ የሚያመለክተው በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በዲፕሎማና በዲግሪ የሚያሰለጥኑ መምህራን ሂደታዊ ተከታታይ ምዘናን በትውረት ደረጃ እንጂ ራሳቸው በተግባር ስለማይተገብሩት በዛው ሂደት የሰለጠኑ የ8ኛ ክፍል መምህራን ደግሞ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ሲተገብሩት አይስተዋልም፡፡

## 5.2 የጥናቱ መደምደሚያ

አጥኚው በጥናቱ ከተገኙ ውጤቶች በመነሳት የሚከተሉትን የመደምደሚያ ሀሳቦች ላይ መድረስ ችሏል፤

1. በአራቱም ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተወሰነ ጅምር ቢኖርም፤ የሚተገበረው ምዘና ግን በዕቅድ የተመራ አይደለም፡፡
2. ምንም እንኳን ከሁሉም መምህራን የተገኘ ምላሽ የሚያሳየው ስለተከታታይ ምዘና ጥሩ ግንዛቤ ቢኖራቸውም፣ የመማር ማስተማር አካል መሆኑን ተረድተው ተማሪዎቻቸውን በተከታታይ እንደማይመዝኑ ማየት ተችሏል፡፡

3. የተከታታይ ምዘና ስልቶች በርካታ ቢሆኑም፣ አብዛኛውን ጊዜ የሁለቱም ክልሎች የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የሚጠቀሙባቸውን ስልቶች የክፍል ስራ፣ ከተማሪ ፊት እየወጡ ማቅረብ፣ የቃል ጥያቄዎችና የቤት ስራ በተደጋጋሚ የሚጠቀሙባቸው ቢሆኑም የግል ስራ፣ የቡድን ስራ፣ የመምህር ተማሪ ውይይት፣ ምልከታ ና ሌሎች ትኩረት ያልተሰጣቸው ስልቶች መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡
4. ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ ተማሪዎች መማር የሚገባቸውን ይዘቶች ለመወሰንና ለወደፊቱ መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮች ለማስካከል የሚረዳ ቢሆንም፣ በአማራ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረግ ተማሪዎች መሻሻል ያለባቸውን እንዲገነዘቡ አለማስቻላቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡
5. የሁለቱም ክልሎች የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ምጋቤ ምላሽ እንደማይሰጡና ተማሪዎች በራሳቸውም የጓደኛ ለጓደኛ (የቢጤ) እርማት እንደማይጠቀሙ ማየት ችሏል፡፡
6. አልፎ አልፎ የማዕርነትና የሳቃ ተጠኝ መምህራኑ ተከታታይ ምዘና ቢሰጡም፣ ግልጽ የሆነ ማብራሪያና መመሪያ አለመስጠታቸው፣ ምዘናው ውጤታማ ሊሆን አለመቻሉን፡፡
7. የአማራ ክልላዊ መንግስት የመምህራኑ የምዘና ትኩረት በሂደቱ ሳይሆን በውጤት ላይ መሆኑን ማየት ችሏል፡፡
8. በሁለቱም ክልሎች የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ተከታታይ ምዘና በክፍል ውስጥ ተግባራዊ እንዳያደርጉ ያስቸገራቸው ብዙ ተማሪዎች በአንድ ክፍል መማር፣ የክፍል ጊዜ ብዛት፣ መሰላቸት፣ ድጋፍና ስልጠና አለማግኘትና የእርስ በእርስ ሱፐርቪዥንን ስርዓት አለመዘርጋት መሆናቸውን መገንዘብ ችሏል፡፡
9. በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚያሰለጥኑ መምህራን ተከታታይ ምዘናን በትውረት ደረጃ እንጂ ተግባራዊ ስለማያደርጉ እነዚህ መምህራንም ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን እንደማይጠቀሙበት መገንዘብ ችሏል፡፡

## 5.3 የመፍትሔ ሐሳቦች

አጥኚው በጥናቱ የተገኙትን ውጤቶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን የመፍትሔ ሐሳቦች ሰንዝሯል፡፡

1. በአራቱም ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና ትግበራ የተወሰነ ጅምር ቢኖርም፤ የሚተገበረው ምዘና ግን በዕቅድ የተመራ ስላልሆነ የሚያካናውኑት ምዘና በዕቅድ የተመራ ቢሆን፡፡
2. የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የተከታታይ ምዘና መርህና ጠቀሜታ በመረዳት ተማሪዎቻቸውን በተከታታይ መመዘን ቢችሉ፤
3. የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን እንደየቃል ጥያቄዎች፣ የክፍል ስራ፣ ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ የመሳሰሉትን ስልቶች የሚጠቀሙ ቢሆንም፣ ሌሎች ተጨማሪ የምዘና ስልቶች ቢጠቀሙ፤
4. የተከታታይ ምዘና ዓላማ የተማሪዎችን መማር ለማስተካከል ወይም ማሻሻያ ለማድረግና ዕድገታቸው ለመከታተል ቢሆንም፣ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ግን ለውጤት ስለሚመዝኑ የተከታታይ ምዘናውን ዓላማ ተረድተው ተማሪዎቻቸውን በተከታታይ መመዘን ቢችሉ፤
5. ተማሪዎች በራሳቸው የእርስ በእርስ እርማት መሰጣጠት ቢችሉ፤ እንዲሁም መምህራን ለተማሪዎቻቸው ገንቢ የሆነ ምጋቤ ምላሽ መስጠት ቢችሉ፤
6. የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የሚያስተምሩዋቸው ተማሪዎች ህጻናት እንደመሆናቸው ተከታታይ ምዘና ሲሰጡ ግልጽ የሆነ ማብራሪያና መመሪያ መስጠት ቢችሉ፤
7. የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ተከታታይ ምዘና ሲመዝኑ ለውጤት ሳይሆን የመማር ማስተማር ስነ ዘዴ ለመምረጥ ቢጠቀሙበት፤
8. የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ እንዳያደርጉ ያደረጉቸውን ችግሮች በመፍታት የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ተመጣጣኝ ተማሪ በአንድ ክፍል መመደብ ቢችል፤ የክፍለ ጊዜ ብዛት ያለባቸው መምህራን የስራ ጫና ለመቀነስ የወረዳና የክልል የትምህርት ባለሙያዎች በቂ መምህራን መመደብ ቢችሉ፤ የግንዛቤ እጥረት ያለባቸውን ደግሞ ድጋፍና ስልጠና ቢያገኙ፤ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ውጤታማ የሆነ የእርስ በእርስ ሱፐርቪዥን ስርዓት መዘርጋት ቢችል፡፡
9. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንን የሚያሰለጥኑ ተቋማት ከትውረት የዘለለ አርአያ ሆነው ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ቢያደርጉ፣ እነዚህ መምህራን ራሳቸውም ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡

# ዋቢ ጽሑፎች

መሀመድ አሊ፡፡ (2002)፡፡ "በደሴ ከተማ በመንግስትና በግል ትምህርት ክፍል በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል የተከታታይ ምዘና አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት፡፡" ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

በድሩ ከድር፡፡ (1994)፡፡ *የትምህርት ተከታታይ ምዘና ግምገማ ጽንሰሐሳቦችና ቴክኒኮች*፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ተስፉ አከለ፡፡ (2000)፡፡ "የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታተይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ፤ በትግራይ ክልል በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች፡፡" አዲስ አበባ፣ የድህረ ምረቃ ማሟያ መርሐ ግብር የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ተካ ወሌ፡፡ (1998)፡፡ "ተከታታይ ምዘና ለትምህርት ጥራት፡፡" በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ለአጭር ስልጠና የተዘጋጀ /ያልታተመ/፡፡

ታጠቁ ታደለና ሌሎች፡፡ (1995)፡፡ *የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተከታታይ ምዘና መመሪያ፡፡* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ፡፡ (1999)፡፡ "ፍተሻ፣ ምዘናን ገምጋምን ብቕዓት ተምሃሮ፡ መምርሒ መረጋገጺ ብቕዓት ትምህርትን ምዘናን፡፡" መቐለ፣ ደስታ ሕትመት ቤት፡፡

አልማዝ ሃይሉ፡፡ (1999)፡፡ "አራተኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

አልማዝ ፍሬው፡፡ (2003)፡፡ "በአማራ ክልል የሚገኙ ሁለት የመንግስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

አማራ ክልል ትምህርት ቢሮ፡፡ (1997)፡፡ “ተከታታይ ምዘና እና ተግባራዊ ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርዕስ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ስልጠና የተዘጋጀ፡፡” ባህርዳር፣ ያተተመ ጥራዝ (ሞጁል)፡፡

አማራ ትምህርት ቢሮ፡፡ (2000)፡፡ “ተከታታይ ምዘና እና ተግባራዊ ምርምር ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርዕስ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ስልጠና የተዘጋጀ፡፡” ባህርዳር፣ ያተተመ ጥራዝ (ሞጁል)፡፡

አማራ ትምህርት ቢሮ፡፡ (2006)፡፡ *የመማር ማስተማር ሂደት አመራር ለርዕሠ መምህራንና ሱፐርቫዘሮች ሥልጠና የተዘጋጀ የሥልጠና ሞጁል፡፡* /ያልታተመ/፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2004)፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር* (3ኛእትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ደሴ መም/ትምህርት ኮሌጅ፡፡ (2004)፡፡ የትምህርት ምዘናና ግምገማ /ለክላስተር ዲፕሎማ ስልጠና የተዘጋጀ/፡፡ (ያልታተመ)።

ዳንኤል ዘውዴ፡፡ (1999)፡፡ “የተከታታ ምዘና አተገባበር፡፡” ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፣ ለአጭር ስልጠና የተዘጋጀ (ያልታተመ)፡፡

AED/BESO II. (2005). “A Concise Manual for Developming and Implementing continuous Assessment in Teacher Education Institutions and Primary Schools of Ethiopia.” Addis Ababa,(unpublished).

AED/BESO II. (2006). “A Concise Manual for Developming and Implementing continuous Assessment in Teacher Education Institutions and Primary Schools of Ethiopia.” Addis Ababa,(unpublished).

Aggrawal, J. C. (1994). *Essential of Educational Psychology*. New Delhi: Vikas Publishing Company.

Airasian, P.W. (1997). *Classroom Assessment.* New York: Mc Graw-Hill,Inc.

Alausa, A. (1999). “Continuouns Assessment in our schools: Advantages and Problems.” Journal of educational Reform in Namibia. Vol. 13, No. 6. Namibai.

Brooks, V. (2002). *Assessment in Secondary School; Recording, Reporting and Accountability.* Buckingham: Open University Press.

Capper, J. (1996). *Testing to Learn- Learning to Test. Improving Educational Testing In Developing Countries*. Washington: International Reading Association Press.

Cullingford, C. (1995). *The Effective Teacher*. New York: Cassell.

Curzon, L. (1990). Teaching in Further Education: An Outline.

Dessalegn Chalchisa. (2004). "Continuouse Assessment in Lower cycle Primary School." IER Flambeau. Vol.12, No.1, PP. 1-8.

Dessalegn Chalchisa and Girma Lemma. (2009). Measurement and Evaluation: Manual For Higher Education Institution. Addis Ababa: AAU Press.

Elington, H. and Earl, S. (1997). Making Effective use of Continuous Assessment and Portifolios.

Hamis, M. (1997). Self Assessment of Language Learning in formal Settings, ELT Journal, vol.51 No, 1. Oxford: Oxford University Press.

ICDR. (2004). Teacher Education Handbook: Institute for Curriculum Development and Research. Ethiopia: Addis Ababa.

Livingston, G. (2001). "Taking Teacher Educators Forward." *Ten steps Towords Quality*: A Report: Ministry of Education. Addis Ababa.

Ministry of Education. (2003). "Teacher Education System. "Addiss Ababa. (Unpublished).

Ministry of Education. (2004). "Guidelines for Continuous Assessment." Addiss Ababa. (Unpublished).

Murphy, J. (1996). Instructional Leadership: Focus on Curriculum responsibilities.

Nitko, J. A. (1996). *Educational Assessments* (2nd Ed.). Englewood: Prentice Hall, Inc.

Nitko, J. A. (2008). Evaluating and Reporting Students Progress, English Language Arts: A Curriculum Guide for Secondary Level- Evaluation Fill://A: English % 20 Language % Arts % 20 A 20 Curriculum % 20

Guide % 20 % for 20 % page 1-7.

Nejabili, A. (1999). *Practical guide for Classroom Measurement and testing, the basic essentials*. Dares Selaam: Mature Publishers.

Puckett, M. B. and Black, J. K. (2008). *Authentic Assessment of the Young Child: Celebrating Development and Learning* (2nd ed.). Des Moins, IA: Prentice-Hall Inc.

Puhi C.A. (1997). Develop, Not Judge Continuous Assessment in the ESL Classroom. English Teaching Forum vol 35, No. 2.

Race, P. and et al. (2008) *500 Tips on Assessment*. (2nd Ed). London: Roultedge Falmer.

Shabaan, K. (2001). "Assessment of Young Learners." English Teaching Forum፡Vol.39, No, 4, PP.16-23.

Teshome Demsie (2001). "Assessment of Pupils Achievements in the Teaching of English Training and practice in focus." The Ethiopian Journal of Education.Vol. 21, No.1, PP.25-47.

WIkPEDIA (2015). last edited on 29 Sepember.www.Business (2016) Dictionary.com/…/continuous assessment.

Witson, S. (2002). Comparing Peer, Self and Tutor Assessment in a course for University. Teaching Staff. Retrieved from http: // www. cshe. unimbl. edu. Au./assessinglearning/05/.

# አባሪዎች

## አባሪ ሀ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒትስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ማስተማር የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በአማራ ክልላዊ መንግስትና በትግራይ ክልላዊ መንግስት 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች የማስተርስ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

### በተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

የዚህ የጽሑፍ መጠይቅ ዋና ዓላማ በአማራ ክልላዊ መንግስትና በትግራይ ክልላዊ መንግስት 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ምን እንደሚመስል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ይህን መረጃ መሰብሰብ ያስፈለገበት ምክንያት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒትስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ማስተማር የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ጥናታዊ ጽሑፍ ለማዘጋጀት ነው፡፡በመሆኑም ከመጠይቁ የሚገኘው መረጃ የተጀመረው ጥናት መሳካት ከፍተኛ እገዛ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

ማሳሰቢያ፡- 1. በጽሁፍ መጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልም፡፡

1 መጠይቁን ከሌላ ጓደኛ ጋር ተመካክሮ መጠይቁን ከሌላ የስራ ተማሪ ጋር ተመካክሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ የተከለከለ ነው፡፡

2 መረጃው ከመመረቂያ ፅሁፍ ውጭ ለሌላ ዓላማ አይውልም፡፡

## ክፍል አንድ፡-አጠቃላይ መረጃ

1. ክልል-------------------------------------------------------------
2. ወረዳ-----------------------------------------------------------------

3. የምትማሪበት/ርበት ትምህርት ቤት ስም---------------------------------------------

4. ክፍል------------------------------ 5. ጾታ--------------------------

**ክፍል ሁለት፡-** ከዚህ ቀጥሎ የአማርኛ ቋንቋ መምህሮቻችሁ የተከታታይ ምዘና አተገባበራቸው በአንተ/ቺ ግንዛቤ ምን እንደሚመስል ለማወቅ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡት ዝርዝር ጥያቄዎች ትይዩ መልስ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡ አራት አማራጮች ቀርበዋል፡፡ እነዚህም አማራጮች በቁጥር የተወከሉ ሲሆን የሚከተሉትን የመስማማት ደረጃዎች የያዙ ናቸው፡፡

4 = በጣም እስማማለሁ

2 = እስማማለሁ

2 = አልስማማም

1 = በጣም አልስማማም

እናንተም በጥያቄዎቹ ትይዩ የምትሰጡትን መልስ የ "×" ምልክት በማድረግ አስቀምጡ፡፡

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | መምህራን የተለያዩ የቡድንና የግል ተግባራትን ከመስጠታቸው በፊት ግልጽ የሆነ መመሪያና ማብራሪያ ይሰጡኛል | | | | |
| 2 | መምህራን ስራዎቼን ሲመዝኑ ግልጽ መስፈርት ይጠቀማሉ | | | | |
| 3 | በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ በማሳያቸው ድክመቶች የማስተካከያ እገዛ ያደርጉልኛል | | | | |
| 4 | በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ መምህራን የተለያዩ የማጠናከሪያ ተግባራትን እየሰጡ ችሎታዬን የበለጠ እንዳዳብር ያደርጉኛል | | | | |
| 5 | ለማከናውናቸው የተለያዩ የቡድንና የግል ተግባራትን መምህራን ምጋቤ ምላሽ /አስተያየት/ ይሰጡኛል | | | | |
| 6 | በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ሁል ጊዜ የራሴን በራሴ እገመግማለሁ | | | | |
| 7 | በግልም ሆነ በግል ለማከናውናቸው ተግባራት ጓደኞቼ አስተያየት /ምጋቤ ምላሽ/ ይሰጡኛል | | | | |
| 8 | በማከናውናቸው የቡድንና የግል ተግባራት የመምህራን ትኩረት | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አንድን ነገር እንዴት አድርጌ እንደሰራሁት ማየት ሳይሆን ምን እንደሰራሁ ማየት ነው | | | | |
| 9 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ እንደሙከራ የቡድንና የግል ስራ የመሳሰሉ የምዘና ስልቶችን የሚጠቀሙት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ሂደት የሳየሁትን መሻሻል ለመመዘን ሳይሆን ውጤት መስጠት ነው | | | | |
| 10 | ከተለያዩ የምዘና ስልቶች የማገኘው መረጃ ለወደፊቱ ማሻሻል ያለብኝን ነገር እንድገነዘብ አስችሎኛል | | | | |
| 11 | በተከታታይ ምዘና ሂደት የሰራናቸው የተለያዩ የቡድንና የግል ስራዎች እንዴት እንደሚታረሙና ምን ያህል ውጤት መያዝ እንዳለባቸው ከመምህራን ጋር ተወያይተን እንወስናለን | | | | |
| 12 | ለምሰራቸው የቡድንና የግል ስራዎች የማገኘው ውጤት ከስራዬ ጋር የሚመጣጠን እንደሆነ ይሰማኛል | | | | |
| 13 | በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የሰራሁት ስራ አጥጋቢ ካልሆነ ድክመቴን የማሻሽልበት ሌላ ዕድል ይኖረኛል | | | | |
| 14 | ከሙከራ፣ ከቤት ስራ፣ ከቡድንና ከግል ስራዎች የማገኘው መረጃ የራሴን የጥናት ፕሮግራም እንዳስካክል ረድቶኛል | | | | |
| 15 | በቡድንና በግል የማከናውናቸው የተለያዩ የምዘና ተግባራት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ ዙሪያ የማሳያቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንድለይ አስችለውኛል | | | | |
| 16 | በጽሑፍ ፈተና ላይ ከተመሰረተ ምዘና ይልቅ በተለያዩ ጊዜያት የማከናውናቸው የቤት ስራዎች፣ የቡድንና የግል ስራዎች በአማርኛ ቋንቋ የማገኘውን ትምህርት የተሻለ አድርገውልኛል | | | | |

**ክፍል ሦስት፡-** *መምህራን የሚከተሉትን የተከታታይ ምዘና ስልቶች እናንተን ለመመዘን ምን ያህል እንደሚጠቀሙባቸው ለማወቅ ከምዘና ስልቶች ትይዩ ሁለት አማራጮች ቀርበዋ፡፡ አማራጮችም በቁጥር የተወከሉ ሲሆን የሚከተሉትን የጊዜ ድግግሞሽ የሚያሳዩ የውሳኔ ሀሳቦችን የያዙ ናቸው፡፡*

2 = እስማማለሁ
1 = አልስማማም

እናንተም በጥያቄዎቹ ትይዩ የምትሰጡትን መልስ የ “×” ምልክት በማድረግ አስቀምጡ፡፡

| ተ.ቁ | የተከታታይ ምዘና ስልቶች | አማራጮች | |
|---|---|---|---|
| | | 2 | 1 |
| 1 | የቃል ጥያቄዎች | | |
| 2 | የቤት ሥራ | | |
| 3 | ምልከታ | | |
| 4 | ሙከራ/ፈተና/ | | |
| 5 | የግል ሥራ/ፕሮጀክት/ | | |
| 6 | የቡድን ሥራ/ፕሮጀክት/ | | |
| 7 | የመምህር ተማሪ ውይይት | | |
| 8 | ሰነደ ትምህርት/ፖርትፎሊዮ/ | | |
| 9 | ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ | | |
| 10 | የግል ምዘና | | |
| 11 | የጓደኛ ለጓደኛ/የቢጤ / ምዘና | | |
| 12 | የክፍል ሥራ | | |

## አባሪ ለ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒትስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ማስተማር የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በአማራ ክልላዊ መንግስትና በትግራይ ክልላዊ መንግስት 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ
የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት
በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች የማስተርስ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

### አማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

ውድ መምህራን! የዚህ የጽሑፍ መጠይቅ ዋና ዓላማ በአማራ ክልላዊ መንግስትና በትግራይ ክልላዊ መንግስት 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ምን እንደሚመስል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡

በጥናቱ የሚደረስበት ውጤት የቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና ላይ ያላቸውን ግንዛቤና ክህሎት ምን መምሰል እንዳለበት በመጠቆም በኩል ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ በመሆኑም ከመጠይቁ የሚገኘው ምላሽ ለተጀመረው ጥናት መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ ጥናቱ የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ ትክክለኛ መረጃ ማሰባሰብ አስፈላጊ በመሆኑ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥንቃቄና በጥሞና በማንበብ ትክክል ናቸው የሚሏቸውን መልሶች በተሰጡት ቦታዎች ላይ በመፃፍ እንዲመልሱልኝ ስጠይቅ የሚደረግልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** 1. በጽሑፍ መጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡

3 መጠይቁን ከሌላ የስራ ባለደረባ ጋር ተመካክሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት
ስለሚያዛባ የተከለከለ ነው፡፡

4 መረጃው ከዚህ ዓላማ ውጭ ለሌላ አይውልም፡፡

**ክፍል አንድ፡- አጠቃላይ መረጃ**

1.ክልል------------------------------------------------------------------------------------

2.ወረዳ-----------------------------------------------------------------------------------

3.የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም---------------------------------------------

4.ጾታ-------------------------------------------------------------------------------------------

5. የትምህርት ደረጃ---------------------------------------------------------------------------

6. በትምህርት ቤቱ ምን ያህል ጊዜ አስተምረዋል-------------------------------------------

**ሀ/ የሚከተሉትን የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ተማሪዎችዎን ለመመዘን ምን ያህል እንደሚጠቀሙባቸው ለማወቅ ከምዘና ስልቶች ትይዩ አማራጮች ቀርበዋል፡፡ አማራጮቹም በቁጥር የተወከሉ ሲሆኑ የሚመዘኑበትን የጊዜ ድግግሞሽ የሚያሳዩ የውሳኔ ሥራዎችን የያዙ ናቸው፡፡**

3 - **ሁል ጊዜ**

2 - **አልፎ አልፎ**

1 - **አልጠቀምም**

እርስዎም በጥያቄዎቹ ትይዩ የሚሰጡትን መልስ የ “ × ” ምልክት በማድረግ ያመልክቱ፡፡

| ተ.ቁ | የተከታታይ ምዘና ስልቶች | አማራጮች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 3 | 2 | 1 |
| 1 | የቃል ጥያቄዎች | | | |
| 2 | የቤት ሥራ | | | |
| 3 | ምልከታ | | | |
| 4 | ሙከራ/ፈተና/ | | | |
| 5 | የግል ሥራ/ፕሮጀክት/ | | | |
| 6 | የቡድን ሥራ/ፕሮጀክት/ | | | |
| 7 | የመምህር ተማሪ ውይይት | | | |
| 8 | ሰነደ ትምህርት/ፖርትፎልዮ/ | | | |
| 9 | ከተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ | | | |
| 10 | ግለ ግምገማ | | | |
| 11 | የጓደኛ ለጓደኛ/የቢጤ / ምዘና | | | |
| 12 | የክፍል ሥራ | | | |

**ክፍል ሁለት፡-**

**ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ዝርዝር ጥያቄዎች መልስ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡት አራት አማራጮች ተሰጥተዋል፡፡እነዚህም አማራጮች በቁጥር የተወከሉ ሲሆን የሚከተሉትን የመስማማት ደረጃዎች የያዙ ናቸው፡፡**

4 = በጣም እስማማለሁ

3 = እስማማለሁ

2 = አልስማማም

1 = በጣም አልስማማም

እርስዎም ጥያቄዎችን ካነበቡ በኋላ በጥያቄዎቹ ትይዩ የሚሰጡትን መልስ “×” ምልክት በማድረግ ያስቀምጡ፡፡

| ተቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | ተከታታይ ምዘና የመማር ማስተማሩ ሂደት አካል ነው፡፡ | | | | |
| 2 | ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ ተማሪዎች መማር የሚገባቸውን የትምህርት ይዘቶች ለመወሰን ይረዳል፡፡ | | | | |
| 3 | ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው መረጃ የሚጠቅመው ለአስተማሪው ብቻ ነው፡፡ | | | | |
| 4 | ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለመለየትና ለመርዳት ከተከታታይ ምዘና የሚገኝ መረጃ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ | | | | |
| 5 | በተከታታይ ምዘና ሂደት ዕቅድ ማውጣት የመጀመሪያ ተግባር ነው፡፡ | | | | |
| 6 | የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን በተከታታይ ምዘና ዕቅድ ውስጥ ማካተት በራሱ በቂ ነው፡፡ | | | | |
| 7 | ተከታታይ ምዘና ተማሪዎችን እንደየቋንቋ ችሎታቸው ለመለየት ያስችላል፡፡ | | | | |
| 8 | የተከታታይ ምዘና በክፍል ውስጥ በመተግበር መምህራን የተማሪዎችን ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ ይጠቅማቸዋል፡፡ | | | | |
| 9 | ብዙ ተማሪዎች ባሉበት መማሪያ ክፍል ውስጥ ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ማድረግ ይቻላል፡፡ | | | | |
| 10 | ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በጓደኞቻቸው ሥራዎች ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ | | | | |
| 11 | በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው መገምገም ይችላሉ፡፡ | | | | |
| 12 | ተከታታይ ምዘና መምህራን ብቸኛ የውሳኔ ሰጭ አካል እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ | | | | |
| 13 | በተከታታይ ምዘና ሂደት የመመዘኛ መስፈርቶችን ማውጣት ያለባቸው መምህራን ብቻ ናቸው፡፡ | | | | |
| 14 | ከተለምዷዊው (በፅሑፍ ፈተና መልክ ብቻ ከሚቀርበው) የምዘና ስርዓት ይልቅ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ያነሳሳል፡፡ | | | | |
| 15 | ተከታታይ ምዘና ተማሪዎችን ትምህርታቸውን ተነቃቅተው እንዲማሩ ያደርጋቸዋል ብዬ አስባለሁ፡፡ | | | | |
| 16 | የተከታታይ ምዘና ትኩረት ተማሪዎችን ጎበዝ ወይም ደካማ ናቸው ብሎ ለመፈረጅ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ | | | | |
| 17 | ከተለምዷዊው (በፅሑፍ ፈተና መልክ ብቻ ከሚቀርበው) የምዘና ስርዓት ይልቅ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን በተሻለ ሁኔታ ለመለየት ያስችላል፡፡ | | | | |
| 18 | የተከታታይ ምዘና ትኩረት በአብዛኛውን ጊዜ በውጤት ላይ እንጂ በሂደት ላይ አይደለም፡፡ | | | | |
| 19 | በተከታታይ ምዘና ሂደት ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ /አስተያየት/ ሲሰጥ ትክክለኛ እና ስህተት መልሶችን በመንገር ላይ ብቻ ማተኮር አለበት፡፡ | | | | |
| 20 | በተከታታይ ምዘና ሂደት ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ /አስተያየት/ መሰጠት ያለበት በመምህራን እንጂ በተማሪዎች መሆን የለበትም፡፡ | | | | |
| 21 | በተከታታይ ምዘና ሂደት ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ /አስተያየት/ ማተኮር ያለበት ተማሪዎች የሚያሳዩትን ደካማ ጎን ለማስተካከል ነው፡፡ | | | | |

**ለ/ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበቡ በኋላ በቀረበው ሳጥን መሰል ክፍት ቦታ ውስጥ የ“×” ምልክት ያስቀምጡ፡፡**

1. በመማር ማስተማሩ ሂደት፣ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘናን ይጠቀማሉ?

   አዎ ☐ አይደለም ☐

2. በተራ ቁጥር 1 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ ተከታታይ ምዘናን በትምህርት ዕቅድዎ ውስጥ ታሳቢ በማድረግ ያካትታሉ?

   አዎ ☐ አይደለም ☐

3. በተራ ቁጥር 2 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ የሚከተሉትን ተግባራት በዕቅድዎ ውስጥ በግልጽ ያስቀምጣሉ?

   ሀ. የተከታታይ ምዘናውን ዓላማ፡- አዎ ☐ አይደለም ☐

   ለ.የተከታታይ ምዘናውን ጊዜ፡- አዎ ☐ አይደለም ☐

   ሐ. የተከታታይ ምዘናውን ዘዴ፡- አዎ ☐ አይደለም ☐

4. የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ተግባራት በአግባቡ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የመከታታያ /የመመዝገቢያ/ ቅጾች ይጠቀማሉ?

   አዎ ☐ አይደለም ☐

5. በተራ ቁጥር 4 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ተግባራት ለመከታተል /ለመመዝገብ/ የሚጠቀሙበት ቅጽ ከየት ያገኛሉ?

   ሀ. ትምህርት ቤቱ አዘጋጅቶ ይሰጠናል ☐

   ለ. በትምህርት ክፍል ደረጃ እናዘጋጃለን ☐

   ሐ. በራሴ አዘጋጃለሁ ☐

6. ለተማሪዎችዎ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ?

   አዎ ☐ አይደለም ☐

7. በተራ ቁጥር 6 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ ምጋቤ ምላሽ /አስተያየት/ በሚሰጡበት ጊዜ የመሚያተኩሩት በምን ላይ ነው?

   ሀ. ትክክለኛውን መልስ በመንገር ☐

   ለ. ትክክለኛውን መልስ በመንገርና ተማሪው ማዳበር ስለሚገባው ገንቢ አስተያየት በመስጠት ☐

8. ለተማሪዎችዎ ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡት መቼ መቼ ነው?

ሀ. በእያንዳንዱ የምዘና ተግባር ላይ ☐

ለ. ፈተናዎችን፣ የግል ስራዎችንና የቡድን ስራዎችን በምመልስበት ጊዜ ☐

ሰ

**ሐ. ከዚህ ቀጥሎ ከተከታታይ ምዘና የሚገኙትን መረጃዎች መሰረት ከማድረግ የተለያዩ ተግባራት ተዘርዝረዋል፡፡ ከተዘረዘሩት ተግባራት ትይዩ ደግሞ አማራጮች ቀርበዋል፡፡አማራጮችም በቁጥር የተወከሉ ሲሆን የሚከተሉትን የጊዜ ድግግሞሽ የሚያሳዩ የውሳኔ ሀሳቦች ናቸው፡፡**

3 = ሁል ጊዜ 2 = አልፎ አልፎ 1= አልጠቀምም

እርስዎም ጥያቄዎችን ካነበቡ በኋላ በጥያቄዎቹ ትይዩ የየሚሰጡትን መልስ የ"×" ምልክት በማድረግ ያመልክቱ፡፡

| ተ.ቁ | ዝርዝር ነጥቦች | አማራጮች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 3 | 2 | 1 |
| 1 | ተማሪዎች መማር ያለባቸውን የትምህርት ይዘት ለመወሰን | | | |
| 2 | ለደካማ ተማሪዎች የማስተካከያ እገዛ ለመስጠት | | | |
| 3 | ትምህርታቸውን በደንብ እየተከታተሉ ላሉ ተማሪዎች የማጠናከሪያ እገዛ ለመስጠት | | | |
| 4 | የሚቀጥለውን የትምህርት ዕቅድ ለማውጣት | | | |
| 5 | የትምህርት አቀራረቡን ለማስተካከል | | | |
| 6 | ተማሪዎች ግልጽ ያልሆነላቸውን ይዘት እንደገና ለማስተማር | | | |
| 7 | ምጋቤ ምላሽ/አስተያየት/ ለመስጠት | | | |
| 8 | የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማወቅ | | | |
| 9 | የምዘና ስልቶችን ለመወሰን | | | |

## ክፍል አራት ፡- ልቅ ጥያቄዎች

*መመሪያ፡- ከዚህ በታች ሦስት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ የእያንዳንዱን ጥያቄ መልሳችሁን በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ግለጹ ፡፡*

1. ከተከታታይ ምዘና ጋር በተያያዘ ስልጠና ተሳትፈው ያውቃሉ፡ መልስዎ አዎ ከሆነ ሀሳብዎን ቢገልፅሉን?

ሀ. የተከታታይ ምዘናው ሥልጠና ይዘቶች ምን ምን ነበሩ?

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------፡፡

ለ. የተከታታይ ምዘናው ሥልጠና በተከታታይ ምዘና አተገባበርዎ ላይ ያመጣው ለውጥ ምንድን ነው?

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------፡፡

2. ተከታታይ ምዘና እንዴት እንደሚተገብሩና በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ወቅት ያጋጠሙዎትን ችግሮች ካሉ ምን ምን ናቸው?

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------፡፡

3. በትምህርት ቤታችሁ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘናዎችን በአግባቡና በተሳካ ሁኔታ እንዲተገብሩ የሚያስችሉ ምን መደረግ አለበት ብለው ያስባሉ?

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------፡፡

# አባሪ ሐ

## የሰነድ ፍተሻ ማረጋገጫ መስፈርት /ቼክሊስት/

ክልል-------------------                                   ወረዳ-----------------------

ሰነዱ የተገኘበት ትምህርት ቤት ስም------------------------------

ሰነዱ የተዘጋጀለት ክፍልና ሴክሽን-------------------------

| ተ.ቁ | ዝርዝር ሀሳቦች | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1 | በትምህርት ቤቱ ተከታታይ ምዘና በወቅቱ ተዘጋጅቷል፤ ተካሂዷልም። | | |
| 2 | የሚዘጋጀው ምዘና ሦስቱ የትምህርት ዓላማዎች ያካተተ ነው፡፡ | | |
| 3 | ተከታታይ ምዘና የተማሪዎች ፍላጎት ያገናዘበ ነው፡፡ | | |
| 4 | ተከታታይ ምዘና መምህራንና ተማሪዎች ግለ ግምገማ እንዲያደርጉ እየጠቀመ ነው፡፡ | | |
| 5 | ትምህርት ቤቱ መስፈርት ተኮር ተከታታይ ምዘና ተግባራዊ አድርጓል፡፡ | | |
| 6 | ተማሪዎች ከሚፈለገው ደረጃ ደርሰዋል፡፡ | | |
| 7 | የትምህርቱ ይዘቶች በተቻለ ሁኔታ በፈተና ተካተዋል፡፡ | | |
| 8 | ተከታታይ ምዘና በመተግበር ወቅታዊ ግብረ መልስ ለተማሪዎች ተሰጥተዋል፡፡ | | |
| 9 | በትምህርት ቤቱ ተከታታይ ምዘና በመተግበሩ መልካም አስተዳደር ሰፍኗል፡፡ | | |
| 10 | በየጊዜው ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየታቸው የተሻለ ስነ ዘዴ ተግባራዊ ሆናል፡፡ | | |
| 11 | በትምህርት ቤቱ ውጤታማ የሆነ የድጋፍ እና ክትትል ስርዓት ተዘርግቷል፡፡ | | |

## አባሪ መ

በቃለ መጠይቅ ወቅት መረጃ የሰጡ የርዕሳነ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች ኮድና የሚሰሩበት ትምህርት ቤት

| ተ.ቁ | የመላሽ ኮድ | ሐላፊነት | ክልል | ወረዳ | የሚሰሩበት ትምህርት ቤት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 01 | ሱፐርቫይዘር ጉ/ማዕከል | አማራ | አበርገሌ | ማዕርነት |
| 2 | 02 | ርዕሰ መምህር | አማራ | አበርገሌ | ማዕርነት |
| 3 | 03 | ሱፐርቫይዘር ጉ/ማዕከል | አማራ | አበርገሌ | ሳቃ |
| 4 | 04 | ርዕሰ መምህር | አማራ | አበርገሌ | ሳቃ |
| 5 | 05 | ሱፐርቫይዘር ጉ/ማዕከል | ትግራይ | ሰሐርቲ ሳምረ | ፊናርዋ |
| 6 | 06 | ርዕሰ መምህር | ትግራይ | ሰሐርቲ ሳምረ | ፊናርዋ |
| 7 | 07 | ሱፐርቫይዘር ጉ/ማዕከል | ትግራይ | ጣንቋ አበርገሌ | የጭላ |
| 8 | 08 | ርዕሰ መምህር | ትግራይ | ጣንቋ አበርገሌ | የጭላ |

# አባሪ ሠ

## ለርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የቀረበ ቃለ-መጠይቅ

ውድ መምህራን! ቃለ- መጠይቅ ዋና ዓላማ በአማራ ክልላዊ መንግስትና በትግራይ ክልላዊ መንግስት 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ምን እንደሚመስል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ይህን መረጃ መሰብሰብ ያስፈለገበት ምክንያት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒትስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ማስተማር የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ጥናታዊ ጽሑፍ ለማዘጋጀት ነው፡፡ በመሆኑም ከመጠይቁ የሚገኘው መረጃ የተጀመረው ጥናት መሳካት ከፍተኛ እገዛ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

የተከበሩ ----------------------------------------------

በዚህ ቃለ-መጠይቅ ተሳታፊ ለመሆን በመፍቀድዎንና ውድ የስራ ጊዜዎን ሰውተው ስለሚሰጡኝ መረጃ አስቀድሜ አመሰግናለሁ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በትምህርት ቤታችሁ ያለውን የተከታታይ ምዘና አተገባበር በተመለከተ እጠቃለሁ ፡፡

## ከቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

**በማዕርነትና በሳቃ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከርዕሳነ መምህራንና ከሱፐርቫይዘሮች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ መረጃ ትንተና**

በዚህ ንኡስ ምዕራፍ ስር በሁለቱም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሁለት ሱፐርቫይዘሮችና ሁለት ርዕሳነ መምህራን የተደረገውን ቃለ መጠይቅ ይቀርባል፡፡

**ጥያቄ** 1፡- በትምህርት ቤታችሁ የተከታታይ ምዘና አተገባበር ምንድን ነው ብለው ያምናሉ? በተለይ የተቀመጠውን ግብና ዓላማ ከማሳካት አኳያ የመምህራንና የትምህርት ቤታችሁ ሚና፣ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ከማርካት አንጻር የተለያየ ዕቅድ በማቀድ እየተተገበረ ነው ብለው ያስባሉ ወይ?

1.1 መልስዎ አዎ ከሆነ ምን አይነት የአተገባበር ስልት ነው የምትጠቀሙት፣

1.2 ምንም ዓይነት የተዘረጋ የአተገባበር ስልት ከሌለ ለምን እንዳልተዘረጋ ሰፋ ባለ መልኩ ይግለጹ፡፡ ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ የርዕሳነ መምህራኑና የሱፐርቫዘሮቹ ምላሽ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

**መላሽ ኮድ 01፡-** በትምህርት ቤታችን ሁለቱም የምዘና ዓይነቶች ማለትም ሂደታዊና ማጠቃለያ ተከታታይ የምዘና ዓይነቶች እንጠቀማለን፡፡ በተለይ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና መጠቀማችን የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት እያሟላ ይገኛል፡፡ በተለይ ተማሪዎች በየዕለቱ መመዘን እንዳለባቸው በትምህርት ቤት ደረጃ ዕቅድ አውጥተን እየሰራን እንገኛለን ብሏል፡፡

***መላሽ ኮድ 02፡-*** ከመላሽ ኮድ 01 ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

**መላሽ ኮድ 03፡-** "ሂደታዊና ማጠቃለያ ተከታታይ የምዘና ዓይነቶች እንጠቀማለን፡፡ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ለውጤት ሳይሆን የመማር ማሳተማሩን ሂደት ለማስተካከል እንጠቀማለን፡፡ በትምህርት ቤት ደረጃም የአተገባበር ስልት ዘርግተን እንተገብራለን"፡፡

**መላሽ ኮድ 04፡-** "ሂደታዊና ማጠቃለያ ተከታታይ ምዘናዎች እንጠቀማለን፡፡"

2. የተከታታይ ምዘና መተግበር ከጀመረ በኋላ የተገኙ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ምንድን ናቸው? የሚከተሉት ነጥቦች ግምት ውስጥ በማስገባት ፡-

2.1 የታዩትን ጠንካራ ጎኖች ፡-

- የተማሪዎች የመማር ሂደት ከማወቅ አንጻር፡
- ተማሪዎች የተለያየ የመማር ችሎታ እንዳላቸው ከመለየት፣
- የታቀዱ ግቦች በሚገባ ከማሳካት፣
- ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ተከታታይ ምዘና ከመተግበር አንጻር፣
- ተከታታይ ምዘና መረጃ ለመሰብሰብ ከመጠቀም አኳያ፣
- የመማር ማስተማር ሂደት በማጠናከር አንድ አካል ተደርጎ ከመውሰድ አኳያ፣
- ተከታታይ ምዘና ቢጋሩ መሰረት በማድረግ የተመዘገበ ውጤት ካለ በጠንካራ ጎን አንድ በአንድ ይግለጹ፡፡

2.2 የታዩት ደካማ ጎኖች ለተለዩ ተከታታይ ምዘና ከመተግበር አንጻር ያሉት ክፍተቶች ምንድን ናቸው ብለው ያምናሉ፣

በተራ ቁጥር 4 ለቀረበው ጥያቄ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሰጡትን ምላሽ፡-

**መላሽ** ኮድ 01፡- በትምህርት ቤታችን ተከታታይ ምዘና በመተግባራችን የታዩትን ጠንካራ ጎኖች የተማሪዎች የመማር ሂደት ከማወቅ አንጻር፣ ተማሪዎችን በሦስቱ የብቃት ደረጃዎች ለይተን እንጠቀማለን፡፡ ይህ የምዘና ስልት መረጃ ለመሰብሰብም እንጠቀምበታለን፡፡ ይሁን እንጂ የታቀዱ ግቦች በሚገባ ከማሳካት፣ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ተከታታይ ምዘና ከመተግበር አንጻር፣ የመማር ማስተማሩ ሂደት በማጠናከር አንድ አካል ተደርጎ ከመውሰድ አኳያ፣ ተከታታይ ምዘና ቢ.ጋሩ መሰረት በማድረግ ጥሩ የሆነ ውጤት አለመኖር፣ ተማሪዎች በምዘና ወቅት መቅረትና ሁሉም መምህራን ተግባራዊ አለማድረግ ይታያል፡፡

**መላሽ** ኮድ 02፡- ተከታታይ ምዘና በትምህርት ቤታችን ተግባራዊ ማድረጋችን የተማሪዎች ባህሪይ ከማወቅ፣ የክፍል ሥራ በመስጠት የማስተማር ስነ ዘዴ ከመቀየርና ከዚህ የሚገኘውን ውጤት ከማሻሻል አንጻር ጥሩ ነው፡፡ ተማሪዎች በአቀባበል ብቃታቸው መለየት ተችሏል፡፡ የእርስ በርስ መደ.ጋገፍ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ይሁን እንጂ በአንዳንድ መምህራን የምዘና ዓይነቶች ለይተው ያለማወቅና የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ለነጥብ መጠቀም ይታያል፡፡

**መላሽ ኮድ** 03፡- “ሦስቱም የመማር ብቃት መሠረት በማድረግ በልየታ ተማሪዎችን ለመደገፍ እንጠቀምበታለን፡፡ ብዙ ጠቀሜታ ቢኖረውም ሁል ጊዜ ያለመተግበር ችግር ይታያል፡፡”

**መላሽ ኮድ** 04፡- የተከታታይ ምዘና አሳታፊ መማር ማስተማር ተግባራዊ ለማድረግና ድ.ጋፍ ለመስጠት እንዲሁም ጾታዊ ተሳትፎ ለማረ.ጋገጥ መጠቀም መቻል በጥንካሬ የሚወሰድ ቢሆንም በዕቅድ የተመራ ምዘና ያለማድረግ፣ የተመዘነውን ነጥብ ለውጤት መያዝ እንደድክመት ይታያል፡፡

3. የተከታታይ ምዘና አተገባበር በቀጣይነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ምን ዓይነት መፍትሄ መወሰድ አለበት፣ የመምህራን ሀላፊነት ከመወጣት አንጻር እንዴት መሻሻል አለበት ብለው ያምናሉ?

**መላሽ ኮድ 01፡-** እጥረቶች በመፈተሽ ግንዛቤ መፍጠር፣ ተከታታይ የሆነ ድጋፍ ማድረግ፣ መምህራን የተከታታይ ምዘና ውጤት አለፈ ወይም ወደቀ ማለት ሳይሆን የማስተማር ዘዴ ለማስተካከል እንዲጠቀሙበት ማድረግ፣ በግድየለሽነት ወይም በመሰላቸት ተከታታይነት ያለውና በዕቅድ የተመራ ምዘና እንዲጠቀሙ ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

**መላሽ ኮድ 02፡-** "ተከታታይ ምዘና አማራጭ ሂደት በመሆኑ መምህራን ሊጠቀሙበት ይገባል"፡፡

**መላሽ ኮድ 03፡-** "መምህራን በየዕለቱ ተማሪዎቻቸውን በተከታታይ እንዲመዝኑ ማገዝና የእርስ በርስ ሱፐርቪዥን መዘርጋት ያስፈልጋል"፡፡

**መላሽ ኮድ 04፡-** "መምህራን በዕቅድ የተመራ ተከታታይ ምዘና ተግባራዊ እንዲያደርጉ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል"፡፡

4.በትምህርት ቤታችሁ የትኛው የተከታታይ ምዘና ዓይነት ሂደታዊ ወይስ ማጠቃለያ ምዘና ሁል ጊዜ የሚተገበረው፣

4.1 መልስዎ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ከሆነ እንዴት እንደሚተገበር ሰፋ ባለ መልኩ ይግለጹ፡፡

4.2 መልስዎ ማጠቃለያ ተከታታይ ምዘና ከሆነ በምን አገባብ እንደሚተገበር ቢያብራሩልኝ ፡፡

**መላሽ ኮድ 01፡-** በትምህርት ቤታችን ሁለቱም የምዘና ዓይነቶች ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡ የተማሪዎች የመማር ዕድገት ለማወቅ ሂደታዊ የምዘና ስልት እንጠቀማለን፡፡ እንዲሁም ከአንድ ክፍል ወደ ሌላ ክፍል ለመዛወር ደግሞ ማጠቃለያ የምዘና ስልት እንጠቀማለን፡፡

**መላሽ ኮድ 02፡-** "ሁለቱም የምዘና ዓይነቶች እንጠቀማለን፡፡"

**መላሽ ኮድ 03፡-** "ሁለቱም የምዘና የምንጠቀም ስንሆን ሁል ጊዜ በሳምንት አንድ በወር ደግሞ 4 ጊዜ አጭር ፈተና እንፈትናለን፡፡ ከፈተናቸው ፈተና የተሻለውን ይያዛል፡፡"

**መላሽ ኮድ 04፡-** "ለድጋፍ ስርዓቱ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ጠቃሚ ቢሆንም የትምህርት ቤታችን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከመሰልቸት የተነሳ በብዛት የሚጠቀሙት ማጠቃለያ ምዘናን ነው፡፡"

5. በትምህርት ቤታችሁ ተከታታይ ምዘና አተገባበር ውጤታማ እንዲሆን በየደረጃ የሚገኙ አካላት የሚያደርጉት ድጋፍ አሰጣጥ ስርዓት እንዲሆም በተከታታይ ምዘና ውጤታማነት ዙሪያ ያላቸው እምነትና አመለካከት እንዴት ይገለጻል?

**መላሽ ኮድ 01፡-** በትምህርት ቤታችን የተከታታይ ምዘና አተገባበሩ መምህራን በራሳቸው የምዘና ዕቅድ ያወጣሉ፣ ባወጡት ዕቅድ መሰረትም ተግባራዊ እንዲሆን ክትትል እናደርጋለን፡፡ ነገር ግን በርካታ መምህራን ዕቅድ ቢያወጡም ተግባራዊ ግን አላደርጉም፡፡ ችግር ያለባቸው መምህራን በመለየት ስልጠና ይሰጣል፣ የእርስ በርስ ሱፐርቪዥን ይካሄዳል፡፡

**መላሽ ኮድ 02፡-** የተከታታይ ምዘና አተገባበር ውጤታማ እንዲሆን በትምህርት ቤት ደረጃ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ይለያሉ፡፡ በተለየው መሰረትም የተከታታይ ምዘና መልካም ተሞክሮዎች ተቀምረው ውይይት እናደርጋለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተማሪዎች ማህደር በመፈተሽ ያሉበትን ደረጃ እናስቀምጣለን፡፡ይሁን እንጂ መምህራን ተከታታይ ምዘና ሁል ጊዜ አይተገብሩም፡፡

**መላሽ ኮድ 03፡-** ተመሳሳይ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

**መላሽ ኮድ 04፡-** ተመሳሳይ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

6. በመጨረሻ ሌሎች በተከታታይ ምዘና አተገባበር ዙሪያ ጠቃሚ የሚባሉት ሀሳቦች በባለድርሻ አካላት ችግሮችን ለመፍታት መደረግ የሚገባቸውን ነገሮች ካሉ ሰፋ ባለ መልኩ ቢገልጹልኝ፡፡

**መላሽ ኮድ 01፡-** ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና በመማር ማስተማር ሂደት ተግባራዊ የማይሆን ከሆነ መማር ማስተማሩ ሕይወት የለውም፡፡ ስለዚህ ሁሉም መምህራን ተከታታይ ምዘና

እንደ አንድ የትምህርት አካል ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡ በተከታታይ ምዘና ዙሪያ ተማሪዎችና መምህራን ውይይት ማድረግ አለባቸው፡፡

**መላሽ ኮድ** 02፡- ተመሳሳይ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

**መላሽ ኮድ** 03፡- ተመሳሳይ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

## በየጭላና በፌናርዋ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከርዕሳነ መምህራንና ከሱፐርቫይዘሮች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ መረጃ ትንተና

በዚህ ንኡስ ምዕራፍ ስር በሁለቱም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሁለት ሱፐርቫይዘሮችና ሁለት ርዕሳነ መምህራን የተደረገውን ቃለ መጠይቅ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ጥያቄ** 1፡- በትምህርት ቤታችሁ የተከታታይ ምዘና አተገባበር ምንድን ነው ብለው ያምናሉ? በተለይ የተቀመጠውን ግብና ዓላማ ከማሳካት አኳያ የመምህራንና የትምህርት ቤታችሁ ሚና፣ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ከማርካት አንጻር የተለያየ ዕቅድ በማቀድ እየተተገበረ ነው ብለው ያስባሉ ወይ?

1.1 መልስዎ አዎ ከሆነ ምን አይነት የአተገባበር ስልት ነው የምትጠቀሙት፣

1.2 ምንም ዓይነት የተዘረጋ የአተገባበር ስልት ከሌለ ለምን እንዳልተዘረጋ ሰፋ ባለ መልኩ ይግለጹ፡፡ ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ የርዕሳነ መምህራኑና የሱፐርቫዘሮቹ ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**መላሽ ኮድ** 05፡- አዎ፡፡ በትምህርት ቤታችን ተከታታይ ምዘና በየጊዜው ይተገበራል፡፡ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ዕድገት ለመከታታል ዕቅድ አውጥተው ሁል ጊዜ ይመዝናሉ፡፡ በሳምንት አንድ ጊዜ የጽሑፍ ፈተና ይሰጣል፡፡

**መላሽ ኮድ** 06፡- የኮድ 05 ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

**መላሽ ኮድ** 07፡- ተከታታይ ምዘና ሁሉም የትምህርት ቤታችን መምህራን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ በመጀመሪያ ሁሉም መምህር የተከታታይ ምዘና ዕቅድ ያወጣሉ፤ በዕቅዳቸው መሰረትም ተማሪዎቻቸውን ይመዝናሉ፡፡ መምህራን የሐሰት የነጥብ ማጠራቀሚያ

በማዘጋጀት ተከታታይ ምዘና ከቃል ጥያቄዎች ጀምሮ እስከ አጭር የጽሑፍ ፈተና ይፈትናሉ፡፡

**መላሽ ኮድ 08፡-** ከመላሽ ኮድ 07 ጋር ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

**ጥያቄ** 2. የተከታታይ ምዘና መተግበር ከጀመረ በኋላ የተገኙ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ምንድን ናቸው? የሚከተሉት ነጥቦች ግምት ውስጥ በማስገባት ፡-

2.1 የታዩትን ጠንካራ ጎኖች ፡-

- የተማሪዎች የመማር ሂደት ከማወቅ አንጻር፤
- ተማሪዎች የተለያየ የመማር ችሎታ እንዳላቸው ከመለየት፣
- የታቀዱ ግቦች በሚገባ ከማሳካት፣
- ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ተከታታይ ምዘና ከመተግበር አንጻር፣
- ተከታታይ ምዘና መረጃ ለመሰብሰብ ከመጠቀም አኳያ ፣
- የመማር ማስተማር ሂደት በማጠናከር አንድ አካል ተደርጎ ከመውሰድ አኳያ ፣
- ተከታታይ ምዘና ቢጋሩ መሰረት በማድረግ የተመዘገበ ውጤት ካለ በጠንካራ ጎን አንድ በአንድ ይግለጹ፡፡

**መላሽ ኮድ** 05፡- በትምህርት ቤታችን ተከታታይ ምዘና መተግበር ከተጀመረ የታዩት ጠንካራ ጎኖች የተማሪዎች የመማር ሂደት ከማወቅ አንጻር፣ ተማሪዎች የተለያየ የመማር ችሎታ እንዳላቸው ከመለየት፣ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ከመተግባር አንጻር፣ እንደመረጃ ምንጭ ከመጠቀም አንጻርና የመማር ማስተማር ሂደት በማጠናከር አንድ አካል ተደርጎ ከመውሰድ አኳያ በጠንካራ ጎን የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

**መላሽ ኮድ** 06፡- በትምህርት ቤታችን ተከታታይ ምዘና በመተግበራችን ተማሪዎች ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንድንለይ አስችሎናል፡፡

**መላሽ ኮድ 07፡-** የተከታታይ ምዘና በመተገበር የተማሪዎችን ተሳትፎና ውጤት ሊሻሻል ችሏል፡፡ በተለይ በመስከረም ወር የመግቢያ ፈተና ፈትነን ተማሪዎች ያሉበትን ደረጃ በመለየት ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን በመያዝ መምህራን የማስተማር ስነ ዘዴ እያቀያየሩ እንዲጠቀሙ አስችሏል፡፡

**መላሽ ኮድ 08፡-** ከኮድ 07 ጋር ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

2.2 የታዩት ደካማ ጎኖች ለተለዩ ተከታታይ ምዘና ከመተግበር አንጻር ያሉት ክፍተቶች

ምንድን ናቸው ብለው ያምናሉ?

**መላሽ ኮድ 05፡-** ምንም እንኳን መምህራን ተከታታይ ምዘና በመተግበራቸው በርካታ ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩም የታቀዱ ግቦች ከማሳካት አንጻርና የተከታታይ ምዘና ቢጋሩ መሰረት በማድረግ አመርቂ የሆነ ውጤት ሊመጣ አልቻለም፡፡

**መላሽ ኮድ 06፡-** ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

**መላሽ ኮድ 07፡-** የተከታታይ ምዘና ስርዓቱ ሳይሆን በትግበራው ላይ ችግር ይታያል፡፡ በተወሰኑ መምህራን ውጤት ተኮር አድርጎና በአንዳንድ መምህራን በኩል ደግሞ ከስራ ጫና ጋር በማያያዝ ሁል ጊዜ ለመተግበር ስልቹ መሆን ናቸው፡፡

**መላሽ ኮድ 08፡-** አንዳንድ ተማሪዎች በተከታታይ ሲመዘኑ ለመመዘን ዝግጁ ሆኖ ያለመምጣት ችግር ይታያል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በተከታታይ መቅረት ለመመዘንና ለመደገፍ የሚያስቸግርበት ሁኔታ አለ፡፡

**ጥያቄ** 3. የተከታታይ ምዘና አተገባበር በቀጣይነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ምን ዓይነት መፍትሄ መወሰድ አለበት? የመምህራን ሀላፊነት ከመወጣት አንጻር እንዴት መሻሻል አለበት ብለው ያምናሉ?

**መላሽ ኮድ 05፡-** የተከታታይ ምዘና አተገባበር በቀጣይነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል መምህራን ምዘናው በሳምንት ወይም በሁለት ሳምንት ከመመዘን ይልቅ በየቀኑ ቢመዝኑ የተሻለ ይመስለኛል፡፡

**መላሽ ኮድ 06፡-** መምህራን ስለተከታታይ ምዘና በቂ የሆነ ዕውቀትና ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪም የመማር ማስተማር ሂደት አንድ አካል እንደመሆኑ መጠን መምህራን አላስፈላጊ ምክንያት ከመደርደር ይልቅ ተማሪዎቻቸውን በተከታታይ በፍላጎት ሊመዝኑ ይገባል፡፡

**መላሽ ኮድ 07፡-** መምህራን ከመሚረቁበት ተቋም ስለተከታታይ ምዘና ጠቀሜታ ተምረው ቢመጡም ለመተግበር ግን በጣም ይቸገራሉ፡፡ ዕውቀት የሚባል ግን ስለጉዳዩ ያለን

ግንዛቤ ሳይሆን ያለንን ዕውቀት በተግባር ስናውለው ስለሆነ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በተከታታይ ሊመዝኑ ይገባል፡፡

**መላሽ ኮድ 08፡-** ከኮድ 07 መላሽ ጋር ተመመሳሳይ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

**ጥያቄ 4.** በትምህርት ቤታችሁ የትኛው የተከታታይ ምዘና ዓይነት ሂደታዊ ወይስ ማጠቃለያ ምዘና ሁልጊዜ የሚተገበረው፣

4.1 መልስዎ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ከሆነ እንዴት እንደሚተገበር ሰፋ ባለ መልኩ ይግለጹ፡፡

4.2 መልስዎ ማጠቃለያ ተከታታይ ምዘና ከሆነ በምን አገባብ እንደሚተገበር ቢያብራሩልኝ ፡፡

**መላሽ ኮድ 5፡-** በትምህርት ቤታችን ሁለቱም የምዘና አይነቶች ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና በሳምንት አንድ ጊዜ እንመዝናለን፤ እንዲሁም ማጠቃለያ ፈተና እንመዝናለን፡፡

**መላሽ ኮድ 06፡-** ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

**መላሽ ኮድ 07፡-** ተከታታይና ማጠቃለያ ምዘናዎች እንጠቀማለን፡፡ ተከታታይ ምዘና የቃል ጥያቄዎች የመምህራን የሁል ጊዜ ተግባር ሲሆን የቡድን ስራና የግል ስራዎችም በተቻለ መጠን ይሰጣል፡፡ ማጠቃለያ ፈተናዎች ደግሞ ለውጤት ይፈትናሉ፡፡

**መላሽ ኮድ 08፡-** ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

**ጥያቄ 5.** በትምህርት ቤታችሁ ተከታታይ ምዘና አተገባበር ውጤታማ እንዲሆን በየደረጃ የሚገኙ አካላት የሚያደርጉት ድጋፍ አሰጣጥ ስርዓት እንዲሆም በተከታታይ ምዘና ውጤታማነት ዙሪያ ያላቸው እምነትና አመለካከት እንዴት ይገለጻል?

**መላሽ ኮድ 05፡-** የተከታታይ ምዘና አተገባበር ውጤታማ እንዲሆን ተማሪዎች በዕውቀትና በውጤት የተሻሉ እንዲሆኑ መምህራን ሁል ጊዜ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ በየደረጃው የሚገኙ አካላትም የሚያደርጉትን ድጋፍ፣ በተለይ ደግሞ የግንዛቤ እጥረት ላለባቸውም የግንዛቤ መፍጠሪያ ስልጠና መስጠት ከተቻለ የተከታታይ ምዘና ስርዓቱ ውጤታማ ሊሆን ይችላል፡፡

**መላሽ ኮድ 06፡-** ተመሳሳይ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

**መላሽ ኮድ 07፡-** ተከታታይ ምዘና ውጤታማ እንዲሆን በእምነት ደረጃ ሁሉ ቢቀበለውም ለመተግበር ግን ይቸገራል፡፡ ስለዚህ ሁሉም መምህራን በተከታታይ ምዘና ዙሪያ ጥሩ የሆነ ግንዛቤ ከተፈጠረ ተግባራዊ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ በተለይ ደግሞ በጽሑፍ ፈተና ፈትኖ ለውጤት መያዝ ሳይሆን የዘዴ ማቀያየሪያ ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

**መላሽ ኮድ 08፡-** ተመሳሳይ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

6. በመጨረሻ ሌሎች በተከታታይ ምዘና አተገባበር ዙሪያ ጠቃሚ የሚባሉት ሀሳቦች በባለድርሻ አካላት ችግሮችን ለመፍታት መደረግ የሚገባቸውን ነገሮች ካሉ ሰፋ ባለ መልኩ ቢገልጹልኝ፡፡

## አባሪ ረ

## የተከታታይ ምዘና አተገባበር የክፍል ውስጥ ምልከታ ማረጋገጫ ዝርዝር /Checklist/

የትምህርት ቤቱ ስም----------------------------- ክልል----------------- ወረዳ---------------

ሴክሽን--------- ምልከታው የተካሄደበት ቀን--------------- የተማሪዎች ብዛት ወንድ------- ሴት------ ድምር----------- ሰዓት-------------

**ለረዳት ተመልካች የተሰጠ መመሪያ፡-** ይህ የማረጋገጫ ዝርዝር ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት የክፍል ውስጥ የተማሪና የመምህር የተከታታይ ምዘና ክንውኖች የ/X/ ምልክት በማድረግ ብዛቱን የመዝግቡ፡፡ ስለክንውኑ ሁኔታ የሚገልጹት ካለ አስተያየት ከሚለው ስር በጽሑፍ ይግለጹ፡፡

| ተ.ቁ | የመምህሩ ተግባር | ተከናውኗል | አልተከናወነም | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የተከታተይ ምዘና ዘዴዎችን መጠቀም | | | |
| 1.1 | የቃል ጥያቄ ማካሄድ | | | |
| 1.2 | የክፍል ሥራ ማሰራት | | | |
| 1.3 | የቤት ሥራ መስጠት | | | |
| 1.4 | የቡድን ተግባራትን ማሰራት | | | |
| 1.5 | የክፍል ውስጥ ምልከታ ማካሄድ | | | |
| 1.6 | የቢጤ ምዘና እንዲካሄድ ማድረግ | | | |
| 1.7 | ተማሪዎች በጓደኞቻቸው ፊት እየወጡ እንዲያቀርቡ ማድረግ | | | |
| 1.8 | የግል ሥራን ማሰራት | | | |
| 1.9 | የመምህር ተማሪ ውይይት ማካሄድ | | | |
| 1.10 | ሙከራና ፈተና መስጠት | | | |
| 1.11 | ሰነደ ትምህርት መጠቀም | | | |
| 1.12 | ተማሪዎች ራሳቸውን እንዲገመግሙ ማድረግ | | | |
| 2 | ምጋቤ ምላሽ መስጠት | | | |
| 2.1 | ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ መስጠት | | | |
| 2.2 | ጽሑፋዊ ምላሽ መስጠት | | | |

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች የተጠቀሰው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ማስተማር መርሐ ግብር ተማሪ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የራሴ መሆኑንና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው ተዛማጅ ጽሑፎችና የመረጃ ምንጮች በሙሉ በአግባቡ የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ገብረመስቀል ገብረእግዚአብሔር

ፊርማ……………………

አድራሻ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

አዲስ አበባ

ነሐሴ 2009 ዓ.ም